የብርጌዶች ውጣ-ውረድ
(አርማጭሆ)

የ7ኛ ክፍለ ጦር 17ኛ ብርጌድ በሌ/ኮ (በኋላ ብ/ጄ) አብደላ መሐመድ የሚመራ ጀግና ሠራዊት ነው። ሁመራ ላይ ሠፈሩን አድርጎ የወልቃይት ጠገዴንና የአርማጭሆን አካባቢ ከተቃዋሚ ቡድኖች አፅድቷል። ከአርማጭሆ ህዝብ ጋር በመተባበርም የጉንደር ሁመራ መንገድ እንዳይዘጋ ከመጣሩም በላይ የአካባቢው ልማት እንዳይቋረጥ የራሱን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል።

የአርማጭሆ ህዝብ ከሠራዊታችን ጋር በትብብር ተቃዋሚዎችን ሲፋለም ይኼ የመጀመሪያው አይደለም። እንዲያውም ያለ ሠራዊት ድጋፍ ብቻቸውን ተዋግተው ከተማ በማስለቀቅ ለጦሩ ያስረከቡበት ጊዜም አለ። እንዲህ ነው።

በ1967 ዓ.ም እኔ 2ኛ ክፍለ ጦር የትምህርትና የዘመቻ መኮንን በነበርኩበት ጊዜ ነው። የሁመራ አካባቢ የሚጠበቀው በ4ኛ እግረኛ ሻለቃ ነበር። በወቅቱ በዚያና በጋሉጅ አካባቢ የሚንቀሳቀሰው ጀብሃ ነበርና ባልታሰበ አኳኋን መጥቶ የ4ኛ ሻለቃን ይዞታ ያስለቅቃል። አካባቢውን ተቆጣጥሮ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ በማውረድ የራሱን ምልክት ይሰቅላል።

በዚህ ጊዜ የአርማጭሆ ህዝብ በመናደድ በ4ኛ ሻለቃ ሬዲዮ አቋሙን ያሳውቃል። "ተቃዋሚውን እኛ እናስወጣለን። አውሮፕላን በቦታው ላይ ዝቅ ብሎ ይብረርልን፣ እኛን ከተቃዋሚው ሊለይ ስለማይችል እንዳይተኩሰ" ይላሉ። ይኼ መልዕክት ለእኔ ይደርሰኛል። ሁኔታውን ካጣራን በኋላ በወቅቱ የ2ኛው አየር ምድብ አዛዥ ለነበሩት ለኮ/ል (በኋላ ሜ/ጀ) ፋንታ በላይ እናሳውቃለን። የክ/ጦሩ አዛዥ ብ/ጀ ወርቁ መኮንንም ትዕዛዝና መመሪያ ይሰጣሉ።

ከአንድ ቀን በፊት አውሮፕላን የሚመጣበትን ሠዓት ለአርማጭሆ ህዝብ እናሳውቃለን። ይዜን መልዕክት በ4ኛ ሻለቃ ሬዲዮ የደረሳቸው የአርማጭሆ አርበኞች በዕለቱ በአካባቢው አድፍጠው ይጠብቃሉ። እንደ ምክክሩ አውሮፕላኑ በአካባቢው ዝቅ ብሎ መብረር

ሰጀምር ያደፈጡት የአርማጭሆ አርበኞች ተኩስ ይከፍታሉ። ካደፈጡበት በመውጣት ጀብሃን አጥቅተው ከሁመራ በማስወጣት ጋሉጅ አካባቢ ያደርሱታል። ከዚህ በኋላ የጀብሃን አርማ ከተሰቀሰበት አውርደው በማቃጠል የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ቦታው የመለሱ ጀግና ህዝቦች ናቸው። ሁመራንም ለ4ኛ ሻለቃ መልሰው በማስረከብ ከጎኑ ሳይለዩ ጥበቃቸውን አጠናክረዋል።

የ7ኛ ክፍለ ጦር 18ኛ ብርጌድ

በሌ/ኮ (በኋላ ኮሎኔል) በቀለ ኃይሌ የሚመራው 18ኛ ብርጌድ አንድ ግዳጅ ይሰጠዋል። ግዳጁም በአነስተኛ ጦር ይጠበቅ ከነበረው ከአሥመራ ቃኘው ጦር ሠፈር በስተምዕራብ 2 እና 3 ኪ.ሜትር ርቆ የሚገኘውን መከላከያ ቦታ እንዲይዝ ነው። ቦታው ለአስመራ ከተማ እጅግ ቅርብ በመሆኑ ተቃዋሚዎች አልፎ አልፎ በማዘናጋት የአዳፍኔ ጥቃት ይሰነዝሩ ነበር። አስመራ ከተማና ወደ አውሮፕላን ማረፊያው በሚተኮሰው አዳፍኔ የበለጠ ጉዳት ከመድረሱ በፊት 18ኛ ብርጌድ ግዳጁን እንዲቀበል ይደረጋል።

ሌ/ኮ በቀለ ኃይሌ በራሳቸው አነሳሽነትም ሆነ ከክ/ጦሩና ከሰሜን ዕዝ አዛዦች በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴና ይዞታ በማጥናት ባልታሰበ ቀን የማጥቃት እርምጃ ይወስዳል። ሊነጋጋ ሲል በተወሰደው ተደጋጋሚ የማጥቃት እርምጃ ተቃዋሚውን ከፀአዛ ክርስቲያን በማስለቀቀ አስመራን ከከባድ መሳሪያ ድብደባ ሥጋት እንድትላቀቅ አደረጋት። ሌ/ኮ በቀለ ኃይሌ አሁንም ባልተጠበቀ ጊዜ ከፀአዛ ክርስቲያን በመነሳት የማጥቃት እርምጃ ወስደው ይዞታቸውን ያስፋፋሉ። በዚህም ከአስመራ ምዕራብ አዲገብሩ በመያዝ ከተማዋን በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ እንድትገኝ አድርገዋታል።

ሌ/ኮ (ብ/ጄ) ውበቱ ደግሞ 28 ሜካናይዝድ ብርጌድን በመያዝ ከ2ኛ አየር መደብ ምዕራብ ካለችው ማሪያም ቤተክርስቲያን ተነስተው በየጊዜው ከዕዙ ጋር በመነጋገር ይዞታቸውን አሻሽለው አዲተክላይን ይይዛሉ። በሁለቱ መኮንኖች ማለትም በሌ/ኮ በቀለ ኃይሌና በሌ/ኮ ውበቱ አመራር የአስመራ ከተማ በምዕራብ በኩል ከሚደረግ የተቃዋሚዎች ማጥቃት ሥጋት ድና ነበር።

በዚህ ጊዜ የአዛዦች ለውጥ ተደርጎ የሰሜን ዕዝ አዛዥ የነበሩት ኮ/ል (ሜ/ጄ) ኃይሉ ገብረሚካኤል በምክትላቸው በኮ/ል መርእድ ንጉሴ እንዲተኩ ይደረጋል። ኮ/ል መርዕድ ንጉሴ የሰሜን ዕዝ አዛዥ ሆነው እንደተሾሙ እኔን አስጠርተውሎ አንድ ትዕዛዝ ያስተላልፉልኛል።

የአስመራ ምፅዋን መንገድ ለመክፈት በሁለት አቅጣጫ ለተዘጋጀው ጦር አስተባባሪ እንድሆን ነበር ትዕዛዝ የሰጡኝ። እኔም የ7ኛው ክፍለ ጦር አዛዥነቴ እንዳለ ሆኖ የአስተባባሪነቱን ሥራ ደርቤ ለመጀመር ወደ ደንጎሎ ተንቀሳቀስኩ።

የሰሥጠራ ምፅዋ መንገድ መዘጋት

የአስመራ ምፅዋ መንገድ በሰሜን ዕዝ ስር ላለው ጦር ዋነኛ የድርጅት ማቅረቢያ ሆኖ እንዲሰራ የተደረገበት ምክንያት ከዲስ አበባ በደሴ፣ መቀሌና አስመራ ያለው አንድ መንገድና ሌላኛው አማራጭ ከጐንደር በአድዋ አስመራ መንገድ ሁለቱም በመቋረጣቸው ነበር። እነዚህ ሁለት መስመሮች ከመዘጋታቸው በፊት ግን የአስመራ ምፅዋ መንገድ ሁለተኛ አማራጭ ነበር። ይሄ አንድ አማራጭ መንገድ የተዘጋው እንዲህ ነው።

30ኛ እግረኛ ሻለቃ የነበረበትን የምፅዋን ጥበቃ ለ11ኛ ሻለቃ እንዲያስረክብና ወደ አስመራ እንዲዘዋወር ይወሰናል። 11ኛ ሻለቃ በ351ኛ እግረኛ ሻለቃ አጠናካሪነትና አጃቢነት ምፅዋ ይገባል። 30ኛ እግረኛ ሻለቃ ቦታውን ለ11ኛ ሻለቃ ካስረከበ በኋላ ምፅዋን ለመሰናበት ሲዘናና ያድራል። አየሩ ሞቃት ከመሆኑም በላይ ከድካሙ ሳያገግም በማግስቱ ሲነጋጋ ወደ አስመራ እንዲያቀና ይታዘዛል። ሩሲያ ሰራሽ የሆኑት አዳዲስ ብረት ለበስ (ቢ.ቲ.አር) ተሽከርካሪዎችን ይዞ እንዲንቀሳቀስ ነበር የታዘዘው። ተሽከርካሪዎቹ መሣሪያ ያልተገጠመላ ቸውና ከተራ መኪና የማይሻሉ ስለነበሩ ከመንቀሳቀሳቸው አስቀድሞ መሣሪያው ሊገጠምላቸው ይገባ ነበር። በትዕዛዙ መሠረት 30ኛ እግረኛ ሻለቃ፣ በ351ኛ እግረኛ ሻለቃ አጠናካሪነት እንቅስቃሴው ይጀመራል።

ሻዕቢያ ምፅዋ ውስጥ ባሉ መረጃዎቹ ጦሩ ሲዘናና ማደሩንና ከድካሙ ሳያገግም እንቅስቃሴ የሚጀምር ለመሆኑ ቀድሞ ተነግሮታል። በዚህም ከአስመራ 80 ኪሎ ሜትር ማይ አጣል የተባለ ቦታ ላይ ደፈጣ ይዞ በመጠባበቅ ጦሩ ሲደርስ አደጋ ይጥልበታል። በአደጋው 351ኛ እግረኛ ሻለቃ አብዛኛው ተደምሶ የሻለቃ አዛዡ ይሰዋ ይማረክ ሳይታወቅ ጠፍቶ ይቀራል። 30ኛ እግረኛ ሻለቃ ሌሊቱን በመዝናናት ቢያሳልፍም መደበኛ ጦር በመሆኑ ከፍተኛ ውጊያ ለማካሄድ አልሰነፈም። በመጨረሻም በሻለቃ (ብ/ጀ) የማታ የተመራው 11ኛ እግረኛ ሻለቃ

ቦታው ላይ ደርሶ 30ኛ ሻለቃን ከውጊያ ሊያላትቀው ችሏል። በዚህ የሻዕቢያ ደፈጣ ጥቃት የ30ኛ ሻለቃ አዛዥ በዕኩ በመቁሰሉ ለከፍተኛ ሕክምና ወደ አስመራ ተልኳል።

ከ30ኛና ከ351ኛ ሻለቆች መጎዳት በኋላ የአስመራ ምፅዋ ብቸኛው መንገድ ተዘጋ። ወዲያው አፋጣኝ እርምጃ ባለመወሰዱ ሻዕቢያ አካባቢው ላይ ጠንካራ ምሽግ በመቆፈርና ከፍተኛ ጦር በማከማቸት ተደላደለ። ይሄ የአስመራ ምፅዋ መንገድ ጠመዝማዛና፣ በተራሮች መካከል የሚያልፍ መሿለኪያ የበዛበት በመሆኑ አስጊና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሆኑ እርግጥ ነው። በዚህ መንገድ ላይ ድርጅቶችን ለማጀብ የሚንቀሳቀሱት ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ሁለት ሻለቆች ብቻ ነበሩ። እነሱም 31ኛ እግረኛ ሻለቃና 205 ነበልባል ሻለቃ ነበሩ። እነዚህ ሻለቆች በተደጋጋሚ ድርጅቶችን ከምፅዋ አስመራ ሲያጅቡ የቆዩ በመሆናቸው እረፍት እንዲያደርጉ ተወስኖ በ11ኛ ሻለቃ የተጠናከረው 351 እግረኛ ሻለቃ 30ኛ ሻለቃን አጠናክሮ እንዲመለስ ታዘዘ። ልምዱ ያላቸው 31ኛ እግረኛ ሻለቃና 205ኛ ነበልባል ቢላኩ ኖሮ የአስመራ ምፅዋ መንገድ ባልተዘጋ ነበር።

ከሻዕቢያ የደፈጣ ጥቃት በኋላ ከመጠናከሩ በፊት ዕዙ አፋጣኝ እርምጃ ቢወሰድ ኖሮ ወዲያው ማስከፈት ይቻል ነበር። ያ ሳይሆን በመቅረቱ ከደንጎሎ ምሥራቅ በገሃቴላይ ተራሮች ላይ እንዲሁም ከዶጉአሌ ምዕራብ ሲል በማይአጣል ቁልፍ መሬቶች ላይ ሻዕቢያ ለመጠናከር እድል አገኘ። ከአስመራ እና ምፅዋ የሚመጣውን የወገን ጦር ለመመከት የሚያስችል ምሽግ ሰርቶ ኃይሉን አጠናክሮ ለመጠባበቅ ጊዜ አገኘ። በዚህም ብዙ ችግር ተፈጠረ። የየብስ የድርጅት አቅርቦቱ ሙሉ በሙሉ የተቋረጠው ምፅዋ ወደብ ላይ ከፍተኛ ክምችት እያለ ነው። ከአሰብ በመርከብ መጥቶ ወደቡ ላይ የተራገፈው ክምችት በአውሮፕላን ተጓጉዞ የማያልቅ ከመሆኑም በላይ አውሮፕላኖቹ ጥቂቶችና የማንሳት አቅማቸውም ውስን ነበር።

በዚህም የአስመራ ምፅዋን መንገድ ባለው ኃይል ሁሉ ተጠቅሞ መክፈት የግድ ሆኖ ተገኘ። በዚህም 205 ነበልባል ሻለቃ በአውሮፕላን ወደ ምፅዋ ተጓጉዞ 11ኛ እግረኛ ሻለቃን እንዲያጠናክር ተደረገ። በሁለት አቅጣጫ በማጥቃት መንገዱን የመክፈት ዕቅድ ይነደፋል። አንዱ በምፅዋ አቅጣጫ ወደ ደንጎሎ፣ ሌላው ደግሞ በደንጎሎ ወደ ምፅዋ አቅጣጫ በማጥቃት በሁለት በኩል መንገዱን ለማስከፈት ነው። ለሁለቱም አቅጣጫ አዝማች መሪዎችና አንድ አስተባባሪ ተመደበ።

ከደንጉሉ ወደ ምፅዋ የሚያጠቃውን ጦር የሚመራው ሌ/ኮ (በኋላ ብ/ጄ) ገብረአብ ወልዳይ ሲሆን ከምፅዋ ወደ ደንጎሉ የሚያጠቃውን ጦር የሚመራው ደግሞ ሌ/ኮ አስናቀ ወ/ኪዳን ሆነ። የሁለቱን አቅጣጫ ጦር እንዳስተባብር እኔ ተመደብኩ።

የአስመራ ምፅዋውን መንገድ ለማስከፈት የተካሄደውን ዘመቻ ሻምበል ተስፋዱ ርስቱ "ምስክርነት" በተሰኘ መፅሐፋቸው ላይ ጠቅሰውታል። በገፅ 307 እና 308 ላይ እንደጠቆሙት ብ/ጄ ለሜሳ በዳሌ የአስመራ ምፅዋን መንገድ ለማስከፈት አልታዘዙም። ብ/ጄ ለሜሳ በወቅቱ የኤርትራ ፖሊስ ዋና አዛዥ ነበሩ። ከላይ ለመግለፅ እንደ ሞክርኩት የሁለቱ አቅጣጫዎች አስተባባሪ እኔ ኮ/ል አስጢፋኖስ ገ/መስቀል ነበርኩ። ሻምበል ተስፋዱ በመጽሐፋቸው ላይ እንደጠቀሱት ሻለቃ ጌታቸው መንግስቴ ደንጉሉ ላይ የብ/ጄ ለሜሳ ዘመቻ መኮንን አልነበረም። ሻለቃው የእኔ አስተዳደር መኮንን ነበር። ውጊያው ከመጀመሩ በፊት ሻለቃ ጌታቸው በመታመሙ ምክንያት ወደ አስመራ ተመልሷል። ከዚህ በተጨማሪ ሻምበሉ በመፅሐፋቸው ላይ እንደጠቀሱት በምፅዋ ግንባር ኮ/ል ወይም ብ/ጄ ሙሉጌታ የሚባል ሰው አልነበረም። የኔ ዘመቻ መኮንኖች ሻም (ብ/ጄ) እርቅይሁን ባይሳ፣ ሻም (ኮ/ል) ካሣ እና ሻም (ኮ/ል) ጌታሁን ዕርቁ ነበሩ።

***

የዘመቻው ዕቅድ የወጣው በወቅቱ የጦር ኃይሉች ኤታማዦር ሹም በብ/ጄ (ሜ/ጄ) ኃይለጊዮርጊስ ሀ/ማርያም፣ በኮ/ል (ሜ/ጄ) መርዕድ ንጉሴ፣ በኮል አይተነው በላይ እና በእኔ በሌ/ኮ (ኮ/ል) አስጢፋኖስ ገብረመስቀል ሲሆን ከምድር ጦር የውጭ አማካሪዎችም ነበሩበት። ብዙ ምክክርና ክርክር ከተደረገ በኋላ ዕቅዱ ፀደቀ።

የአጥቂው ጦር አመዳደብ

በምፅዋ ግንባር

- 205ኛ ነበልባል ሻለቃ - 230 የሰው ኃይል ይዞ
- 207ኛ ነበልባል ሻለቃ - ያልተሟላ
- ከ34ኛ ሻለቃ ከ1 ሻምበል የማይበልጥ
- አንድ ባትሪ በደቡብ የመናኛ የሚተኮስ 122 ሚ.ሜ መድፍ
- 72ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ በሻለቃ ተሰፋጊዮርጊስ የሚመራ
- አንድ መኪና ቢ.ኤም. 21 መድፍ (40 መድፍ የጫነ) በኤሌክትሮኒክስ የሚተኮስ። ምፅዋ ላይ ሆኖ ለሁለቱም ግንባሮች

በደንጎሉ ግንባር

- አንድ 122 ሚ.ሜትር ባትሪ መድፍ በደቡብ የመን ጎዶች የሚተኮስ
- 12ኛ ብርጌድ
- 2 ሚሊሽያ ሻለቆች
- 1 ታንክ ሻምበል በየመን ታንከኞች የሚተኮስ
- 1 ባትሪ 122 ሚ.ሜ መድፍ ሲሆኑ፣ 2ኛው አየር መደብ ለሁለቱም ግንባሮች በታቀደ ቅድመ-ማጥቃትና በጥያቄ የአየር ድብደባ እንደሚያደርግ ተወሰነ።

ለምፅዋ ወደብ ጥበቃ

- በሌ/ኮ (ብ/ጄ) ዓለማየሁ ወልድ የሚመራ 274 ሚሊሻ ብርጌድ
- 11ኛ እግረኛ ሻለቃ
- አንድ የአባት ጦር ሻለቃ (ያልተሟላ)
- ከ36ኛ ሻለቃ - 1 ሻምበል የማይሞላ
- የባህር ኃይል የኢትዮጵያ መርከብ፣ ተዋጊ ጀልባዎችና ቁጥራቸው ያልታወቀ፣ የባህር ኃይል አባሎች።

በሕዳር 12 ቀን 1970 ዓ.ም በሁለቱም በደንጎሉና በምፅዋ አቅጣጫ ማጥቃቱን ቀጠለ። በምፅዋ በኩል የተነሳው ለግቡ ቅርብ ስለነበር ቀድሞ ግቡ ላይ ደረሰ። በሻለቃ (ኮ/ል) በቀለ ገቢ የሚመራው 205ኛ ነበልባል ሻለቃ የጠላትን ግንባር ሰብሮ ሲገባ ሌሎቹ ከጎኑ የተሰለፉት በተለያየ ምክንያት ሰብረው ሊገቡ ሳይችሉ ቀሩ። በመሆኑም 205ኛ ነበልባል ሻለቃ በጠላት ተከብቦ ጉዳት ደረሰበት። ሻለቃ አዛዡ በህይወት ካሉት አባሎች ጋር እየተታኮሰ ሰብሮ ለመውጣት ቻለ።

ከደንጎሉ አቅጣጫ የተነሳው ጦር በየመን ታንከኞች ቀደም ብሎ ከማጥቂያ መነሻው ባለመድረሱና በመዘግየቱ የመጀመሪያው ቀን ውጊያ በህብረት ሳይከናወን ቀረ። ሻዕቢያዎች ለየብቻ ስላገኙዋቸው በጦሩ ላይ መጠነኛ ጉዳት ደረሰ። በተለይ ለሁለቱም ግንባር ለሚሊሻው የተመደቡት መሪዎች አንዳንድ የመቶ አለቆችና ልምድ የሌላቸውም ነበሩ።

እነዚህ ጉዳቶችና ክፍተቶች እያሉ ለአሥር ቀን መዋጋት ቢቻልም መስመሩን መስበር አዳግቶ ነበር። ከመሬቱ መጥፎነት የተነሣ ሻዕቢያዎችን ለረጅም ጊዜ ካዘጋጁት ምሽግ ማስወጣት አልተቻለም ነበር። በዚህ ላይ መጥፎ የአየር ሁኔታው በተለይ ለሚያጠቃ ጦር እንደ ጠላት ሆኖ የሚጋፈጠው ነው። ከፍተኛ የአየር ድብደባና የቢ.ኤም. 21 መድፍ እሩምታ ቢያወርድባቸውም ሊገኙ ችልቻሉም።

አየር ኃይልም ባወጣው የጦር ዕቅድ መሠረት የተመረጡ ቦታዎችን ይደበድብ ነበር። ዘግይቶ የሚፈነዳ ቦምብ ስለነበረው ከአየር ከተጣለ በኋላ የአውሮፕላኑን መሄድ ያዩ የሻዕቢያ ተዋጊዎች ሲወጡ እየፈነዳ ብዙ ጉዳት አደረሰባቸው። በዚህ ሁኔታ ተደጋጋሚ ጉዳት ከደረሰባቸው በኋላ ግን ጥንቃቄ ማድረግ ጀመሩ። እጃቸውን የሰጡ ሲናገሩም በስውር የሚበር አውሮፕላን የሚጥልባቸው ይመስላቸው ነበር።

በሁለቱም አቅጣጫ የተሰለፉት የሚሊሺያ ጦሮች ይበዙ ነበር። መሪዎቻቸውም አነስተኛና ልምድ የሌሉዋቸው ነበሩ አንዳንድ ጊዜ ሚሊሺያዎቹ በቆራጥነትና በድፍረት ገፍተው የያዙትን ገዢ መሬት ባለማወቅ ጥለው የሚመለሱበት ጊዜ ነበር። ምክንያቱም መሪያቸው ሲሞት ማን ተክቶ ውጊያውን እንደሚመራ የትዕዛዝ ሰንሰለት ህጉን ባለማወቃቸው የአዛዦቸውን እራሣ ላለማስማረክ ተሸክመው እያስቀሱ ወደኋላ ይመለሳሉ። ሁኔታው ከአፄ ዮሐንስ የመጨረሻ ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ነው። አፄው መተማ ላይ ጠላትን ድል ከመቱ በኋላ በመቁሰላቸው ጦሩ ድል የተመታ መስሎት መሸሽ እንደጀመረው ማለት ነው።

ከሚሊሺያዎች መመለስ በላይ ትልቅ ጥፋት የሰሩት በወቅቱ የነበሩት አማካሪዎቻችን ናቸው። የሚሊሽያው ጦር ቦታውን ለቆ ከመጣ በኋላ እንደ ደንቡ መልሶ ሳይቋቋምና ቅስቀሳ ተደርጎለት አዛዥ ሳይመደብለት በፍጥነት እንዲመለስና እንዲዋጋ ግፊት ያደርጉ ነበር። ይሄ ትክክል እንዳልሆነ ሲነገራቸውም ምራቃቸውን በአስተባባሪዎች ፊት ላይ እየተፉ ይሄዱ ነበር። በዚህ ድርጊታቸው የአንዳንድ አዛዦች ሞራል ከመነካቱም በላይ አማካሪዎችን ለመረሽን የሞከሩም ነበሩ። ሆኖም የአገር ጉዳይ ይቅደም በሚል ታግሰው ከከባድ ስህተት ተርፈዋል። እንዲህ ያለውን የድፍረት ድርጊት እኔም ደርሶብኝ በትዕግስት አሳልፌዋለሁ።

በእንዲህ ያለ ሁኔታ ብዙ ሙከራ ቢደረግም የአስመራ ምዕዋን መንገድ የማስከፈት ዕቅዱ ላይሳካ ይቀራል። የሰሜኑ ዕዝ አዛዥ ኮ/ል (ሜ/ጀ) መርዕድ ንጉሴና የሁለቱ ግንባር አስተባባሪ እኔ ሌ/ኮ እስጢፋኖስ ገ/መስቀል በመመካከር በዚህ ሁኔታ መቀጠሉ ሰውን ከማስጨረስ ውጭ ፋይዳ እንደሌለው መስማማት ላይ ደረስን። ዳግም ማጥቃቱ ሌላ ጥናት ተደርጎ ቢቀጥል ይሻላል የሚል ሐሳብ ቀረበ። ሀሳቡም በበላይ አካል ታምኖበት ተቀባይነት አገኘ።

የምፅዋ ሰጣ ፈንታ

በአዲስ መንፈስ ውጊያውን ለመቀጠል ዕቅድ ወጣ። 8ኛ ብርጌድ ከባሬንቱ ወደ ምዕዋ እንዲንቀሳቀስ ትዕዛዝ ተላለፈለት። 8ኛ ብርጌድም በሁለት ብርጌዶች ይጠበቅ የነበረውን ባሬንቱን ለጀግናው 16ኛ ብርጌድ፣ ለኤርትራ ፈጥሮ ደራሽና ለኩናማ ሕዝባዊ ሠራዊት ብቻ ትቶ በዕቅድና በትዕዛዙ መሠረት ተንቀሳቅሶ ምዕዋ ገባ። 8ኛ ብርጌድ ምዕዋ በገባበት ወቅት ከሩሲያ በባህር ላይ መቅዘፍና መንሳፈፍ የሚችሉ ታንኮች ተገዝተው እኩል ደረሱ።

በእቅዱ መሠረት ከልምምድ አስቀድሞ አጠቃላይ ውይይት ለማድረግ ታንኮቹ ያሉበት ምዕዋ ላይ ተቀመጥን። ሩሲያዊዎቹ አማካሪዎቻችንና እኛ የጦር ዕቅድ ላይ ሙሉ ስምምነት ላይ ደረስን። የታንኮቹ አሰላለፍ ጉዳይ ላይ ግን ተወያዮቹን ለሁለት እኩል ሰንጥቆ አፋጠጠን። የዕዙ አዛዥ ኮ/ል (ሜ/ጀ) መርዕድ ንጉሴና የሁለቱ ግንባር አስተባባሪ የሆንኩት እኔ ሌ/ኮ እስጢፋኖስ ገ/መስቀል በአንድ ወገን ሆነን ከተቀሩት አማካሪዎቻችን ጋር ያልተስማማንበትን የታንክ አሰላለፍ እቅድ አቀረብን። አማካሪዎቻችን የሚሉት እግረኛና ታንከኛ በተለያየ አቅጣጫ ወደ ግባቸው ተነጣጥለው ይሂዱ ነው። ይሄንን እኛ ተቃውምን። ምክንያታችን ደግሞ

1ኛ/ እግረኛው በአንድ አቅጣጫ ታንኩ ለብቻው በሌላ በኩል ለአንድ ግብ ሲላኩ ፍጥነታቸው እኩል አይሆንም። ታንኩ ቀድሞ ስለሚደርስ በጠላት ሊጠቃ ይችላል። ስለዚህ እግረኛው በታንክ እየተረዳ ቢያጠቃ ይሻላል።

2ኛ/ ታንኩ በአሰራሩ ከፊት ለፊትና ከቱሬቱው በስተቀር ሌላ መመልከቻ ስለሌለው በእግረኛ ካልታጀበ ለጥቃት የተመቸ ነው። ታንኩ የሚንቀሳቀስበት አካባቢ በቁጥቋጦ የተሸፈነ በመሆኑ ለደፈጣ ውጊያ የተጋለጠ ይሆናል። ስለዚህ ለእግረኛው ድጋፍ እየሰጠ አብሮ ቢያጠቃ ይሻላል።

3ኛ/ እንደ አጋዴን ወይም ምዕራባዊ ቆላ ያሉት ሜዳማ ቦታዎች ላይ ታንክ ለታንክ የሚደረግ ውጊያ ካልሆነ በስተቀር ታንክ ብቻውን

እግረኛን ለማጥቃት ውጤት አይኖረውም። ታንክ የጠላት ሽምቅ ተዋጊ ያለበትን በትክክል ለማየት ሳይችልና ሳያውቅ፣ በዚህ ላይ ከጐኑ የሚጠብቀው እግረኛ ሳይኖረው ለመዋጋት ይቸገራል አልን።

በዚህ በእኔና በኮ/ል መርዕድ ንጉሴ ሐሳብ አማካሪዎቻችን ተናደዱ፣ ጠፉ። "ስለ ታንኮቻችን ችሎታ የምናውቀው እኛ እንጂ እናንተ አይደላችሁም!" በሚል ከድንፋታ ጋር ተናገሩ። እኛም አልተበገርንም። በታንክ አሰላለፉ ላይ ሳናምንበት ጦሩን ለግዳጅ ማሰማራት በህይወት ላይ እንደመፍረድ ስለቆጠርነው አምርረን ተከራከርን። በዚህ መካከል የጦር ኃይሎች ኤታማጆር ሹሙ (በኋላ የአገር መከላከያ ሚኒስቴር) ሜ/ጀ ኃይለጊዮርጊስ ሀ/ማሪያም ክርክራችን መካከል ጣልቃ ገቡ። የሜ/ጄኔራሉ ውሳኔ ለአማካሪዎቻችን ያደላ ሆነ። የጉዳዩ ስህተትና አደገኝነት ጠፍቷቸው ሳይሆን ሳያምኑበት አማካሪዎቻችን ላይ ቅሬታ እንዳያድር አቋሙን የያዙ ይመስላል። እናም "በእነሱ ሐሳብ መሠረት ፈፅሙ" ሲሉ ወሰኑ። ብዙውን ጊዜ በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ያሉ ቁንጮ ካድሬዎች አማካሪዎቻችንን እንዳናስቀይም ይነግሩናል። በአማካሪዎቻችን ሐሳብ መሠረትም በምዕዋና በዶገአሌ መካከል ልምምድ ተደረገ።

ዕቅዳችንና ክርክራችን የታጠፈብን ወገኖች አንድ ነገር ግልፅ ሆኖ ታይቶናል። እሱም የጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ውሳኔ አማካሪዎቻችንን ለማስደሰት የተሰነዘረ፣ ነገር ግን በወገን ጦር ላይ የሞት ፍርድ ጠባይ ያለው መሆኑ ገብቶናል። ምንም ማድረግ ስላልቻልን ሕዳር 26/1970 ዓ.ም በዕቅዱ መሠረት ልምምዱ ተጠናቀቀ። ማታውኑ ጦሩ ከሻዕቢያ ጋር ተፋጥጦ በማደር ለጦርነት ተዘጋጀ። በዚህ መካከል ግን በጀግናው 8ኛ ብርጌድ አንድ ጥያቄ ቀረበ። ብርጌዱ ኤርትራ ውስጥ የቆየ በመሆኑ አደገኛ ቦታዎችን ሁሉ እንደ እጅ መዳፉ ጥርት አድርጎ ያውቃቸዋል። ከዶገአሌ ወደ አስመራ ሲል በስተቀኝ አንድ አደገኛ ኮረብታ አለች። ብርጌዱ የጠየቀው ይቺ አደገኛ ኮረብታ በወገን ጦር መያዝና አለመያዟን ለማረጋገጥ ነበር። ካልተያዘች አስሰን በማዕዳት እንለፍ የሚል መፍትሔ በተደጋጋሚ ከብርጌዱ ቀርቧል። የሻለቃ ማዕረግ ያለው የምፅዋ አካባቢ ጦር የዘመቻ መኮንኑ "በእኔ ይሁንባችሁ በኛ ጦር ተይዟል" የሚል ምላሽ ይሰጣል። የዘመቻ መኮንኑ ኮረብታዋ እንድትያዝ ለአንድ ጦር ትዕዛዝ ቢሰጥም እርግጠኛ ሆኖ መያዝና አለመያዟን አላረጋገጠም ነበር።

ሕዳር 28 ቀን 8ኛ እግረኛ ብርጌድና ታንኮቹ በሁለት አቅጣጫ ማጥቃት ሰነዘሩ። በምፅዋ አቅጣጫ ያሉት ታንኮቹ በሻለቃ በሻህ መሪነት

3. ከሴት ጋር ስንጫወት መደበኛ ጦር ከመጣ ሴቶቹን "የሱን ደሞዝ (ሃያ ብር) እኔ እሰጥሻለሁ" እያለ ይሳለቅብናል።
4. መደበኛው ጦር በበዓል ቀን ከብት አርዶ በመብላትና በመጠጣት በአሉን ሲያከብር እኛ በገንዘብ አቅም ምክንያት ይሄን ልናደርግ አልቻልንም። በዓሉን ሌላው ሲበላ እኛ በማሽተት እናከብራለን።

ከላይ የተገለፁትንና ሌሎቹንም ብሶቶቻቸውን በዚያው በመፈክራቸው እያጀቡ አሰምተው ጨረሱ። በመጨረሻም "በሦስት ቀን ውስጥ ምግባችንና ደሞዛችን ይሻሻልልን" አሉ። "ሁላችንም የምንቆስለውና የምንሞተው ለአንድ አላማ ስለሆነ በሦስት ቀን ውስጥ መልስ እንፈልጋለን"[17] በሚል ጠንከር ያለ አቋም ያዙ። እኛም መልሳችንን አሳወቅን።

"ጥያቄው የእናንተ ብቻ ሳይሆን የመላው የኢትዮጵያ ሚሊሺያ ነው። ስለዚህ እኛ እንዲህ ነው፣ እንዲህ ይደረጋል ብለን ቃል ገብተንላችሁ አንሄድም። ጥያቄው በብሔራዊ መንግስት ተጠንቶ መልስ የሚሰጥበት ነው" አልን።

የኛን ምላሽ በማየት ሚሊሽያው የአቋም መሳላት አሳየ። ሦስት ቀን ያሉትን 15 ቀን፣ ከዚያም አንድ ወር፣ በኋላም ሦስት ወር ብለው አራዘሙ። እዚያ ላይ የኛ አቋም ቀናትን በመቁረጥ ከኛ እጅ እንደሚወጣ አድርገን በሆነ ውሳኔ ላይ መደራደሩ አልታየንም።

"በዚህ ቀን ይፈፀምላችኋል ብለን አጉል ተስፋ በመስጠትም ልንዋሻችሁ አንሽም። ጉዳዩ በኛ አቅም የሚፈፀም ባለመሆኑና በኢትዮጵያ ያለ ሚሊሽያ ሁሉ ጥያቄ ስለሆነ የሚጠናውና የሚፈቀደው በማዕከላዊው መንግሥት በኩል ነው። ቶሎ ሊሳካ ወይም ላይሳካ ይችላል" ብለን አስረዳን።

"እና እናንተ ምን ልታደርጉልን ትችላላችሁ?" የሚልሺያመቹ ቀጣይ ጥያቄ ነበር።

"በእኛ በኩል ሁኔታውን በቅርበት አይተን የተረዳን ስለሆነ አስቸኳይነቱን በመግለፅ በአፋጣኝ መልስ እንዲሰጥ ሪፖርት እናቀርባለን" አልን።

---

[17] በዚህን ጊዜ ከመካከላቸው ሃምሳ አለቃ ሆኖ ከሚልሽያነት ወደ መደበኛው ሰራዊት የተዛወረው ጓደኛቸው የሆነ ካድሬ መልስ ለመስጠት፣ ሲምክር አንተ ዝም በል የዲያሌክቲክስ ሕግ ዕድገቱን ያሳየው ባንቱ ላይ ነው ብሰው እንዳይናገር ከለከሉት

ጦሩ ከብዙ ክርክር በኋላ ሃሳባችንን ተቀብሎ ካሰበው መጥፎ ድርጊት ታግሶ መልሱን መጠበቅ ጀመረ።

ከብርጌዱ ጋር በተነጋገርንበት ዕለት ብዙ ጥያቄ ያቀርቡ የነበሩ 5 እና 6 የሚሆኑ ወጣቶች ማታውኑ ጠፍተው ከሻዕቢያ ጋር ተደባለቁ። በዚህ ሁኔታ ውስጡን የሚያውቁ የሻዕቢያ ወኪሎች ቀስቅሰው ሚልሺያውን እንዳነሳሱት ጠርጥረናል።

ማዕከላዊው መንግሥት የቀረበለትን ሪፖርት መሠረት በማድረግ የሚልሺያው ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑን እና የሚያስከትለውን ችግር በመረዳት ሚልሺያው በደሞዝም ሆነ በምግብ ከመደበኛው ጦር ጋር እንዲስተካከል ወሰነ። ውሳኔው ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በመድረሱ አፋጣኝ ምላሽ ነበር ለማለት ይቻላል። በዚህም በሚልሺያውና መደበኛው ጦር መካከል ሊከሰት ይችል የነበረው መጥፎ አዝማሚያ ተቀረፈ። በመልሱም በኢትዮጵያ የሚገኘው ሚልሺያ ሁሉ ተጠቃሚ ሆነ።

የናቅፋ ውጊያ ማገርሸትና የ508 ግብረ ኃይል ማቋቋም

በኤርትራ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ሻዕቢያ ማጥቃት የሚሰነዝርባቸው ወራት የታወቁ ናቸው። ከጥቅምት እስከ የካቲት ባሉት 5 ወራት ውስጥ ነው። ወራቶቹ በኤርትራ ደጋማው ክፍል ጉም መሸፈን የሚጀምርበት፣ የባህሩ አካባቢና ቆላው የሚቀዘቅዝበት በመሆኑ ነው ለሻዕቢያ ማጥቃት የተመቸው። ናቅፋም ወይራ የሚበቅልባት ወይናደጋነት የሚሰማት አካባቢ ናት።

ናቅፋ ላይ ሻዕቢያና 508 ግብረ ሃይል ለአንድ አመት ያህል ተኩስ ሳይለዋወጡ ቆይተዋል። በዚህ ይመስላል የወንን ጦር አደራጅቶ የሠራውን ምሽጉን እንደቤቱ መቁጠር ጀምሯል። መሣሪያውን ከአጠገቡ ለይቶ፣ ጫማውን አውልቆ ሌሊቱን ዘና ብሎ ያሳልፋል። እንዲያነቃው ከምሽጉ ፊት ለፊት ያጠመደውን ፈንጂ ባለመጠበቁ ሻዕቢያ ሌሊት ፈንጂዎቹን በማውጣት በራሱ መከላከያ ፊት አጥምዷቸዋል። ከጦሩ ፊት ለፊት የሚወጡ አድማጭና አንቂ ሰላዮችም እንዲወጡ ሳይደረግ

በመቆየቱ፣ ከወጡም ነቅተው ባለመጠበቃቸው በዚህ ረጅም ጊዜ ውስጥ ሻዕቢያ የራሱን መሠናዶ ሲያደርግ አልታወቀም።

ሻዕቢያ የራሱን ዝግጅት አድርጎ የማጥቃት ዕቅዱን ካጠናቀቀ በኋላ በህዳር ወር ሌሊት ማጥቃት ጀመረ። ማጥቃቱ ያልተጠበቀና ድንገተኛ በመሆኑ ጥቂት የጦሩ አባሎች በጨለማ መሣሪያቸውንና ጫማቸውን በመተው ከምሽጋቸው ወጥተው ማፈግፈግ ይጀምራሉ። ጥንቁቆቹም ሻዕቢያ ሰብሮ ከገባ በኋላ በጉን በኩል አልፎ ከኋላቸው ማጥቃት ስለጀመረ ሁሉም ከምሽጋቸው ውጭ መዋጋት ያዙ። ሁኔታው ለሻዕቢያ በማድላቱም የክፍለ ጦሮቹና የግብረ ኃይል ጠቅላይ ሠፈሮች ለሻዕቢያ መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ማፈራረስና ይዘው ሊንቀሳቀሱ የማይችሉትን የጽሑፍ መረጃዎችን፣ ጥይቶች በማቃጠል ማፈግፈግ ጀመሩ። ጦሩ ከምሽግ ውጭ ሆኖ ለረጅም ጊዜ ለመከላከል ቢሞክርም አዳገተው። በመሆኑም ብቸኛ አማራጩ እየተዋጋ ማፈግፈግ ሆነ።

እኔ የ506 ግብረ ኃይል አዛዥ ነበርኩ። የብሔራዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው ም/ኃላፊ ሜ/ጄ ኃይለጊዮርጊስ ሀ/ማሪያም ወደ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው አስጠሩኝና "በክ/ል (ሜ/ጄ) አስራት ብሩ የሚመራው የ508 ግብረ ኃይል ከሻዕቢያ በተሰነዘረበት ድንገተኛ ማጥቃት ከምሽጉ ወጥተው እየተከላከለ ነው። ምናልባት ያፈገፈገ እንደሆነ አንተ ወደ ኩበኩብ በአስቸኳይ ሄደህ ለሁለት ክፍለ ጦር የሚሆን ምሽግ አስቆፍር። 508 ግብረ ኃይልም ከኩበኩብ እንዳያልፍ አድርግ" የሚል መመሪያ ሰጡኝ።

በመደናገጥና በመገረም ፈዝዤ ቀረሁ። ጀኔራሉ ያዘዙኝ እውነትም አልመሰለኝ። ሳምን አልቻልኩም። ሁኔታዬን የተረዱት ጀኔራሉ ደጋግመው ትዕዛዝ በመስጠት እውነቱን አረጋገጡልኝ። የጦር ሜዳ ላይ ትዕዛዝ እንቢታ የለበትምና ትዕዛዙን ተቀብዬ ወጣሁ።

"አካፋና ዶማውን አከታትዬ በሔሊኮፕተር እልክልሃለሁ" አሉኝ።

በአፋጣኝ ሄሊኮፕተር ጠይቄ ወደ አፍአበት አመራሁ። የ508 ግብረ ኃይል ከኋላ እንዳይቋረጥና የድርጅት ማቀቢያው መንገድ እንዳይዘጋ የ506 ግ/ሃይል አካል ለሆነው ለ31ኛ ብርጌድ ሁኔታውን አስረዳሁ። ከብርጌድ አዛዡ ከሌ/ኮ (ብ/ጄ) ኃይሉ ወ/ሐዋርያት በዚህ ጉዳይ ላይ ካወራን በኋላ ኩበኩብ መተላለፊያ የግራና ቀኝ ኮረብታዎች ላይ ያሉትን ሁለቱን ሻለቆች እንዲያነቃ ነገርኩት። የ508 ግብረ ኃይልን ሻዕቢያ ሰርጎ በመግባት ከኋላ እንዳያጠቃቸው ነቅተው እንዲጠብቁ ትዕዛዝና መመሪያ ሰጠሁ። ከዚያ እኔም ወደ ኩበኩብ ወንዝ ወረድኩ።

ዘመቻ መኮንኔ ሌ/ኮ (ብ/ጀ) ዘውዱ ታደሰ ከአራት አጃቢዎቼ ጋር መንቀሳቀሴን ግንባር ላለው ጦርህ አሳውቅ ብዬ ትዕዛዝ ሰጠሁ። ካሳወቅኳቸው በኋላም ተንቀሳቀስኩ።

ሜ/ጀ ኃይለጊዮርጊስ ሀ/ማሪያም በማግስቱ ቃላቸውን አክብረው በሄሊኮፕተር አካፋና ዶማውን ላኩ። እንኳን ምሽግ የሚቆፍር ዶማውን ከሄሊኮፕተር የሚያወርድ ሰው አልነበረም። ሌ/ኮ ዘውዱ ታደሰና አጃቢዎቻችን ብቻ ሆነን አካፋውን አወረድን። 31ኛ ብርጌድን ምሽግ ለማስቆፈር የሚቻል አልሆነም። ምክንያቱም የጥበቃ ኃላፊነቱ ይህን እንዲሠራ አይፈቅድለትም ነበር። አንድ ሻለቃ አፍአበትን፣ ሁለቱ ሻለቆች ደግሞ የ508 ግብረ ኃይልን ከኋላ እንዳይቆረጥና የድርጅት መቀበያ መስመሩን ሁለት ኮረብቶች ላይ ግራና ቀኝ ተከፍለው ይጠብቁ ነበር። ጦሩ ጥበቃውን ትቶ ምሽግ ይቆፍር ቢባል እንኳን ሁለት ሻለቆች ብቻ የአንድ ግብረ ኃይል የመከላከያ ወረዳ ለማዘጋጀት አይችሉም - ያውም በአጭር ጊዜ ውስጥ።

ምሽግ የማስቆፈሩ ግዳጅ ከጭንቀት የመነጨ አማራጭ የማጣት ትዕዛዝ እንደተሰጠኝ ገምቼና አምኜ ነበር። ሜ/ጀ ኃይለጊዮርጊስ ሀ/ማሪያም የውጊያ ስልት ጠንቅቀው ከሚያውቁ ጥቂት ጀኔራል መኮንኖቻችን አንዱ መሆናቸውን አውቃለሁ፤ አምናለሁም። ግን ትዕዛዛቸው ግራ የሚያጋባ ሆነብኝ። ለሁለት ቀን ያሰበቂ ጥበቃ ሳንሰባሰብ ፈንጠር ፈንጠር ብለን ነበር ኩብኩብ ላይ ያደርነው።

ጦሩ ከምሽጉ ውጪ ሆኖ በሚዋጋበት ጊዜ የዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው ከ506 ግብረኃይል ለ84ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ አንድ ግዳጅ ይሰጣል። ግዳጁ 508 ግብረ ኃይልን ማፈግፈግ እንዲረዳ ነበር። ይሄንን ጦር በአስቸኳይ ለማንቀሳቀስ ከኩብኩብ ወደከረን ተመልሼ ከዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው ጋር ተነጋገርኩ። ቢያንስ አንዱ ሻለቃ በሄሊኮፕተር እንዲንቀሳቀስ ጠይቄ ተፈቀደ። እንደታቀደው በሄሊኮፕተር ከሚያፈገፍገው ጦር አጠገብ በማረፍ ተጠቃሎ ገባ። ጀግናው የ84ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ አንድ ሻለቃ ብዙ ጀብዱ ፈፀመ። ጦሩ ሲያፈገፍግ አብሮት እንዲያፈገፍግ ያላደረገውን በሌ/ኮ (ኮ/ል) ረጋሳ በየነ የሚመራው አንድ ቢ.ኤም (የአጭር ርቀት ባሌስቲክ ሚሳኤል) ሻለቃ (12 መኪና እያንዳንዱ 40 መድፍ የያዘ) ተከቦ ሊማረክ በተቃረበበት ጊዜ ይህ ባለግዳጅ ሻለቃ በፍጥነት ተንቀሳቅሶ ይደርሳል። በሻዕቢያ ጦር ላይ ማጥቃት በመሰንዘር ተቃዋሚዎችን ማርኮና የሻለቃውን ጦር ከነከባድ መሣሪያው ከሚያፈገፍገው ጦር ጋር ይዞ ወደኋላ ተመልሷል።

ሁለቱ የዚህ ብርጌድ ሻለቆች ከከረን በተሸከርካሪ ሲመጡ በየመንገዱ የተቀበሩትን ፈንጂዎች እያወጡ ስለነበረ የደረሱት ዘግይተው ነበር። ጦሩ ማፈግፈጉን አልተረዱም። በኋላ ግን የግብረ ኃይሉን ይዞታ በማጠናከር ረድተዋል።

ኩብኩብ ላይ ጥበቃ ከሚያደርጉት ሻለቆች ውስጥ ጥቂቶቹ ፊት ለፊት ያለው ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች ላይ ሆነው የድርጅት ማቅረቢያ ሥስመሩን ጋ ጣብቁ ነበር። እነዚህ አባሎች የወገን ጦር እያፈገፈገ መሆኑን ተናገሩ። የታንክና የተሸከርካሪዎች ድምፅም ወደነሱ እየቀረበ መምጣቱን ገለፁልን።

508 ግብረ ኃይል ማፈግፈጉን ባፈጠነበት ጊዜ የግብረ ኃይሉን የድርጅት መሥመር ለመጠበቅ ከ31ኛ ብርጌድ አምባ ከሚባልና ሌሎች ቁልፍ ቦታዎችን የመከላከያ ይዘው የነበሩትም አባሎች አብረው በማፈግፈግ ከሻለቆቻቸው ጋር ተቀላቀሉ። ጦሩ ማፈግፈጉን እንደቀጠለ የቀዳሚ መምሪያው የዘመቻ መኮንን ኮ/ል ገብረክርስቶስ ቡሊ በሄሊኮፕተር ኩብኩብ ድረስ መጡ። አመጣጣቸው ለእኔ ትዕዛዝ ለመስጠት ነበር። "ጦሩ ኩብኩብ እንዳያልፍ!" የሚል ነበር ትዕዛዛቸው። ይሄ ትዕዛዝ የሚመለከተው 508 ግብረ ኃይል አዛዥ ኮ/ል አሥራት ብሩን ነበር። ይህ ግብረ ኃይል ክፍሌ ስላልሆነ እኔ ማዘዝ አልችልምና ነው።

የ508 ግብረ ሃይል ከምሽጉ ውጪ እንቅልፉን አጥቶ ያለእረፍት ሲዋጋ ከቆየ በኋላ ኩብኩብ ላይ በተበታተነ መልኩ ደረሰ። ኩብኩብን ለማለፍ በሚሞክርበት ጊዜ እኔና ሌ/ኮ (ብ/ጀ) ዘውዱ ታደሰ ሁኔታውን በማስረዳትና በማግባባት እንዲቆም ጣርን። ውሃና ምግብ ኩብኩብ ላይ እንደተዘጋጀላቸው፣ ቁስለኞችም በሄሊኮፕተር እንደሚገለሉ፣ በማስረዳት ጥረት አደረግን። ከብዙ ድካም በኋላ ለማስቆም ተቻለ። ቁስለኞችም በሄሌኮፕተር ሞተነሱ። የተዘጋጀውም ውሃ ቀረበላቸው ምግብ ግን የራሳቸው ስለነበራቸው አልጠየቁንም።

የ508 ግብረ ሃይል ተካቶ ኩብኩብ ላይ እንደገባ ሲቋረጥ የተወሰነ ጦርና ታንኮችን ከፊታቸው ጥሩ የተኩስ ዕይታ ሊኖራቸው በሚችልበት በኩብኩብ ወንዝ ዳር የመከላከያ ቦታ አስያዝኑ። "ከእንግዲህ ወዲህ የሚመጡትን የይለፍ ቃል እየጠየቃችሁ ማንነታቸውን አረጋግጣችሁ አሳልፉ። ማንም በቀጥታ እንዳያልፍ" ብዬ ለአንድ ትግሪኛ ተናጋሪ የፖለቲካ ካድሬና ለሌላ አንድ መኮንን መመሪያና ትዕዛዝ ሰጠሁ።

ልክ እንደተጠራጠርኩት ለ2 ሰዓት ያህል የማፈግፈጉ ሁኔታ እንደተቋረጠ መስዋዕትነት ከከፈሉት የወገን ጦር አስከሬን ላይ ልብስ እየገፋፉ ለብሰው ተመሳስለው ተቃረቡ። ማንነታቸውን እንዲገልፁ ሲጠየቁ "እንተ ማንነትህን ግለፅ" ይላሉ። ይሄ በተከላተፈ አማርኛ የተሰጠ መልስ ጥርጣሬ አጫረ። ተመሳስሎ የመጣው ጦር ጠመንጃውን ሲያዞር መከላከያ ቦታ ይዞ የነበረው የወገን ጦር ይረፈርፋቸዋል። በዚህ አጋጣሚ ተዋጊ አውሮፕላኖች በመምጣታቸው ይደበደቡ ጀመር። ከእኔ ጋር በነበረ አንድ የ508 ግብረ ኃይል የአየር ተኩስ መሪ መኮንን አማካኝነት ድብደባው ተጠናክሮ ቀጠለ።

ተዋጊዎቹ አውሮፕላኖቹ በአየር ላይ እንዳሉ ከፍተኛ የጠላትን እንቅስቃሴ በማየታቸው እዛው አየር ላይ እያሉ ሌሎችንም ተዋጊ አውሮፕላኖች በመጥራት ለሁለት ቀን ያህል አከታታለው ከፍተኛ የአየር ድብደባ በማድረጋቸው ሻዕቢያዎች በመጎዳታቸው ማጥቃታቸውን አቆሙ።

በወቅቱ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ አያጠራጥርም። ነገር ግን ከከፍሌ ውጭ በመሆኑ 508 ግብረ ኃይል ለማዘዝ ያዳግተኛል። ይሁንና የ508 ግብረ ኃይል አዛዥ በቀረበላቸው ሄሊኮፕተር አልፈው አፍአበት የ506 ግብረ ኃይል አካል የሆነው የ31ኛ ብርጌድ ጠቅላይ ሠፈር በማረፋቸው ሁኔታውን መልክ ለማስያዝና ከባሰ ችግር ለመዳን የ508 ግብረ ኃይሉን የዘመቻ መኮንን ኮ/ል (ብ/ጀ) ውበቱ ፀጋዬን አስጠርቼ ተመካከርን። ቀጥሎም ሁለቱን የክፍለ ጦር አዛዦች ማለትም የ3ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ኮ/ል (ሚ/ጀ) አብዱላሂ ዑመርንና የ17ኛ ክፍለ ጦር አዛዥን ኮ/ል (ሚ/ጀ) ቁምላቸው ደጀኔን አስጠራሁ። ስብሰባ ካደረግን በኋላ ሁለቱ ክፍለ ጦሮች ወደ ናቅፋ ከመሄዳቸው በፊት የያዙትን የኩበኩብ ወንዝ መጋጠሚያ ግራና ቀኝ ላይ ይዘው እንዲቆዩና ይዞታቸውንም እንዲያጠናክሩ ተስማማን። በኋላ በዘመቻ መምሪያው ም/ኃላፊ በሚ/ጀ ኃይለ ጊዮርጊስ ሀ/ማርያም ስም 3ኛ ክፍለ ጦር ከኩበኩብ ወንዝ በስተግራ፣ 17ኛ ክፍለ ጦር ቀኙን ይዘው ፊት ለፊታቸው በሚገኙት ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች ላይ አዘግይና አንቂ ጦሮችን እንዲያስይዙ መመሪያና ትዕዛዝ በሰጠሁት መሠረት የመከላከያ መስመራቸውን ያዙ። አካፋና ዶማውንም እኩል አከፋፈልኳቸው።

ሦስቱም የ508 ግብረ ኃይል መኮንኖች ቀደም ሲል አብረን በመሥራታችን እናም ቀደምት (ሲኒየር) መኮንን መሆኔን ስለሚያውቁ እንጂ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ከእኔ ለመቀበል ግዴታ አልነበረባቸውም።

ለጋራ ዓላማ የምንሠራ መሆናችንን ተረድተው እንጂ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ መቀበል የነበረባቸው ከ508 ግብረ ኃይል አዛዥ ነበር።

ከዚህ በኋላ የ506 ግብረኃይል አካል የሆነውን 31ኛ ብርጌድ እና 84ኛ ብርጌድ ልዩ ትዕዛዝ እና መመሪያ እስኪደርሳቸው ድረስ በተደራቢነት አብረው እንዲሠሩ ትዕዛዝ ሰጠሁ። የ508 ግብረ ኃይል ያጋጠመውን ሁኔታ በወሬ አጋናኞች እየተጋነነ እንዳይሰማና ጦሩ እንዳይረበሽ የ506 ግብረ ኃይል የጥበቃ ኃላፊነቶች ወዳሉበት ቦታዎች እየተዟዟርኩ ለማስረዳት ወደከረን ከተማ ተመለስኩ። አላማዬ ሠራዊቱ መካከል ውዥንብር እንዳይፈጠር ለመከላከል ነበር።

የ506 ግብረ ኃይል የጦር ክፍሎች ባሉበት አውራጃዎች እየተዟዟርኩ 508 ግብረ ኃይል ያጋጠመውን ችግር ማስረዳት ጀመርኩ። በዚህ መካከል ነበር 508 ግብረ ኃይል እንደገና በደረሰበት ጥቃት ከኩብኩብ ይዞታውን ለቆ ማፈግፈግ የጀመረው። አሁንም እንደገና 508 በማፈግፈጉ ከብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ ም/ኃላፊ ከሚ/ጀ ኃይለጊዮርጊስ ሀ/ማሪያም የትዕዛዝ ቴሌግራም ይደርሰኛል። "እንደገና ወደ አፍአበት ተመልሰህ የ508 ግብረ ኃይልን የመልሶ መቋቋምና የመከላከያ ወረዳ ይዞታ እንድትረዳ" ይላል ትዕዛዙ።

የጀመርኩትን ማብራሪያ አቋርጬ የ508 ግብረ ኃይል አዛዥ ወዳሉበት ወደአፍአበት ተንቀሳቀስኩ። መድረሴን በቅድሚያ ለዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው፣ በኋላም ለ508 ግብረ ኃይል አዛዥ አሳወቅሁ። በተሰጠኝ ትዕዛዝ መሠረት የ508 ግብረ ሀይል መልሶ በሚቋቋምበት ጉዳይ ላይ ሰፊማክርና በመርዳት ቆየሁ። ከጓደኛዬ ይልቅ ቀደም ብዬ አካባቢውን ስለማውቀው ከኩበኩብ እስከ ቀምጨዋና መርሳ ጉልቡብ ከፍተኛና አነስተኛ ጀልባዎች ወደብ ድረስ ያለው የመከላከያ ቦታና ይዞታ በማጠናከር አዛዦን (የረጅም ጊዜ ጓደኛዬን) በመርዳቴ ለሀሊናዬ እርካታ ሰጥቶኛል። በመጨረሻ ሁሉም ነገር መልክ ከያዘ በኋላ የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ "ኃይለጊዮርጊስኮ የላክህ እኔን እንድታጫውት ነው" አለኝ። አያደርጉም አልልም።

ያደረግሁት አርዳታ ሁሉ ክንቱ ሆኖ አጫዋች በመሆኔ በጣም አሳዝኖኛል። እሳቸው ቢሉት እንኳን ይሄንን ሊነግረኝ አይገባም ነበር። የ508 ግብረ ኃይል በተደጋጋሚ በማፈግፈጉ ማዕከላዊው መንግስት ከፍተኛ ሥጋት ላይ የወደቀ ይመስለኛል። ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃ/ማሪያም በቅድሚያ ለ508 ግብረ ኃይል ጦር አስታታለውም ለሌሎቹ ግብረ ኃይሎች ማስፈራሪያ ያቀው መልዕክት አስተላለፉ። በቴፕ

ድምፃቸውን አስቀርፀው የላኩት መልዕክት ከዚህ በኋላ የትኛውም ጦር ቢያፈገፍግ የሚወሰዱት እርምጃ እንደሚከፋ ይገልፃል። በዛ ባሉ ወጣት ካድሬዎች አማካኝነት ወደተለያዩ የመከላከያ ወረዳዎች የደረሰው መልዕክት ለጦሩ ተደመጠ።

ጦሩ መረጋጋት ሲጀምር የዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው አዲስ መዋቅር አፀደቀ። አዲሱ መዋቅር ቀደም ሲል አፍርሶት የነበረውን "ሰሜን ዕዝ" ከነሥያሜው ዳግም አምጥቶ አቋቋመው።

ዳግም ሰሜን ዕዝ መቋቋም

የሰሜን ዕዝ እንደገና ሲቋቋም የአዛዦች ምደባ ተደረገ። ኮ/ል አሥራት ብሩ ብርጋዲየር ጄኔራል ተብለው የሰሜን ዕዝ አዛዥ ሆኑ። ኮ/ል (ሜ/ጀ) መስፍን ገብረቃል በኮሎኔልነት ማዕረግ እንዳሉ የሰሜን ዕዝ ም/አዛዥና ኤታማዦር ሹም ሆነው ተሾሙ። ኮ/ል (ሜ/ጀ) ቁምላቸው ደጀኔ ከ17ኛ ክፍለ ጦር አዛዥነት የ508 ግብረ ኃይል አዛዥ፣ ኮ/ል (ብ/ጀ) ኃይሉ በረዋቅ የ17ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው ተሾሙ። ኮ/ል (ሜ/ጀ) አብዱላሂ ዑመር እዚያው 3ኛ ክ/ጦር ቆዩ።

እኔ ኮ/ል እስኪፋኖስ ገ/መስቀል የ506 ግብረ ኃይልን በጀት በሙሉ ለሰሜን ዕዝ እንዳስረክብና የ506 ግብረ ኃይልን ያሰበጀት በዘመቻና መረጃ ብቻ እንድመራ ትዕዛዝ ደረሰኝ። በማዕረግ በምቀድማቸው እንድታዘዝ ስለተደረገ በድጋሚ አዘንኩ። 506 ግብረ ኃይል በዘመቻና ወታደራዊ መረጃ ብቻ እንድመራ መደረጉን ሀሊናዬ አልተቀበለውም። ችግሩን በቅርብ ለማላይለትና አጠቃላይ አስተዳደሩን በቅርብ ለማልከታተልለት ጦር እንዲሞት ብቻ ለማዘዝ በመመደቤ ነው ሀሊናዬ ያልተቀበለው። ይሄንኑ ምክንያቴን አስረድቼ ትዕዛዙ እንዲታረምልኝ ከመፍትሔ ሃሳብ ጋር አመለከትኩ። የቀረበው የመፍትሄ ሐሳብ ግብረ ኃይሉ ፈርሶ ክፍለ ጦሮቹ በቀጥታ ራሳቸውን ችለው ከሰሜን ዕዝ ጋር እየተገናኙ እንዲሠሩ የሚል አዲስ ሃሳብ ነበር።

በመጀመሪያ ሃሳቤን ባለመቀበል ከቆዩ በኋላ የእኔን ያለመለሳለስ ሲመለከቱና ሁኔታውንም ረጋ ብለው ሲያዩት ትዕዛዛቸው ትክክል አለመሆኑን ተረዱ። በቀረበው ሃሳብም ተስማምተው የ506 ግብረ ኃይል ፈርሶ ክፍለ ጦሮቹ በቀጥታ ከሰሜን ዕዝ ጋር እንዲሰሩ ተወሰነ። ሰሜን

ዕዝን እንደገና ለማቋቋም ሲያስቡ በቅድሚያ ስለበጀቱም ማሰብ ነበረባቸው። ይህ ባለመሆኑ ግብረ ኃይሉን እንዲፈርስ ሆኗል።

የኤርትራና የትግራይ ዘመቻዎች በሙሉ ውጤት አልባ የሆኑት በአንድ ስህተት ነው። ይኸውም በየግንባሩና መሐል አገር የነበሩትን ልምድ ያላቸው ከፍተኛ መኮንኖችን፣ ለማራቅና ላለማማከር የተማለ ይመስላል። ሁሉንም ዘመቻ የውጊያ ልምድ በሌላቸው እንዲመሩ ከመደረጉም በላይ በተፋጠነ መልኩ እየታቀደ ስለሚሠራ ውጤቱ እንደተጠበቀውና እንደተፈለገው ሳይሆን ቀርቷል።

በዚህ ወቅት እኔ የማዘው 506 ግብረ ኃይል በመፍረሱ ያለ ሥራ ለአራት ወራት ተቀመጥኩ። በዚያ ወቅት የጀመርኩት የህይወት ታሪኬ አንድ መቶ ገፅ ያህል ሞልቶ ነበር። ኮምፒዮተር ባለመኖሩ በታይፕራይተር አፅፌ ለልጆቼ ስጥቻቸው ስለነበር ለአሁኑ ፅሑፌ መሠረት ሆኖኛል። ከዚያ የአራት ወር ያለሥራ መቀመጥ ያተረፍኩት ይሄንን ነው።

ያለሥራ በተቀመጥኩበት ጊዜ ከኮ/ል (ሜ/ጀ) ቁምላቸው ደጀኔ በኋላ የ508 ግብረ ኃይል አዛዥ የነበሩት ኮ/ል (ሜ/ጀ) አብዱላሂ ዑመር ድንገት ይታመማሉ። ቢታመሙም የሚተካህ ሰው የለንም በማለት ፈቃድ ማጣታቸው ቅሬታ ስለተሰማኝ ታክመው እንዲመጡ ለዕዙ ፈቃደኝነቴን ገልጬ ለ2 ወር ያህል ትዕዛዙን ተረክቤ ሠርቻለሁ። የመልሶ መቋቋምን የረዳሁ በመሆኔና ሁኔታውን ስለማውቀው ችግር አልነበረብኝም። ጦሩንም በየመከላከያ ወረዳው ስጎበኝ ቆየሁና ስጨርስ መኮንኑም ሕክምናቸውን ጨርሰው በመምጣታቸው የገነት ጦር ት/ቤት አዛዥ ሆኜ መመደቤ ተገለጠልኝ።

ገነት ጦር ትምህርት ቤት

ቀደም ብዬ ባዘገዘኩት ጦር አጠገብ ያለሥራ መቀመጤ መንፈሴን ነካው። በመሆኑም ከሠራዊቱ እንድሰናበት፣ ካልሆነም ወደ ምሥራቅ ተዛውሬ በብርጌድ አዛዥነትም እንድሰራ አመለከትኩ። ብዙ መንፈሴን ከነኩት በኋላ ወደ ገነት ጦር ት/ቤት እንድዛወር ተደረገ። በፈቃደኝነት የረዳሁት ኮ/ል አብዱላሂ ዑመር መጥቶ ዕዙኝ ከተረከበኝ

በኋላ ነሐሴ 22 ቀን 1972 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባሁ። ሰው ጠንካራ ነው። ያጋጠመውን ችግርና ሥቃይ ቶሎ መርሳት ባይችል ኖሮ በህይወት መቀጠል ባልቻለ ነበር።

ብዙ ፈተናዎች ቢፈራረቁብኝም ሁሉንም ረስቼ በአዲስ መንፈስ ሥራዬን ለመጀመር በነሐሴ 29 - 1972 ዓ.ም ገነት ጦር ት/ቤት አመለከትኩ። የወቅቱ የጦር ት/ቤት አዛዥ ከነበሩት ከኮ/ል (ብ/ጄ) አስፋው ሲራጎ ሠፊ ገለፃ ተደርጎልኝ ሥራዬን ጀመርኩ።

ሥራዬን ስጀምር ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም። በዕቅድና መልክ ባለው ሁኔታ ሥራዬን መጀመር ሲገባኝ ጠረጴዛዬ ላይ የተወሳሰቡ አስተዳደራዊ ችግሮች ተከምረው አገኘሁ። በቀላሉ ሊፈቱና ሊቃኑ የሚችሉ ባይሆኑም እነሱኑ ወደመፍታት ተሸጋገርኩ። ጊዜው የ1973 ዓ.ም የዘመን መለወጫ አካባቢ ጳጉሜ ውስጥ ነበር፤ ለችግሩ ክብደት የሰጠውም ይህ በዓል ነበር።

እንግዲህ የ41ኛው ዕጩ መኮንኖች ሠልጣኞችና አዲሱ ዓመት ተፋጥጠዋል። በዚህ በዘመን መለወጫ በአል ላይ ሠልጣኞቹ የተሻለ ምግብ ማግኘት ባለመቻላቸው ነው የቅሬታ ፍጥጫው የተፈጠረው። እጩ መኮንኖችን ይመግብ የነበረ አንድ መኩንን በወቅቱ ቁጥጥር ስላልተደረገበት 15 ሺህ ብር ያባክናል። በዚህም ቀደም ብለው በነበሩት የጦር ት/ቤቱ አዛዥ ግለሰቡ ታስሮ ሁኔታው እንዲጣራ በመደረግ ላይ ነው። ይሁንና በት/ቤቱ የምግብ በጀት ላይ የተፈጠረው ክፍተት ሠልጣኞቹን ከበዓሉ ጋር አንዲፋጠጡ አድርጓቸዋል።

መከላከያ ለበዓሉ መርዳት ይችል እንደሆነ ቢጠየቅ ሳይለማማ ይቀራል። ክፍተቱ አይኑን አፍጥጦ በመምጣቱ ጉርምርምታ ተፈጠረ። በእርግጥ እጩ መኮንኖቹ ማን እንደበደላቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ። ነገር ግን "ይህ ችግር የተፈጠረው በኮ/ል አስጢፋኖስ ጊዜ ነው" የሚል አሉባልታ መነዛቱ አልቀረም። ይሄ አሉባልታ በክስ መልክ እስከ መከላከያ ድረስ ሄዶ ለሚኒስትሩ ይነገራቸዋል። በአስቸኳይ በአገር መከላከያ ሚኒስትሩ ዘንድ ተጠርቼ ስለሁኔታው ተጠየቅሁ።

ለጓድ ሚኒስትሩም "ጦር ት/ቤቱን የተረከብኩት ጳጉሜ ውስጥ ነው። ችግሩ የተፈጠረው ደግሞ ከግንቦት 73 ዓ.ም ጀምሮ ነው። አጥፊ የተባለው መኮንን በቀድሞ የት/ቤቱ አዛዥ ትዕዛዝ ታስሮ እየተጣራ ይገኛል" የሚል ምላሼን ሰጠሁ።

ሚኒስትሩ ካዳመጡኝ በኋላ፦

"እኔ የጠራሁህ አንተ ችግሩን እንደፈፀምከው በመስማቴ ነው። ይቅርታ" ብለው ያሰናብቱኛል። የአሉባልታ ዕድሜው አጭር ነው የሚባለው ለዚህ አይደል?

ዕጩ ሠልጣኞች ሌላ መፍትሔ ስላልተገኘ በዓሉን ብቻ ሳይሆን ቀጣዩን ሥልጠና ሽሮአቸውን እየበሉ ለመፈፀም ተገደዱ።

ወደዚህ ት/ቤት ስመጣ ችግሩ ይህ ብቻ አልነበረም። በትምህርት ቤት አሰጣጥና ጥራትም በኩል ጉልህ ድክመት ነበር። አማካሪዎቻችን ቀደም ሲል በዳበረ ልምድ በልፅገው የተዘጋጁ መፅሐፍቶችን የኢምፔሪያሊስት ስልት ስለሆኑ አያስፈልጉም በማለት ከየተቀመጡበት እያወጡ ማርቀቂያ በማድረግ ሊያጠፉዋቸው በመሞከር ላይ ነበሩ። እኔ ይሄ ተገቢ ያለመሆኑን በመግለፅ ዳግመኛ ልናገኛቸው የማንችላቸውን እነዚህ መፅሐፍቶች ማሰባሰብ ጀመርኩ። ካላገቡ ሰኮንኖች መኖሪያ አንድ ክፍል ተረክበን ከዕጩ መኮንንነት አንስቶ እስከ አዛዥነት እና መምሪያ መኮንንነት ያሉት የትምህርት ዘርፎች ላይ የሚያተኩሩትን መፅሐፍትና መፅሐፎችን እንዲቀመጡ አደረኩ።



የኮት ጦር ት/ቤት አዛዥ በነበርኩበት ጊዜ

ቀደም ሲል በሰሜን ጦር ግንባር በነበርኩበት ጊዜ ግዳጃችንን በብቃት ለመወጣት ያልቻልነው በወታደሩ ድክመት ብቻ ይመስለኝ



የጎጎት ጦር ት/ቤት አዛዥ በአዘርጉበት ጊዜ

ነበር። ወደ ጦር ት/ቤቱ ከመጣሁ በኋላ ግን ይሄን አቋሜን ለመለወጥ ተገድጃለሁ። ድክመቱ የመስመራዊ መኮንኖችም ጭምር ነበር። በመኮንኖች የትምህርት ጥራትና ልምድ ማነስ ምክንያት የአያሌ አባሎቻችንን ህይወት በመስዋዕትነት እንደከፈልን ከተረዱት ወገኖች አንዱ ሆንኩ። ጦር ት/ቤቱ ቀድሞ የነበረበት ደረጃ ላይ ለመመለስ ጥረት አደረኩ። ከእኔ በፊት የነበሩት ሁለቱ የት/ቤቱ አዛዦች መሥራትና ማሻሻል ሲችሉ በሶቪየት አማካሪዎች እንቅፋትነት እንዳላደረጉት ነግረውኛል።

በወቅቱ የነበሩ አማካሪዎች የሚመረቁ መኮንኖችን ደካማ በማድረግ በአማካሪነታቸው ተፈላጊ ሆነው የመቆየት ህልም ይዘው እንደሚንቀሳቀሱ ተረዳሁ። በዚህም ረዘም ላለ ጊዜ ለመቆየት ስለሚፈልጉ ብቻ ለመኮንኖች በጣም አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት አይነቶችን እንዳይማሩ ያደርጉ ነበር። አማካሪዎቻችን ቀደም ሲል ዳጎስ ያለ፣ በራሳቸው ቋንቋ የተፃፈ የሥልት ንድፍ ያለበት መጽሐፋቸውን አሳይተውኝ ነበር። እንደገለፃቸው ከሆነ ግሩም የሚመስል ነበር።



የሶት ጦር ት/ቤት 41ኛው እዉ መኮንኖች ሲመረቁ ለሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማሪያም በትያትር መልክ ምስጋናቸዉን እንዴት እንደሚገልፁ ገለፃ ሲደረግላቸው

ዘግይቼ ሴራቸው ሲገባኝ ዋናውን አማካሪ ከነረዳቱ አስጠርቼ "ካሳያችሁኝ ዳጎስ ያለ የስልት ትምህርት መፅሐፍ ላይ በተሟላ መልኩ በእንግሊዘኛ ተርጉማችሁና አዘጋጅታችሁ ስጡኝ። ያለበለዚያ ግን ጦር ትምህርት ቤቱ በጣም የዳበረ የማስተማሪያ መፅሐፍቶችና ዕቃዎች ስላሉት በዚያ ማስተማር እንጀምራለን" አልኳቸው።

እነሱም "እሱ የያዝከውክ የኢምፔሪያሊስቶች ታክቲክ ነው" ይሉኛል።

"እሺ የእናንተን የተሟላ ትምህርት የያዘ ፅሁፍ ስጡኝ" አልኳቸው። አልተስማሙም። "እንግዲያውስ ስልት የሰውን ልጅ አእምሮ ወይም አስተሳሰብ የሚያሰፋና ብስለቱንም የሚያዳብርበት እንጂ ሶሻሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝም በሚል ከርዕዮተ አለም ጋር የሚያገናኘው የለም" አልኩ።

አማካሪዎቻችን ያልተስማሙ ቢሆንም ክርክሩ እዚህ ላይ ተቋጭቶ እኔ ወደተግባር ገባሁ። የአገር ጉዳይ ስለሆነብኝ ወደኋላ አላልኩም። የሚመጣውን ለመቀበል ወሰንኩ። በመጀመሪያ ትምህርቱን ለማያውቁ አስተማሪዎች ሥልጠና አዘጋጀሁ። ከጦር ት/ቤት በድሮ ትምህርት ከተመረቁት ውጭ ከመከላከያም ውሎ አበል እየከፈልኩ ከፍተኛ መኮንኖችን በማስመጣት ሥልጠናውን ጀመርኩ። አስተማሪ የነበሩት ተማሪ ሆነው የቀድሞውን የሥልጠና ስልት መቅሰም ሲጀምሩ "ይሄንን ለምን ቀድማችሁ አላስተማራችሁንም?" ማለት ጀመሩ። ወደዱትም።

ይሁንና አማካሪዎቻችን "ኮ/ል አስጢፋኖስ እኛ የማናውቀውን ትምህርት ይሰጣል" ሲሉ ከሰሱ።

የአገር መከላከያው ሚኒስትር ሜ/ጄ (ሌ/ጄ) ተስፋዬ ገብረኪዳንና የመከላከያ የፖለቲካ ኃላፊው ሜ/ጄ ገብረየስ ወ/ሃና ወደ ገጎት ጦር ት/ቤት እንደሚመጡ አስማለሁ። ከምድር ጦር ትምህርት ክፍል ኮ/ል (ብ/ጄ) አዲስ አግላቸው ይሄንን በነገረኝ ማግስት እንደተባለው መጡ። ቢሮ እንድንገባ አድርገው ከአማካሪዎች ጋር ልግባባ ያልቻልኩበትን ምክንያት ጠየቁኝ።

"ያልተግባባነው በትምህርት አሰጣጥ ላይ ነው" ስል ቀጠልኩ "ጦር ት/ቤቱ የዳበረ የማስተማሪያ መፅሐፍትና ልምድ አለው። ዛሬ ለእግረኛ ውጊያ ትምህርት አማካሪ የሚያስፈልገን አይመስለኝም። ከተጠቀምንባቸው ብዙ ሊያስተምሩ የሚችሉ ሥራ ፈትተው የተቀመጡ ከፍተኛና መስመራዊ መኮንኖች አሉን። አሁን እየተሰጠ ያለው ትምህርት አንድን መኮንን ብቁ የሚያደርግ አይደለም።"

"አታስተምሩ አላልንም፣ ተስማሙና ሥሩ ነው ያልነው" አሉ ሚኒስትሩ።



የካት ጦር ት/ቤት 41ኛው አጭ መኮንኖች ሲመረቁ ለሊቀመንበር መንግስቱ ኃይለማሪያም
በትያትር መልክ ምስጢሮች እንዴት እንደሚባክኑ ገለፃ ሲደረግላቸው

ቀደም ሲል የጦር ት/ቤቱ አዛዥ የነበሩት ኮ/ል አዲስ አግላቸው ጣልቃ ገብተው "ይኸው እንደምታዩት ነው" አሉ። "ለመስማማትኮ እነሱ ያሉትን መፈፀም አለብን። በዚህ ምክንያት ነው ችግር የሚፈጠረው" ሲል መለሰ።

መከላከያ ሚኒስትሩ "ዘዴኛ ሁኑ ማለታችን ነው" አሉ

በዚህ መካከል የአገር መከላከያ የፖለቲካ ኃላፊው ሜ/ጄ ገብረየስ ወ/ሃና በቁጣ መልክ "ሶቪየቶችን አታስቀይሙብን። ሃያ አምስት ሚሊየን ህዝብ ያለቀባቸው ልምድ ያላቸው ናቸው" አሉ።

"ጌታዬ" አልኩ እኔም "እኛ እንደነሱ የምናስጨርሰው ሃያ አምስት ሚሊዮን ህዝብ የለንም። በእነስተኛ ኃይል እየተዋጋን ውጤት ማምጣት ነው የምንፈልገው። ደሞም 25 ሚሊየን ማስጨረስ ድክመት ይመስለኛል" በማለት መልስ ሰጠሁ።

ሁኔታው ያላማራቸው የመከላከያ ሚኒስትሩ ሜ/ጄ ተስፋዬ ገ/ኪዳን "እዚሁ ላይ እናብቃና አካባቢውን እንጎብኝ" ሲሉ ጣልቃ ገቡ። ወዲያውም የጦር ት/ቤቱ መጎብኘት ጀመርን። በጉብኝቱም ወቅት እንዴት ትምህርት እንደሚሰጥ በማላየት ያለውን ችግርና የሚያስከትለውን ድክመት ገለፅኩላቸው። እግረ መንገዴንም የቀድሞውን አነስተኛውን የሰልፍ ሜዳ ለመተካት ክፍት በሆነው ሜዳ ላይ ያስጀመርኩትን የሰልፍ ሜዳ አሳይቼ ምሣ በልተን ተለያየን።

በጀመርኩት ገፋሁበት። የምድር ጦር ትምህርት መኮንን ኮ/ል (ብ/ጄ) አዲስ አግላቸው እንደሚረዳኝ ቃል ስለገባልኝ ማስተማሩን ቀጠልኩበት። 43ኛው ዕጩ መኮንኖች ገብተው ትምህርቱን ቢጀምሩም አማካሪዎቻችን በድጋሚ ስለከሰሱ ለአስተማሪዎቹ ይሰጥ የነበረው ትምህርት ተቋረጠባቸው። ከአገር ጉዳይ ይልቅ አማካሪዎቻችን እንዳይቀየሟቸው ስለሰጉ ብቻ እኔን ከቦታዬ ላይ ለመቀየር አስፈላጊ ሆኖ አገኙት። ኮ/ል (ብ/ጄ) እሸቱ መኮንን ቀይረውኝ ብዙ መኮንኖች ተመድበውላቸው መጡ። ጦር ት/ቤቱንም የቀድሞ ደረጃውን እንዳይለቅ ከአደራ ጋር አስረክቤ ወደተዛወርኩበት ወደ ምድር ጦር ዕቅድና ፕሮግራም መምሪያ ሄድኩ። ኮ/ል እሸቱ እኔ የጀመርኩት ትምህርት እንዳይቀጥል በቅድሚያ ስለተነገራቸው መቋረጡን አረጋገጥኩ። ያም ሆኖ ኮሎኔሉ ሌላው አደራ ያልኳቸውን እኔ ያስጀመርኩትን ሜዳ ላሰራው ካሰብኩት በበለጠ ሁኔታ አሳምረው በማስጨረሳቸው እንደ ማካካሻ ቆጥሬ እጅግ ደስ ተሰኝቻለሁ።

ምድር ጦር

ወደ ምድር ጦር ዕቅድና ፕሮግራም መምሪያ መዛወሬ አላስከፋኝም። እንደውም በአንፃሩ ደስ ተሰኝቻለሁ። ምክንያቱም በዕቅድና ፕሮግራም በመምሪያው የሚሰሩ ብዙ ሥራዎች ስለነበሩ ሥራ ፈትነት እዚህ አይታሰብም። ዕቅድና ፕሮግራም የሚወጣላቸው ዘርፎች ብዙ ናቸው። በትምህርት፣ በድርጅት፣ በሰው ኃይል ቁጥጥር፣ በምድር ጦር የአቋም መዋቅር ላይ ዕቅድና ፕሮግራም ይወጣላቸዋል። በበጀት አሰራር፣ በእርዳታና በግዢ ስለሚገቡ ጦር መሣሪያዎች እንዲሁም የተለያዩ ንብረቶችን በተመለከተ ዕቅድና ፕሮግራም አለ። በተጨማሪም በእርዳታም ሆነ በግዢ የሚገቡትን ንብረቶች ብዛት፣ ጥራትና አስፈላጊነትን እያጠና ለምድር ጦር ዋና አዛዥና ለሚመለከታቸው መምሪያዎች ያመለክታል። ንብረቶቹ የሚገቡበትን ጊዜ የመከታተልና የመቆጣጠር ኃላፊነትና ሌሎች ሥራዎችንም የመርዳት ግዴታ ያለበት መምሪያ ነው።

ይህ ክፍል በየሙያው የበሰሉ መኮንኖችና ሲቪል ሠራተኖች ቢያስፈልጉትም ሥራው እየተከናወነ ያለው በሁለትና ሦስት አባሎች ብቻ ነበር። በምድር ጦር ካሉ መምሪያዎች ሁሉ በላይ ብዙ ሥራ ሊሠራበት የሚችል ሠፊ መሆን ሲገባው ኮስሞኖ መስተዋሉ አልቀረም።

ችግራቸውን ሊያውቁ የሚችሉት በየጊዜው እየተመደቡ የሥራ ቀደምት ያለበት ቦታ የሚመደቡ የምድር ጦር አዛዦች ብቻ ናቸው። በአንድ ወቅት የምድር ጦር አቋም መዋቅር ድንገት በመለወጡ ብዙ የአሰራር ችግሮች ተፈጥረው አስተውያለሁ። ከጦሩ ጋር በነበርኩበት በዚያን ጊዜ ችግሩ ገጥጦ ስለተመለከትኩት አሁን መዋቅሩ እንዲታይ ሲጠየቅ እጅግ በጣም ደስ ብሎኝ ነበር።

***

የምድር ጦር ልዩ ልዩ ኪነታዊ ክፍሎች በሙሉ ፈርሰው ነበር። የእነዚህ ክፍሎች የሙያ ሥልጠና፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል ምደባ፣ የሚበላሹትን የተለያዩ መሣሪያዎች ጥገና ሲታሰብ ዳግም ለማካሄድ ችግር ተፈጥሮ ነበር። ባለሙያዎችን ኃላፊነት ወስደው የሚያሰለጥኑ እና የሚመደቡ ክፍሎችም በመፍረሳቸው የባለሙያ እጥረት ነበር።

የቀድሞው የምድር ጦር መዋቅር እጅግ በጣም ጥሩ የነበረ ሲሆን የኢምፔሪያሊስት ነው እየተባ በአማካሪዎቻችን ግፊት በመለወጡ አቅል አጥቶ ብዙዎቹ አሰራሮች ተጎድተው እንደነበር አስታውሳለሁ። ጥገናን በተመለከተ የሬዲዮ፣ የመድፍ፣ የታንክና የመሣሪያዎች እንዲሁም ሌሎች ጥገናዎች በተሽከርካሪ ጥገና ውስጥ ተመድበው ነበር። በዚህም የጥገና ወጪዎች በሙሉ ለተሽከርካሪ ጥገና እየዋለ ብዙ ሬዲዮኖችና ከላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ መሳሪያዎች በየዕዙ ተከምረው ይታዩ ነበር።

የማዕረግ ቀደምትነት ስለነበረኝ በእኔ ሰብሳቢነት፣ የምድር ጦር ድርጅት መምሪያ ኃላፊ በሆኑት ኮ/ል (ሚ/ጄ) አለማየሁ አየለና አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ የሆኑት ኮ/ል (ብ/ጄ) ፈቃደ ክበበው ሆነን መዋቅሩን እንድናጠና ታዘዝን። የጥናታችን ውጤት የቀድሞውን የምድር ጦር መዋቅር አንዳንድ ነገሮች በማሻሻል ሰርተን በወቅቱ ለነበሩት የምድር ጦር አዛዥ አቀረብን። ሥራውን የጀመርነው ሁለት የመምሪያ መኮንኖች ራሳቸውን እቦታው ላይ እንደሌሉ ቆጥረው ለምክትሎቻቸው ሙሉ ውክልና ሰጥተው ነበር።

አዛዡ ጥናታችንን ካዩ በኋላ "ይሄ በሊቀመንበሩ የተወሰነ ስለሆነ የሰው ኃይል ጨምሩ እንጂ አቋሙ አይለወጥም" የሚል መልስ ሰጡን።

እኛም "አቋሙ ሲፀድቅ በሥራ እየተፈተነ፣ መሻሻል የሚገባው ይሻሻል ተባለ እንጂ ቋሚ ሆኖ ይሠራበት አልተባለም" በማለት ተከራከርን። ነገር ግን የአዛዡን ሃሳብ ማስቀየር አልቻልንም። ጥናታችን ተቀባይነት ሲያጣ አብረውኝ በእኔ ሰብሳቢነት ሲሰሩ የቆዩት የመምሪያ መኮንኖች ወደየ መምሪያዎቻቸው ተመለሱ።

እኔም አዲስ ዝውውር መጣልኝ። "ወቅቱ የቀይ ኮከብ ዘመቻ" የታቀደበት በመሆኑ በሹመትና ሽልማት ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት ተመድቤ ወደ ኤርትራ እንዲሄድ ተመደብኩ። ታህሳስ 19 - 1974 ዓ.ም ከአለቆቼ ጋር ወደ አስመራ ተንቀሳቀስኩ።

ተቃዋሚው ኃይል ተከታታይ ማጥቃት በማድረጉና ጦሩ ዶገአሌን ለቆ በማፈግፈጉ ሻዕቢያም ዶጋሌን ለቆ የምጽዋን ከተማ ምአራብ ክፍል እደጋንና አጂኘን እንዲሁም ለከተማው ውሃ የሚያከፋፍለውን ማጠራቀሚያ ያዘ። ጦሩ በውሃ ጥም ተፈትቶ እጁን እንዲሰጥ ለማድረግ በመቆረጡ አማካሪዎቻችን አፋጣኝ መልስ በመስጠት ከባህር ኃይል ማጠራቀሚያ ውስጥ ያለው ውሃ ከማለቁ በፊት ከየመን በራሺያኖች መርከብ እየመጣ በምጽዋ ባህር ኃይል ማጠራቀሚያ እየተከማቸ በቀን ለጦሩም ሆነ ለምጽዋ ህዝብ በተመደበለት መጠን በምጽዋ ባህር ኃይል አከፋፋይነት ይዳረስ ነበር። ከየመን እንዲመጣ የተደረገውም የለስብ ውሃ መጠን አነስተኛ በመሆኑ ነበር።

ሩሲያኖች ምጽዋ ላይ ይከላከል ለነበረው ጦር አፋጣኝ መልስ በመስጠት በውሃ ጥም እንዳይፈታ በማድረጋቸውና ዓለም አቀፍ ግዴታቸውን በመወጣታቸው ከ1970ው የምጽዋ ታሪክ ጋር ስናስታውሳቸውና ስናመሰግናቸው እንኖራለን።

ማጠቃለያ

አየር ኃይል

እኔ አየር ወለድ ውስጥ በነበረኝ የስራ ግንኙነት አየር ኃይልን ከጠቅላይ መምሪያው ጀምሮ የ1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ የአየር ምድቦችን አኩሪ ስራ ከማውቀው በላይ በምስራቁ ግንባር ለሶስተኛ ክፍለ ጦር ተደራቢ ሆኜ በሰራሁበት ጊዜ በቶጉ ውጫሌ ወረራና እንዲሁም በዋርዶር የአየር ኃይልን አኩሪ ውጤት አይቻለሁ። በኢርትራም ውስጥ ከአየር ወለድና በኢርትራ ክፍለ ሀገር ከነበረው ጦር ጋር በልዩ ልዩ የስራ ምድቦችና ኃላፊነቶች ተመድቤ በሰራሁበት ጊዜ ለ1ኛውና ከ2ኛው የአየር ምድብ ጋር ያልተቋረጠ የሥራ ግንኙነት ነበረኝ።

ሁለተኛው አየር ምድብ 15ኛ ሻለቃ ናቅፋ ላይ ተከቦ በነበረው ጊዜና ለቆ እስከወጣበት በየቀኑ እየተመላለሰ እንዳይደመሰስ የረዳ ጀግና የአየር ኃይላችን ነው።

2ኛው አየር ምድብ በ2ኛ ክ/ጦር፣ በሰሜን እዝና በኋላም በዘመቻ መምሪያው በሚሰጠው መመሪያና ትእዛዝ መሰረት በማጥቃት፣ በማሳደድ፣ በማፈግፈግና በመከላከል ጊዜ ወደር የሌላቸው ስራዎችን ያከናወነ ክፍል ለመሆኑ አይነተኛ ምስክር ነኝ። እኔ ኤርትራ ውስጥ በሰራሁበት ጊዜ የ2ኛው አየር ምድብ አዛዦች የነበሩት ብ/ጄ ዮሐንስ ወ/ማርያም፣ ሚ/ጄ ፋንታ በላይ፣ ኮ/ል ብርሃኑ ሀ/ወልድ፣ ብ/ጄ ሰሎሞን በጋሻው፣ ሚ/ጄ አምሀ ደስታ ናቸው።

በክ/ል (ሚ/ጄ) አምሀ ደስታ የሚመራው 2ኛው የአየር ምድብ ለ12/3/1970 - በ12/4 - 14/4 -28/4/1970 ዓ.ም. በደንስሱና በምጽዋ ግንባር ለተደረጉ ፍልሚያዎች በማጥቃቱም በመከላከሉም ጊዜ እንዲሁም ለአርዳታና ለማጠናከር በሚመጡት የሻዕቢያ ጦር ላይ መተኪያ ለሌላት ህይወታቸው ሳይሳሱ ዝቅ በማለት ኢላማቸውን በትክክል በመምታት የምጽዋን ወደብ ለማዳን ያደረጉት ተጋድሎ ከምጽዋ ታሪክ ጋር አብሮ ሲወሳ ይኖራል።



የአየር ኃይልና የአየር ወለድ ሠራዊቶች በአንድነት ተባብረው ይሰሩ ነበር

የምድር ጦር አየር ክፍል

የምድር ጦር አየር ክፍል (አቪዬሽን) ሲቋቋም በክ/ል ይገዙ ይመኑ በምድር ጦር ውስጥ ሲሆን፣ በኋላም በክ/ል እሸቴ ዋጋዬ አዛዥነት ከአየር ኃይል፣ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጦር አካዳሚ መኮንኖች፣ ከአየር ወለድና ከሌሎችም የምድር ጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች በተመረጡ መኮንኖችና ባለሌላ ማእረጐች ነበር።

ይህ ክፍል ምንጊዜም የምድር ጦር ታሪክ ሲገለጽ አብሮ ሲታወስ የሚኖር ነው። ለተዋጊው ጦርም ሆነ ለምድር ጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች በሰጠው እጅግ በጣም የሚያኮራ አገልግሎት፣ በተዋጊውም ሆነ በምድር ጦር ልዩ ልዩ ክፍሎች እጅግ የተወደደና የተመሰገነ ታሪክ የሚይረሳው ክፍል ነበር።

የምድር ጦር አየር ክፍል (አቪዬሽን) ተዋጊው የእግረኛው ጦር የመጓጓዣ መኪና ሳያስፈልገው በእግሩ ተራራና ገደሉን፣ ዳገት ቁልቁለቱንና


ሸለቆውን እየወጣና እየወረደ ተቃዋሚዎችን በሚያድንበት ጊዜ የሚንቀሳቀሰው የአምስት ቀን ቀለቡን፣ ለውጊያ የሚጠቀምበትን ሁለት መደበኛ ጭነት ጥይት (ቤዚክ ሎድ) እንደሚንቀሳቀሰው ጦር ኃይል ብዛት የተለያዩ ቀላልና ከባድ መሣሪያዎችን፣ እንዲሁም የግንኙነት መሣሪያዎችን ይዞ ነበር። የወጣው ጦር ከተቃዋሚዎች ጋር ጦርነት ሲያካሂድ ጦሩ የተለያዩ የጥይት አይነቶች በሚያስፈልጉበት ጊዜና የአምስት ቀን ቀለቡንም በሚጨርስበት ወቅት ለህይወታቸው ሳይሳሱ በከባድ ተኩስ ውስጥና ለማረፍ በሚያስችግርበት ቦታ ሁሉ በማረፍ አስፈላጊውን ድርጅት ሁሉ በማቅረብ ቁስለኞችንም በማግለል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ክፍል ነው። ጦሩም አቪዬሽኑ የሚያበራቸው ሄሊኮፕተሮች በመጡ ቁጥር "እናት መቀነት! እናት አጉራሻችን መጣች!" እያሉ ያሞካሿቸው ነበር።

የምድር ጦር አየር ክፍል (አቪዬሽን) ከሙያ አንፃር የተሻለ ድጋፍ ለማግኘት ሲባል ወደ አየር ኃይል እስከተዛወረና ከተዛወረም በኋላ በድርጅት ማቅረብ ብቻ አልተወሰነም። በሲሲና፣ በኦተርና በሌሎችም የጠላትን ወረዳ በአውሮፕላኖች እየቃኘ መረጃዎችን ሰጥቷል፣ ጦርን ከቦታ ቦታ አጓጉዘዋል። በከፍተኛ ውጊያ ላይ ሳለ ጦር እርዳታ በማድረስ አይነተኛ ሚና ተጫውቷል። በአየር ላይ ሆነው ለተዋጊ አውሮፕላኖችና ለከባድ መሣሪያዎች ትክክለኛ ኢላማቸውን እንዲመቱ ተኩስ በመምራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጋቸውም በላይ በተጨማሪም ሮኬቶችና መትረየሶች የተጠመደባቸው ሔሊኮፕተሮች በማጥቃትም ሆነ በመከላከል ጊዜ የተኩስ ድጋፍ በመስጠት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የምድር ጦር አየር ክፍል (አቪዬሽን) እንደ እግረኛው ጦርና አየር ኃይል ሰፋ ያለ የራሱ ታሪክ ያለው ክፍል ነው። አንድ ቀን ዘርዝሮ ባለ መልኩ እንደሚጻፍ እምነቴ ነው።

ትራንስፖርት እስኳድሮን

ትራንስፖርት እስኳድሮን በየአቅጣጫው ለእግረኛው ሠራዊት ካለበት ቦታ በማረፍ፣ ማረፊያም በሌለበት ቦታ በፓራሹት በመጣል የተለያዩ ድርጅቶችን ያቀርብ ነበር፣ ሠራዊቱንም ሆነ ባለሥልጣኖችን ከቦታ ቦታ ያጓጉዝ ነበር። በተለይም የአየር ወለድን ጦር በሥልጠናና በልምምድ፣ ለሥነ ልቦና ውጊያ ለሚደርጉና በጦር ሜዳም በጠላት ለተከበበ ጦር እርዳታ አየር ወለድን በተኩስ መሐል በማዘለልና በማንኛውም የጠላት ወረዳ ከፍተኛ ቦንቦችን እንደ ቦምቦር አውሮፕላን በመጣል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ የአንደኛው የአየር ኃይል መደብ አካል ነው።



የአየር ኃይልና የአየር ወለድ ሠራዊቶች በአንድነት ተጣብረው ይሰሩ ነበር

የምፅዋ ስሥመራን መንገድ መክፈት ዳግም የመጣ ዕቅድ

በጦሩ ጠንካራ መከላከል ሻዕቢያ ክፉኛ ከተመታ በኋላ የምፅዋ ግንባር አንድ ጥይት የማይጮህበት ቦታ ሆነ። በዚህ ፀጥተኛ ሁኔታ ውስጥ የሚኖረው ጦር ለመጠጥም ሆነ ለፅዳት የሚሆን ውሃ ያጣ ጀመር። በመሆኑም የምፅዋ አስመራ መንገድ መከፈት ብቸኛው አማራጭ ሆኖ ቀረበ። ዕቅድ ወጥቶለት መንገድ የማስከፈቱን ማጥቃት ለማጠናከር 29ኛው ሜካናይዝድ ጦር ከአሰብ ወደ ምፅዋ እንዲንቀሳቀስ ተወሰነ። በክ/ል (ሜ/ጄኔራል) አስራት ብሩና በም/አዛዥ ሌ/ኮ (ክ/ል) ነጋሽ ዱባለ የሚመራው ይሄ ጦር ከምፅዋ የአየር ሁኔታ ጋር እንዲለማመድ በቅድሚያ ዳህላክ ገባ። በታንከኛነቱ በጣም የሚታወቀው ሻለቃ (ብ/ጄ) ካሣዬ ጪመዳ የታንከኛው ሻለቃ አዛዥ ነበር። የሜካናይዝዱና የእግረኛው ሻለቆች አዛዦች ሻምበል (ክ/ል) ዘውዴ ገብረሣዲቅና ሌላ ስሙን የዘነጋሁት አንድ ሻምበል ነበሩ።

የምፅዋ አሥመራን መንገድ የመክፈት ማጥቃት ሊወሰን የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መቀሌ ላይ ተሰባስቦ ወደ ኤርትራ እንደሚዘምት መረጃ ይደርሰዋል። ሻዕቢያም ይህንን ጦር ለማገድ ከአንዳንድ አደገኛና አስቸጋሪ ቦታዎች ለቆ የደጋውን አውራጃዎች ሙጥኝ ማለቱ ነበር። በአስመራ ዙሪያ መከማቸቱ ጥሩ ማጥቃት ከተደረገ መንገዱን በቀላሉ መክፈት እንደሚቻል መተማመኛ ሆነ። ዕቅዱ ሲወጣ እግረኛው በታንከኛና በአየር እየተደገፈ ማጥቃት የሚችልበት ሁኔታ ማመቻቸት እንዳለ ግልፅ ሆነ። የከተማ ውስጥ ውጊያ ልምምድ ምፅዋ ባህር ኃይል ሠፈር እንዲካሄድ ተወሰነ። ከታንክ ጋር ልምምድ ደግሞ ዳህላክ ደሴት ላይ እንዲደረግ ታቀደ። የመሪዎች እጥረት ስለነበር ለጓድና ለመቶ መሪነት የሚያገለግሉ ከመደበኛው ጦር መካከል ተመለመሉ። እነዚህ ወታደሮችና የበታች ሹሞች ተመርጠው ቀጥታ ለልምምድ የተላኩት ዳህላክ ደሴት ላይ ነበር። ለልምምድም ሆነ ለልዩ ልዩ ስልጠና የተላከው ጦር ልምምዱ ከተከናወነ በኋላ ተጠቃልሎ ምፅዋ እንዲከት ተደረገ።

የዘመቻው እቅድ በጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም (በኋላ የአገር መከላለያ ሚኒስትር በነበሩት) በሜ/ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ ኃ/ማሪያም፣ በኮሎኔል (ሜ/ጀ) መርዕድ ንጉሴ፣ በክ/ል አይተነው በላይና በእኔ ሌ/ኮ (ክ/ል) አስጢፋኖስ ገብረመስቀል የግንባሩ አስተባባሪ ተዘጋጀ። ከአማካሪዎቻችን ጋር በመመካከር ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላም ዕቅዱ ፀደቀ።

ዕቅዱ ሻዕቢያን በማዘናጋት ላይ ያተኮረ ነበር። የሻዕቢያን ይዞታ በከባድ መሣሪያ፣ በአየርና በታንክ ቀጥታ ተኩስ ለስምንት ቀን ያህል በመደብደብ ማጥቃት ስለመኖሩ እንዲዘናጉና 'ልማዳቸው ነው' እንዲሉ ማድረግን ያካትታል። መዘናጋታቸው እንደተረጋገጠም 29ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ማጥቃቱን ጀምሮ ሰብሮ እንዲገባ። በእኔ የሚታዘዘው እግረኛ ጦር ደግሞ ሻዕቢያ ሊከላከል በማይችልበት በጉን በኩል 29ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድን ተከትሎ በመግባት ሻዕቢያን መደምሰስ የዕቅዱ ግብ ነበር።

ትዕዛዙ ለ29ኛ ሜ/ብርጌድ፣ ለሁለቱም ግንባር አስተባባሪ፣ ለ2ኛው አየር ምድብ አዛዥና ለምፅዋ ባህር ኃይል አዛዥ ተሰጠ። ሁሉም ጦሮች እንዴት እንደሚያጠቁና መረዳዳት እንደሚችሉ ቅኝት አደረጉ።

በሁለተኛው ቀን ላይ በዕቅዱ መሠረት የአየርና የከባድ መሣሪያ ድብደባው ተጀመረ። እንዳቀድነው ሻዕቢያ ተረበሸ። በየመገናኛ መሣሪያዎቻቸው በየት በኩል ማጥቃት እንደተጀመረ በመጠያየቅ ተካለቡ። ግራ ተጋቡ።

ከተወሰነ ድብደባ በኋላ የዕለቱ የከባድ መሣሪያ ተኩስ ቆመ። የሁለተኛው ቀን ከባድ መሣሪያ ድብደባ ሲጀመር እንዲሁ ግራ ተጋቡ። ቀናቶች እየጨመሩ ድብደባው ለ7 ቀን ያህል እየቀጠለ ሲሄድ የሻዕቢያ ግራ መጋባትና የመገናኛ መሣሪያዎቻቸው ውትወታ ቆመ። "ተዉዋቸው፣ ልማዳቸው ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ ደረሱ። ስለዚህ በቀጣዩ ቀን ከከባድ መሣሪያ ድብደባው ጋር ማጥቃት ይጀመራል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደረሰ። ሁሉም ለማጥቃቱ ተዘጋጅቶ ንጋቱን በመጠባበቅ ላይ ሳለ ሜ/ጄ ኃይለጊዮርጊስ ኃ/ማሪያም ከምሽቱ 2 ሰዓት ላይ አንድ ትዕዛዝ አስተላለፉ። ግራ የሚያጋባና ምክንያቱ የማይታወቀው ትዕዛዝ ማጥቃት ማድረጋችን እንደቀረ የሚገልፅ ነበር።

"ለምን?" የሁሉም ጥያቄ ቢሆንም ምክንያቱን ሊገለፅልን አልቻለም። ከማጥቃት መቅረቱ ትዕዛዝ ጋር, የመኮንኖች የዝውውር መመሪያም ተልኮ ነበር። ብ/ጄ መርዕድ ንጉሴ ወደ ዕዛቸው እንዲመለሱ፣

ኮ/ል አስራት ብሩ የገነት ጦር ት/ቤት አዛዥ ሆነው ወደዚያው እንዲንቀሳቀሱ፣ ሌ/ኮ ነጋሽ ዱባለ ወደ ደርግ ጽ/ቤት እንዲመለሱ ታዘዙ። ለእኔም በግል ማጥቃቱ የቀረ በመሆኑ ምንም አይነት ማጥቃት እንዳይደረግ ትዕዛዝ ሰጡኝ። እንደ ትዕዛዙም በአፋጣኝ የመኮንኖቹን ዝውውር ለማከናወን ሜ/ጀ ሃይለ ጊዮርጊስ ሀብተማርያምና ሌሎች መኮንኖች በጠሩት ሄሊኮፕተር ወደ አስመራ ተነቃነቁ።

የማጥቃቱ መቅረት የጦሩን ሁሉ ወሽመጥ ቆረጠው። ማጥቃት እንደምንሰነዝር ሲነገር ሠራዊቱ እጅግ ተደስቶ ዕለቷን በጉጉት ሲጠብቅ ነበር። የውሃ እጥረቱ ችግር ስላንገሸገሸው "እኛ እየጠማን ተቃዋሚው እንደ ልቡ እየጠጣ አይቀርም" በማለት ማጥቃቱን ከልቡ ደግፎት ነበር። የማጥቃቱ መቅረት ሲሰማ እጅግ አድርጎ ተበሳጨ። ቁጣም ታየበት። ማጥቃቱ የቀረበት ምክንያት ለመኮንኖችም ሆነ ለጦሩ ባለመነገሩ ድንጋሬ ተከተለ። ለሁለተኛ ጊዜ ቃል የተገባለት ነበርና ጦሩ በአዛዦቹ ላይ እምነት እስከማጣት ደረሰ። እናም ሁኔታው በጦሩ ውስጥ ለተሰገሰጉት ፀረ- አብዮተኞች የተመቸ ሆነ ቅስቀሳቸው በማጥቃት መቅረቱ ላይ አነጣጠረ። እስጊ ሁኔታዎች ተፈጠሩ። ለፀረ አብዮተኞቹ ፕሮፓጋንዳ የአፀፋ ፕሮፓጋንዳ የሚያካሂዱ ጥቂት እውነተኛ ካድሬዎች ሠራዊቱ መካከል እንዲገኙ ተደረገ። የአፀፋ ፕሮፓጋንዳውም ማጥቃቱ የቀረው ለጦሩ በማሰብ እንደሆነ መግለፅ ሆነ። ጦሩ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዳይደርስ በማሰብ ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት እስኪመጣ ማጥቃቱ እንዲዘገይ መደረጉን ለጦሩ ተነገረው። አደጋው የሚቀነስበት መንገድ ከተመቻቸ በኋላ ማጥቃቱ እንደሚጀመር ተብራራለት። በአፀፋ ፕሮፓጋንዳው ላይ አስተባባሪው እኔ ጭምር ተሳትፌ ሁኔታዎችን ለማቀዝቀዝ ብሞክርም ጦሩ የሚቀበል አልሆነም።

የፀረ-አብዮተኞቹ አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ተጠናክሮ ቀጠለ። ቅስቀሳቸው ወደ ማሣደም ተሸጋግሮ በጦሩ መካከል በፅሁፍ ያዘዋውሩ ጀመር። የሁለቱን ግንባሮች አስተባባሪ የእኔን ሥም ያካተተ የብርጌድና የሻለቃ አዛዦችን እንዲሁም የባህር ኃይል ከፍተኛ መኮንኖችና ታዋቂ መኮንኖችን ሥም ያጣቀስ ወረቀት በጦሩ መካከል ሲዘዋወር በሴት ሚሊሺያ (ሻለቃ ባሻ) እታፈራሁ ተይዞ ለኛ ደረሰን። ሥም ዝርዝራቸው ወረቀቱ ላይ የሰፈረው ሁሉ ተይዘው እንዲታሰሩና እርምጃ እንዲወሰድባቸው የጦሩን ትብብር የሚጠይቅ መልዕክት ነበረው።

ወረቀቱን ሲያዘዋውር የነበረው ሚሊሺያ ተይዞ ሲጠየቅ ማን እንደሰጠው ጠቆመ። ከአሳዳሚዎቹ አንዱ እኔ አየር ወለድ በነበርኩበት

ጊዜ የተቀጠረ በጣም የማውቀው፣ እሱም የሚያውቀኝ ፯ አለቃ መርሻ የሚባል ወታደር ነው። በእሱም በጣም አዘንኩ።

እነዚህ አመፅ ቀስቃሾች በተያዙ ዕለት ማታውኑ በባህር ሐይል ካድሬዎች እርምጃ እንደተወሰደባቸው ሰማሁ። እርምጃ የተወሰደባቸው እኔም ሆንኩ የምፅዋ ባህር ኃይል አዛዥ ሳያውቅ፣ ወንጀላቸውን በህግ አግባብ ለማጣራት ለፍርድ ሳይቀርቡ ነበር። በሥልጣናቸው ያለፍርድ እርምጃ የወሰዱትን ጠርቼ ስጠይቃቸው፡-

"እኛም ከእርሶ እኩል ሥልጣንና ኃላፊነት አለን" ሲሉ መለሱልኝ። እጅግ በጣም ቅር አለኝ። እነዚህ ካድሬዎች በማዕረግ መኮንኖች አልነበሩም። በገዛ ሥልጣናቸው የፈፀሙት ወንጀል በመሆኑ ለበላይ ይገለፃል። በተጨማሪም ሌላም ወንጀል ፈፅመው ኖሮ ወደ አዲስ አበባ እንዲላኩ ተጠይቆ ይለካሉ። እነሱም በተራቸው እርምጃ ተወሰደባቸው።

በዚያ የአመፅ ወቅት በየቀኑ ሟችና ማታ ጦሩን ምሽጉ ድረስ በመሄድ የመጎብኘት ልምድ አዳብሬ ነበር። ጦሩን አበረታትቼ ቅሬታዎች ካሉ ምላሽ ሰጥቼ እመለሳለሁ። በአንድ አድማው እየተጋጋለ በሄደበት ዕለት የተለመደ ጉብኝት ሳደርግ ሴረኞቹ አድብተው ይጠብቁኝ ኖሯል። እንደ እድል ሆኖ ሳያዩኝ በመመለሴ ሴረኞቹ ተቆጭተው "አመለጡን" እያሉ ይነጋገራሉ። ይሄንን የሴራ ንግግር ያደመጡት የ72ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ አዛዥ ሌ/ኮ (ብ/ጄ) አለማየሁ ወልዱ ለእኔ ሳይነግሩኝ ቆይተው ሴረኞች ወታደሮች ተይዘው ጥፋተኛም ሆነው በመገኘታቸው በካድሬዎች ያለፍርድ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ከተደረገ በኋላ ጉዳዩን ለእኔ አብራርተው የነገሩኝ።

አመፁ ከተዳፈነና የአመፅ ቀስቃሾች ከተቀጡ በኋላ የተለመደው የምፅዋ ህይወት ተረጋግቶ ቀጠለ። ሙቀቱ ከማየሉ የተነሣ ራሱን እየሳተ የሚወድቀው ብዙ ነው። ለዚህ መፍትሔ በማፈላለግ ላይ ሳለን ድንገት አንድ ወሬ ይደርሰኛል። የተበላሸውን የበረዶ ፋብሪካ ሊጠግኑ የሚችሉ ጣሊያኖች ምፅዋ ውስጥ እንዳሉ። የምፅዋ ባህር ኃይል አዛዥ ካፕቴን መርሻ ጣሊያኖቹን እንዲያስተዋውቁኝ አድርጌ የበረዶ ማምረቻው እንዲጠገን ተዋዋልኩ። ጦሩም ሆነ የምፅዋ ህዝብ ከሙቀቱ ማየል የተነሣ በስቃይ ውስጥ ስለነበር በረዶ አስፈላጊ ነውና ፋብሪካው በፍጥነት እንዲጠን አስደረኩ። በረዶው ለጦሩም ሆነ ለነዋሪው ህዝብ ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ የህክምና ጣቢያዎችም ለህሙማኖቻቸው በረዶ አገኙ።

ከሃ፱ጭ ወደ ሰሜን ዕዝ

ስ/ሠፈሬን ሠከሳከሰ

ሻዕቢያ ባደረጋቸው ተከታታይ ማጥቃቶች ተጠቅቶ በቀላሉ ሊተካው የማይችለውን ኃይል አጥቷል። ከማጥቃት ወደ ቧልት ተሸጋግሮ ዘወትር በራዲዮው "እስረኞች እጠብቃለሁ" የሚል ጭውውትና ፈዝ ማስደመጥ ያዘ። በዚህ ፋታ መካከል ከየክፍሉ የተውጣጣውን 15ኛ ክፍለ ጦር የማቋቋም ሐሳብ ቀረበ።

ክፍለ ጦሩ የሚቋቋመው ተበትነው የነበሩ ጦሮችን እንደገና በየቀድሞ ክፍላቸው በማሰባሰብ ነው። ከ29ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ስፔሻል ፎርስ አባት ጦር ሻለቃና ከ11ኛ ሻለቃ በስተቀር ሁሉም ማለት ይቻላል የመበተን ዕጣ የደረሳቸው ናቸው። በጀት ያልተመደበለት ክፍለ ጦር ስለነበር አዲስ በጀት ተመደበለት። 15ኛ ክ/ጦርን በማቋቋም ላይ እያለሁ ሌ/ኮ (ሜ/ጀ) አበራ አበበ የ15ኛ ክፍለ ጦር አዛዥ ሆነው ተመደቡ። እኔ ደግሞ የኮሎኔልነት ማዕረግ ተሰጥቶኝ የሰሜን ዕዝ ምክትል አዛዥ ሆኜ ተሾምኩ። ማዕረጉ የዘገየና እድግ ስሜቴን ጉድቶት ስለነበር ቅንጣት ታህል ደስታ አልተሰማኘም። ለ6ወር ያህል ምንም አይነት የሥራ ብቃት ሪፖርት (ኤፍሽንሲ ሪፖርት) ሳይሞላልኝ፣ ቆይቶ መንፈሴ ከተንኮታኮተ በኋላ የተሰጠኝ የኮሎኔልነት ማዕረግ ነበርና።

በእኔ ዕዝ ሥር ሆኖ በመቋቋም ላይ የነበረውን 15ኛ ክ/ጦርን ከአየር ወለድ መቋቋም ጀምሮ የረጅም ዘመን ጓደኛዬ ለነበረው ለሌ/ኮ (ሜ/ጀ) አበራ አበበ አስረክቤ አዲሱን ሥራዬን ለመጀመር ወደ አስመራ ተነቃነቅሁ። አስመራም እንደደረስኩ ለጓደኛ አለቃዬ ለብ/ጀ መርዕድ ንጉሴ አመለከትኩ። በዕዙ መምሪያ መኮንኖችም ስለአጠቃላይ የኤርትራ ሁኔታ ገለፃ ተደረገልኝ። ስለጦሩ አሰላለፍና አሰፋፈር እንዲሁም ስለተቃዋሚዎች አሰላለፍ፣ ስለ አስተዳደርና ድርጅት ሁኔታ በየቢሮው እየሄድኩ ከተረዳሁ በኋላ ወደ ዕዙ አዛዥ ተመለስኩ። በመጨረሻም በብ/ጀ መርዕድ ንጉሴ ጠቅላላ ገለፃ ተደርጎልኝ በአስመራ ዙሪያ መደረግ ስላለበት ሁኔታ ተወያየን። የቀሩትን ልዩ ልዩ ክፍሎች ከጎበኘሁ በኋላ መደረግ ስለሚገባው ሁሉ ዕቅድ አወጣን።



ከቀኝ ወደ ግራ ብ/ጀ ሰሜላ በዳኔ የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ሜ/ጀ መርዕድ ንጉሴ የሰሜን ዕዝ አዛዥ እኔም የሰሜን ዕዝ ምክትል አዛዥ በአስበሳ ላይ

የዕቅዱ የመጀመሪያና ዋነኛ ግብ አስመራንና የሁለተኛው የአየር ምድብን ከሻዕቢያ ከባድ መሣሪያ ተኩስ ተዕዕኖ ማላቀቅ ነው። ሻዕቢያ ጀብሃ አስመራ ከተማን በቅርብ ርቀት ከበው የተቀመጡበትን ሁኔታ ተራ በተራ ማጥቃትና ይዞታችንን ማስፋት እንዳለብን ዕቅዱ ይገልፃል።

ዕቅዱ ወደተግባር መለወጥ የጀመረው በ18ኛ እግረኛ ብርጌድ ነበር። በሌ/ኮ (ኮ/ል) በቀለ ኃይሌ የሚመራው ይሄ ብርጌድ ከፀአዳ ክርስቲያን በመነሳት ይዞታውን አዲገብሩ አስከተባለችው መንደር ድረስ ቀስ በቀስ እያስፋፋ እንዲይዝ በዕዙ ዋና አዛዥ የተሰጠው ትዕዛዝ ያመላክታል። በትዕዛዙ መሠረት ሌ/ኮ በቀለ ኃይሌ ቆራጥና ማስተዋል የተሞላበት አመራር በመጠቀም ዕቅዱን አሳካ። ሌ/ኮሎኔሉ የማንንም ትዕዛዝ ሳይጠብቅ ለዕዙ ዋና አዛዥ ብቻ በምስጢር እያሳወቀ ተራ በተራ በማጥቃት ቁልፍና አደገኛ የሚባሉትን ነጥቦች በመያዝ የመጨረሻው ግቡ ከሆነው አዲገብሩ ገባ።

ዕቅዱን ወደተግባር ለመለወጥ የሚያስችለው ሁለተኛው ግዳጅ ለሌ/ኮ ውብቱ (ብ/ጀ) ፀጋዬ ተሰጠ። 28ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ከሁለተኛ አየር ምድብ ምዕራብ ካለችው የቅድስት ማሪያም ቤተክርስቲያን በመነሳት ቀስ በቀስ ሁኔታዎችን እያረጋገጠ የአዲተክላይ መንደርን አጥቅቶ እንዲይዝ የዕዙ ዋና አዛዥ ብ/ጀ መርዕድ ንጉሴ መመሪያና ትዕዛዝ ሰጡ። ከአስመራ ከተማና ከ2ኛው አየር ምድብ በስተምዕራብ



ከቀኝ ወደ ግራ ብ/ጀ ለሚሳ በዲሴ የኤርትራ ፖሊስ አዛዥ ሚ/ጀ መርዕድ ንጉሴ
የሶሜን ዕዝ አዛዥ እኔም የሶሜን ዕዝ ምክትል አዛዥ በአዲስ ላይ

የነበረው አስጊና ለጥቃት አጋላጭ የሆነ ኮረብታማ ቦታን በወገን ጦር እጅ ውስጥ ማስገባት ወሳኝ የሚባል ግብ ነበር። ሌሎ ውበቱ ፀጋዬ ባላቸው ልምድና ብልህ አመራር እየታገዙ ነጥብ በነጥብ በማጥቃት ወደፊት ገሰገሱ። ለዕዙ ዋና አዛዥ ለብ/ጀ መርዕድ ንጉሴ በምሥጢር እያሳወቁ በማጥቃት የመጨረሻ ግባቸውን የአዲ ተክላይን መንደር ያዙ።



የግይነፈ የመጠጥ ውሃ ግድብ ከጥበቃ ኃላፊው ሌሎ አየለ ሳህሌ ጋር


እነዚህ ሁለት ግቦች መሳካታቸው የአስመራ ከተማንና የ2ኛ አየር ምድብን ከክፍ መሣሪያ ተኩስ ሥጋት ገላግሏል። ከዚህ በተጨማሪም አስመራ ከአዲገብሩና ከአዲተክላይ በመነሳት ተመሳስለው ከተማ እየገቡ ግድያ ይፈፅሙ ከነበሩ ገዳይ ቡድኖች (ፈዳያን) ነፃ ወጥታለች። በምሥራት በኩል በሻዕቢያም ሆነ በጀብሃ ብዙ ችግር አልነበረም።

እንደ ሁለቱ ግቦች ሁሉ በሰሜንና በደቡብ ያሉትን ይዞታዎች የማስፋፋት ዕቅድ ቢሞክርም አልተሳካም። በተለይ በደቡብ ያለው የሻዕቢያ ይዞታ ለ2ኛ አየር ምድብ በጣም ቅርብ ከመሆኑ የተነሣ የከባድ መሣሪያ ተኩስ ሥጋት ነበረ። የሚገርመው ግን ሻዕቢያ በከባድ መሣሪያ 2ኛው የአየር መደብን ለማጥቃት በተደጋጋሚ ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል። ምክንያቱም በፀረ-ባትሪ ተኩስ የአፀፋ ጉዳት እንዳያደርስባቸው በስጋት በችኮላ ጠምደው ቶሎ ለማንሳት ሲሉ ያልተረጋጋ ተኩስ ስለሚያከናውኑ ነበር።

የሰሜነዲ ቃኘው ጦር ሠፈር የጥይት ግምጃ ቤት ቃጠሎ

ሻዕቢያ አስመራን ለመያዝ ማጥቃት ከመምከሩ በፊት የቃኘው ሻለቃ ጦር ሰፈር የቀላልና የከባድ መሣሪያ ጥይቶች ግምጃ ቤት በሻዕቢያ ደጋፊዎች በተጠመደ ፈንጂ አማካኝነት የፍንዳታ አደጋ ደረሰበት። የሚገርመው ደግሞ ፍንዳታው የደረሰው እነዚያ የቀላልና የከባድ መሣሪያዎች ጥይቶች በነሐሴ ወር 1970 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ በኮንቮይ ተጭነው ወደ ግምጃ ቤቱ በገቡበት ዕለት መሆኑ ነው።

ፍንዳታው የተከሰተው ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ገደማ ነበር። በወቅቱ ቦጥበቃ ላይ የነበረው ዘብ በፍንዳታው ምክንያት ተረብሾ እየጮኸ ወደ ለማይ በመተኮስ በአረፍት ላይ የነበረውን ጦር በሙሉ ቀስቅሷል። እኔና የጓደኛ አለቃዬ ብ/ጀ (ሚ/ጀ) መርእድ ንጉሤ በመደናገጥና ሻዕቢያ ይህን ሁሉ ጥበቃ አልፎ እንዴት ገባ በሚል በመገረም በፍጥነት ተነሳን። የእዙ አዛዥ ብ/ጀ (ሚ/ጀ) መርእድ ንጉሤ አንድ ሬድዮ ከነሰራተኛው ይዘው ጦሩን ለማረጋጋት በመኪና ከግቢው ሲወጡ እኔ ደግሞ ወደ ቢሮ እየሮጥኩ ሄድኩ። ጨለማ በመሆኑና ከመረበሼ የተነሳ ይመስለኛል በሌላ አቅጣጫ የቢሮ መግቢያ ነው ብዬ ስሄድ በመረብ መልክ በተሰራው የሽቦ አጥር ጋር አጋጭና እወድቃለሁ። መግቢያው በሌላ አቅጣጫ መሆኑን ትዝ ብሎኝ ወደዚያ ስሮጥ አንድ የቢ.ኤም. ጥይት በቢሮው ኮሪዶር ውስጥ ከግርግዳ ግርግዳ እየተገጨ ያልፋል። ሁለተኛ ድንጋጤ። ጥይቶች ቢቃጠሉው ሙቀት እየፈነዱ እንደ ርችት በአየር ላይ ያበራሉ። ወደ ላይ የመውጣት አቅማቸውን ጨርሰው ሲወርዱም በመኖሪያ ቤቶችና በቢሮዎች ጣሪያዎች ላይ ያርፋሉ ሌላ አስደንጋጭ ድምጽ ይሰጣሉ። እኔም ከአጥር ጋር ተጋጭቼ ለጥቂት ወደኋላ ቀረት ማለቴ እንጂ ያ! ከግርግዳ ግርግዳ እየተላጋ ይሄድ የነበረው የቢ.ኤም. ሃያ አንድ ጥይት የመጨረሻ የህልፈት ጽዋዬን ይሰጠኝ ነበር።



የማይነፈ የመጠጥ ውሃ ግድብ ኦፕቢቃ ኃላፊው ሌኮ አየለ ሳህሌ ጋር

ቢሮ እንደገባሁ ምንጊዜም የማልረሳው ጀግናው ሬድዮ ኦፐሬተራችን ባሻ አልዮም ሐሰን[15] ምንም አይነት መረበሽ ሳይታይበት በግንባር ያለውን ጦር እያነቃ "ትእዛዝ ተጠባበቁ!" እያለ መልእክት ሲያስተላልፍ ደረስኩ። እኔም በማንቃቱ ደስ ብሎኝ በግንባር ያለውን ጦር በሙሉ በሬድዮ በአንድ መስመር እንዲሰበሰባቸው የሚከተለውን መልእክት እንዲያስተላልፍ ነገርኩት።

"ፍንዳታው፣ እዚሁ ቃኘው ጦር ሰፈር ውስጥ ነው። አስመራ የተጠቃች መስሏችሁ የመከላከያ ወረዳችሁን ለቃችሁ እንዳትመጡ። አካባቢያችሁን ነቅታችሁ ጠብቁ።"

ጦሩ በተጨማሪም በብ/ጀ (ሚ/ጀ) መርእድ ንጉሤም በኩል እየተነገረው ስለነበር ወዲያው ተረጋጋ።

ፍንዳታው የአንዱ ፍንዳታ ሌላውን እያቀጣጠለ እስከ ጧት ድረስ ቆየ። እንደፍንዳታው ክብደት ይህን ያህል በሰው ሕይወት ላይ ጉዳት አላደረሰም። በንብረት ላይ ግን ጥይቶቹ የነበሩባቸውን ግምጃ ቤቶች እንዳልነበሩ ነው ያደረጋቸው። በፍንዳታው ኃይል አንድ የቢ.ኤም. 21 ጥይት ወደ ከተማ ተወርውሮ ሳይፈነዳ ጣሪያውን ጥሶ በመግባት ባልና ሚስትን አተኝቦት ሲገድል አንድ የበታች ሹም ደግሞ ይኼ ፊዩዝ ነው ብሎ በእግሩ ሊመታው ፈንድቶበት እግሩን ተቆርጧል።

በፍንዳታው ምክንያት የእዙ የመሐንዲስ ክፍል አዛዥ የነበሩትን ሻለቃ (ብ/ጀ) ኪዳኔን በጥርጣሬ ወስደው ያስሯቸዋል። ሲታሰሩ የእዙ ኃላፊዎች አናውቅም ነበር። የእዙ ዋና አዛዥ ብ/ጀ (ሚ/ጀ) መርእድ ንጉሤ ለስራ ጉዳይ ወደ አዲስ አበባ የሄዱበት ጊዜ ነበሩ የሻለቃ (ብ/ጀ) ኪዳኔ

[15] ባሻ አልዮም ሐሰን በእዙ አዛዥ ቢሮ የሚገኘውን የአስመራ ዙሪያንና ሰላሳውንም የጦሩን ሁኔታ መቆጣጠሪያ ሬድዮ ኃላፊ ነበር። ከእዙ መናኛ ኃላፊ የሚሰጠውን ትእዛዝና ሌሎችንም ተግባሮች በጥንቃቄ የሚያከናውን፣ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ከሬድዮው የማይለይ፣ ምክሩን እንኳ ከሬድዮው ላለመለየት ሲል በራሱ ፍላጐት አለበት ድረስ እየመጣበት የሚመገብ ትጉህ ሰው ነበር።

ባሻ አልዮም ሐሰን በምግሽ ሰዓቱ በአስመራ ዙሪያ ያሉትን የሬድዮ መናኛ ሰራተኞች ያነቃ፣ ያስተባብር ነበር። ከእዙ አዛዥ የሚሰጠውን ትእዛዝም እያስተላለፈ፣ ከጦሩ ክፍሎች የሚመጣውንም መልእክት እየተቀበለ ለሚመለከተው አካል ሲያቀርብ በሥራ ተጠምዶ ስለሚውል የእንቅልፍ ሠዓቱ ምን ጊዜ እንደሆነ አይታወቅም ነበር። በቃኘው ፍንዳታ ወቅት በፍንዳታው እየተመታ ባለው የእዙ ቢሮ ውስጥ ሳይረበሽና በድንጋጤ ሳይሸበር በግንባር ያለውን ጦር ቦታውን እንዳይለቅና ወደ ከተማም እንዳይመጣ የውስጥ ችግር መሆኑን እያስረዳ ጦሩን ደጋግሞ ያረጋጋ ነበር።

ባሻ አልዮም ሐሰን በአስመራ ዙሪያና በተለያዩ ግብረ ኃይሎች ባሉት ጦሮች እጅግ የተወደደና የተከበረ፣ ደህንኛ ለሰኖኘ የማይል፣ እንቅልፍ የማያሸንፈው ጠንካራና ብልህ የሬድዮ ሰራተኛ ነበር። ለአስመራ ዙሪያ ጥበቃ እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ጀግናም በመሆኑ በዘኩሉ በጣም አደንቀዋለሁ፣ በስራ ትጋቱም አክብረዋለሁ።

ባለቤት መጥተው የሻለቃ (ብ/ጀ) ኪዳኔን መታሰር የነገሩኝ። እኔም ማን እንዳሰራቸው ስጠይቅ የወታደር ፖሊሱ አዛዥ "በፈንጂው ምክንያት ተጠርጥረው ነው" አለኝ። "ሳይጣራ ሰው አታስቀይሙ፣ ይፈታ" አልኩ። ሻለቃው ግን አልተፈቱም። "እሱ ቢያደርገው ኖሮ እዚህ አይኖኝም ነበር" በማለት አሁንም እንዲፈታ አዘዝኩ። "ትፈታ እንደሁ ፍታ! አለዛ አንተም ትታሰራለህ!" ስለው "የመከላከያ ሚኒስትሩ በጀነራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ትእዛዝ ነው እኮ የታሰሩት" አለኝ። ጀነራል ተስፋዬ ገብረኪዳን ዘንድም ደውዬ ስለሁኔታው ብጠይቅ "አንተን አያጮህም አርፈህ ተቀመጥ!" የሚል መልስ አገኘሁ። በሁኔታውም አዘንን።

ብ/ጀ (ሚ/ጀ) መርእድ ንጉሤ ከሄዱበት ከአዲስ አበባ ለስራ ጉዳይ ሲደውሱ ስለሁኔታው ተነጋገርን። ጉዳዩን ተከታትለው በኢ.ሠ.ፓ. አባልነታቸውም ሁኔታው እንዲጣራ አድርገው የሚፈቱበትን መንገድ እንዲፈልጉም አሳሰብኳቸው። ለጥቂት ጊዜ ቢጉላሉም ሁኔታው እንዲጣራ ተደርጉ ንፁህ ሆነው ተገኙ። እንዲያውም ከሻለቃነት ማእረግ እስከ ብርጋዴር ጀነራልነት ደርሰዋል።

ከፍንዳታው በኋላ በሬ ከአራጁ ይውላል እንደሚባለው የምጽዋው አመጽ ተከትሎኝ መጥቶ እንደሆን አላውቅም፣ እቃዎችን በምናሰባስብበት ማታ ጥቂት የበታች ሹሞች "አለቆቻችንን አስረን እርምጃ ብንወስድ አማካሪዎቻችን የመንግስት ትብብሩን ያቆሙብን ይሆን" በማለት እርምጃ ለመውሰድ ሲያስቡ ከመከላከላቸው አንዱ በጉዳዩ ስላላመነቱትና አደገኛ መሆኑን ተረድቶ ለ፲ አለቃ (ብ/ጀ) ግርማ አየለ የደርግ አባልና የሶሜን ዕዝ ፖለቲካ ሃላፊ ይነግራል። ታዲያ ሁኔታው ሲጣራ በማመናቸው የዕዙ አዛዥ ሳያውቁ እርምጃ እንደተወሰደባቸው ሰምቻለሁ። ያም ሆነ ይህ ፍንዳታውን የፈፀሙት ወንጀለኞች በኤርትራ ፖሊስ ያልተቋረጠና ብርቱ ክትትል ስለመያዝ ችለዋል።

ከፍንዳታው ስምንት ቀን በፊትም አንድ የጦሩ ንኡስ አባት የ፲ አለቃ በካድሬነት ተመልምለው ለጦሩ ከንኡስ አባትነት ወደ ካድሬነት በመለወጣቸው የቤተ ክህነት ካባቸውንና ልብሳቸውን እንዲሁም ማሳለሚያ መስቀላቸውንና መጽሐፍ ቅዱሳን ጨምሮ የተሰያዩ የሃይማኖትና የፀሎት መጽሐፎቻቸውን በሙሉ ለእዙ ፖለቲካ ኃላፊ ለአስር አለቃ (ብ/ጀ) ግርማ አየለ ይሰጡና ፖለቲካ መምሪያው ሙዚየም ውስጥ እንዲቀመጥ ያደርጋሉ። ለዚህ ውለታቸው መጋቢ ፱ አለቃነት ይሰጣቸዋል። ጓኛ አዘንን። መዚየሙ ከመሣሪያ ግምጃ ቤቱ ጋር የተያያዘ እንድ ሰፋ ያለ ክፍል ውስጥ ነበር።

ክስምንት ቀን በኋላ በፍንዳታው ወቅት አልባሳቱ፣ መጽሐፍቱ፣ መስቀሉ፣ በፊልም የተቀነባበረው የጦሩ ታሪክና ጽሁፎች እንዲሁም ፎቶግራፎች አብረው ይወድማሉ። ፎቶግራፎቹ በጥሩ ሁኔታ ታሪክን ለመፃፍ ቀደም ሲል የተዘጋጁ ነበሩ። ቁሱም (ካድሬውም) እግራቸውን ተሰብረው በጡረታ ተገልለዋል።

የሻዕቢያ ሰሥጠራን ሣጥቃትና ጠከሳከል

በሁለቱ አቅጣጫዎች ሻዕቢያን በመግፋት ይዞታችንን ካስፋፋን በኋላ ለረጅም ጊዜ ፀጥ ብሎ የነበረው የአስመራ ዙሪያ እንደነበር አልቀጠለም። ሰኔ 24 እና 25 ቀን 1970 ዓ.ም ሻዕቢያ በደቡብ አቅጣጫ የመጀመሪያውን ማጥቃት ሰነዘረ። ለአስመራና ለ2ኛው አየር ምድብ በጣም ቅርብ ለሆነው በአዲሹማ አቅጣጫ የጀመረው የሻዕቢያ ማጥቃት በኮ/ል (ሜ/ጀ) ሁሴን አህመድ የሚመራው ጦር አከሸፈው።

በዚህ የተናደደው ሻዕቢያ ከሁለት ቀን በኋላ በሰኔ 27 ሁለተኛ ቅርበት ባለው በሰሜን አቅጣጫ ሌላ ማጥቃት ሰነዘረ። በበለዛ፣ በአምባ ደርሆና በአዲንፋስ በኩል አስመራን ለመያዝ የታቀደበት ይሄ ማጥቃት በጠንካራ መከላከል ሊከሽፍ ችሏል።

ሻዕቢያ አስመራን ለመያዝ የአልሞት ባይ ተጋዳይ ማጥቃት የሚሰነዝረው ለአጠቃላይ ህልውናው ወሳኝ በመሆኑ ነበር። ምክንያቱም የምሥራቅ ዕዝ ከምሥራቁ ድል በኋላ 2ኛው አብዮታዊ ሠራዊት ተብሎ ፊቱን ወደሠሜን ያዞረበት ወቅት ነበር። የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት መቀሌና ጎንደር ከትቶ በስድስት ግብረ ኃይል በመቋቋም ሙሉ ትኩረቱን ኤርትራ ላይ አደረገ። የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በየአቅጣጫው መንቀሳቀስ ያለጋው የሻዕቢያ ጦር አስመራን ተቆጣጥሮ "የኤርትራን ዋና ከተማ ይዣለሁና እየተደረገብኝ ያለውን ወረራ አስቁሙልኝ" በማለት ለተባበሩት መንግሥታት ለማመልከት የራሱን ዝግጅት ይጀምራል። በእርግጥም የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት የኤርትራ ትኩረት ሻዕቢያ ላይ ሥጋት ቢያሳድር አይፈረድበትም። መቀሌና ጎንደር ላይ የከተቱትና የተቋቋሙት ስድስቱ የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት ግብረ ኃይሎችና ዕቅዳቸው ይሄን ይመስላል፦

1. 501 ግብረ ኃይል በኮ/ል (ሜ/ጀ) ረጋሳ ጂማ ከጎንደር በመነሣት በሁመራ የተከዜን ወንዝ አቋርጦ፣ ጋሉ ጅን ኡምሐጀር፣ ተሰኔይን፣ ሀይኮታን፣ ጉኚን በማለስ ባሬንቱ ገብቶ ከጀግናው 16ኛ ብርጌድና ከ502 ግብረ ኃይል ጋር መገናኘት። ከዚህ በኋላ 501 እና 502 ግብረ ኃይሎች 508 ግብረ ኃይል በመባል አቆርዳትንና ከረንን መያዝ፣ እንዲሁም አካባቢውን ከተቃዋሚዎች ማፅዳት፣
2. 502 ግብረ ኃይል በኮ/ል (ሜ/ጀ) አስራት ብሩ እየተመራ ከመቀሌ በመነሣት የተንቤንን መንገድ በመከተል፣ ተንቤንን ከተቆጣጠረና ካፀዳ በኋላ አክሱምን፣ አካባቢዋንና ሽሬን ማፅዳት። ከዚህ በኋላ በአዲግእሮ አድርጎ ሺራሮን፣ ባድሜንና የመረብን ወንዝ አቋርጦ ሽምበቆና ባሬንቱ መግባት። ከ501 ግብረ ኃይል ጋር ባሬንቱ ከተገናኘ በኋላ ሥማቸው ከስሞ 508 ግብረ ኃይል ተብለው በመጠራት አቆርዳትንና ከረንን መያዝ። አካባቢውንም ከተቃዋሚዎች ማፅዳት፣ ከዚህ በኋላ ኮ/ል ረጋሳ ጂማ 501 ግብረ ኃይልን ለኮ/ል አሥራት ብሩ አስረክበው ወደ ሌላ የሥራ ምድብ ይዛወራሉ
3. 503 ግብረ ኃይል በኮ/ል ካሣ ገብረማሪያም በመመራት በሦስት ንዑስ ግብረ ኃይሎች ይከፋፈላል። "ሀ"፣ "ለ" እና "መ" በሚል። ሞሀ" ንዑስ ግብረ ኃይ በኮ/ል ሰይፉ ወልዱ እየተመራ ከአድዋ በመነሣት ራማን፣ የመረብን ወንዝንና አካባቢውን ተቆጣጥሮ በአዲካላና መንደፈራ አድርጎ አስመራ ይገባል። የ"ለ" ንዑስ ግብረ ኃይል ደግሞ በኮ/ል (ብ/ጀ) ታረኩ አይኔ እየተመራ ኢንጡቾን፣ ያረና ማይአይኒን፣ ሐዘሞን፣ መረበትንና ደቀመሐሪን አልፎ የአስመራን መንገድ መክፈት። የ"መ" ግብረ ኃይል በበኩሉ በምዕዋው ጀግና በኮ/ል ኃይሉ ወ/ጊዮርጊስ እየተመራ ከአዲግራት በመነሳት አዲቀይሕ፣ ማይስራዋ፣ ሰገነይቲና ደቀምሐሬ በማቆራረጥ የአስመራ መንገዶችን መክፈትና አስመራ ከተማ መግባት፣
4. 504 ግብረ ኃይል ከሰሜን ዕዝ ዘመቻ መከንንነት በተቀየረው በኮ/ል (ሜ/ጀ) ቁምላቸው ደጀኔ እየተመራ የትግራይን ፀጥታ ማስከበር፣
5. 505 ግብረ ኃይል በኮ/ል (ሜ/ጀ) አበራ አበበ በመመራት የምዕዋን ከፊል ከተማ ዕዳጋን ተቆጣጥሮ፣ ለምዕዋ ህዝብ የውኃ አቅርቦት ምንጭ የሆነችውን ዶግአሊን ነፃ ማውጣት። በመቀጠል ማይአጣልን፣ ገሀቴላይን፣ ደንጉሉን፣ ጊንዳዕን፣ አምቲካላንና ነፋሲትን ከወንበዴ ነፃ በማድረግ የአስመራ ምዕዋን መንገድ መክፈት፣

6. 506 ግብረ ኃይል ቀደም ሲል ሰሜን ዕዝ የነበረው ብ/ጀ (ሜ/ጀ) መርዕድ ንጉሴ እየተመራ የአስመራ ከረንን መንገድ መክፈትና የከረን ከተማን መያዝ የሚል ግዳጅ ይሰጠዋል። በተጨማሪም በክ/ል ካሣ ገብረማሪያም የሚመራው 503 ግብረ ኃይል አስመራ እስከገባ ድረስ 506 ግብረ ኃይል አስመራን አጠናክሮ እንዲከላከል ይታዘዛል።

ይሄ የሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ሁሉን አቀፍ ይዘት ያስፈራው ሻዕቢያ ቀደም ሲል የተገለፁትን የሰኔ 24 እና 25 ቀን የማጥቃት ዘመቻ ይከፍታል። የማጥቃት ዘመቻው የአሥመራ ዙርያ ጥበቃ በሚመሩት በክ/ል ሁሴን አህመድ አመራር ቢከሽፍበትም ሻዕቢያዎች ተጠናክረው ስለመጡና ቀደም ሲልም በዚያ አካባቢ ጠንካራ ምሽግ ስለነበራቸው ሁላችንም ተረባርበን እንኳን ከይዞታቸው ልናርቃቸው አልቻልንም። ይህ በንዲህ እንዳለ ከሁለት ቀን በኋላ ሻዕቢያ አሁንም ሌላ የጥቃት ሙከራ ያካሂዳል። ይሄኛው ማጥቃት የአስመራን የአየር ሁኔታ ያገናዘበ ነበር። ወቅቱ አስመራና አካባቢዋ ላይ ከፍተኛ መሬት የያዘ ጉም የሚወርድበት ነበር። ሻዕቢያ ደግሞ እንደዚህ ያለ የአየር ጠባይ እየተጠቀመ ብዙ ጊዜ ስለሚያጠቃ ቅድመ ጥንቃቄ ተደርጎበት ነበር። ከዕዙ አዛዥ ጀምሮ እስከ ታች ያሉ መኮንኖች በመንቀሳቀስና በየምሽጉ በመሄድ ሁኔታዎችን አይተው የሳላው የሚጠናከርበትን አመቻችተውና መመሪያ ሰጥተው ነበር።

ሻዕቢያም በበኩሉ በአስመራ የሚገኙት የአገሩ ተወላጅ የሆኑት የአየር ጠባይ ተንባዮች ከሰኔ 27 ቀን 1970 ዓ.ም ጀምሮ አስመራ ከሳት ቀን በላይ በጉም እንደምትሸፈንና የሻዕቢያም ሃሳብ ሊሳካ እንደሚችል በማመን ይህንኑ መረጃ ለሻዕቢያ ሰጥተዉታል። ሻዕቢያም ባገኘው ጥሩ መረጃ ለመጠቀም ልክ የሚያጠቃበት አካባቢ በጉም በሚሸፍንበት ወቅት ማለትም ሰኔ 26 ቀን 1970 ዓ.ም በ14:00 (8) ሠዓት ላይ የከባድ መሣሪያ የማስተካከያ ተኩስ እየተኮሰ መመዘንብ ጀመረ። ይህም በሌ/ኮ (ክ/ል) በቃና አራርሶ የሚመራው የ83ኛ ሚሊሺያ ብርጌድ የመከላከያ ወረዳ በአምባ ደርሆር በበለዛና አዲነፋስ አቅጣጫ ነበር። በሌ/ኮ (ክ/ል) በቃና የሚመራው ጦር ሽለቢያ በአስመራ ደቡብ አዲ አውሽ ላይ ባጠቃበት ጊዜ ሽለብያ ከአምባድርሆና ከበለዛ ያለውን ጦር አንቀሳቅሶ አዲሀውሽ ያለውን ጦር በማጠናከር እንዳያጠቃ ለማድረግ ትዕዛዝ ተሰጥቶት መጠነኛ ማጥቃትን ሰንዝሮ ሳይለካለት በመቅረቱ ዳገታማ ቦታ ላይ መከላከያውን ሲያዘጋጅ ሜዳ ላይ ተኝቶ ስለነበረ አግረ መንገዳቸውንም እነሱን ለመምታት የሚደረግ ተኩስ ነበር።

ሻዕቢያ የምዝገባ ተኩስ ማድረጉ እንደተሰማ የክ/ጦሩን አዛዥ ኮ/ል ሁሴን አህመድን አስጠርቼ እምባደርሆ ሄድን። የእኔ ጥርጣሬ ተኩሱ ምናልባት በእምባደርሆና በበለዛ በኩል ያሉትን የመብራት ጀኔሬተሮች ለማበላሸት ይሆናል የሚል ነበር። እምባደርሆ ደርሰን የብርጌድ ትዕዛዝ መስጫ ውስጥ ገብተን ስናይ ሻዕቢያዎች ሊያጠቁ ማሰባቸውን ተገንዘብን። ሻዕቢያዎች ማጥቃታቸው ስለማይቀር ሜዳ ላይ የተኙት ዛሬውኑ ተነስተው ወደምሽጋቸው እንዲመለሱ፣ የሽቦ አጥሩንም መልሰው እንዲዘጉ ለብርጌድ አዛዡ ትዕዛዝ ይሰጠው ብዬ በመንገር ተመልሰን ወደ ጠቅላይ ሠፈራችን ሄድን።

እንደጠረጠርነውም ሆነ። ሰኔ 27 ሊነጋግ ሲል አጠቃ። አስመራ በቅርብ ርቀት እንኳን ለአይታ በሚያስቸግር አኳኋን በጉም ተሸፈነች። የሚያሳዝነው ወደ ምሽጉ እንዲመለስ የተነገረው ጦር እዚያው ሜዳ ላይ ነበር። የሻዕቢያን መቃረብ ለማየት እንኳን በማይችልበት ቦታ ላይ ሆኖ ድንገት በደረሰበት መጠቃት መከላከል ባለመቻሉ አፈገፈገ። ወደ ምሽጉ ተመልሶ ሊገባ የሚችልበትን ዕድል ሊያገኝ አልቻለም።

ማጥቃት የተሰነዘረባቸው ቦታዎች ከአስመራ ሰሜን የሚገኙ እምባደርሆ፣ የመብራት ከፍተኛ ጀነሬተሮች የሚገኙበት በለዛና አዲንፋስ የሚባሉ ለአስመራ ቅርበት ያላቸው ቦታዎች ነበሩ።

ከደረሱን መረጃዎች እንደተረዳነው ሁኔታዎች አስጊ ሆነው ታዩን። ስለዚህ እኔና የእዙ ዘመቻ መኮንን ኮ/ል (ሜ/ጀ) ቁምላቸው ደጀኔ እቦታው ድረስ በመሄድ አንዳንድ የመፍትሔ ትዕዛዞችን አስተላለፍን። ወደኋላ የሚያፈገፍጉትን በመመለስ ሌሎች ከባድ መሣሪያዎችን አስተባብረን በግምታዊና በአካባቢ ተኩስ እርዳታ እንዲሰጡ አደረግን።

የአየሩ ሁኔታ እየተባባሰ ከተጫጫነው ጉም በተጨማሪ ዝናብ መጣል ጀምሮ ነበር። እኔና ኮ/ል ቁምላቸው በኃይለኛ ዝናብ ውስጥ ለሦስት ሌሊትና ቀን ማጥቃቱን ለማክሸፍ ጥረት አደረግን። በዚያ ጉም በሸፈነው ኃይለኛ ዝናብ ውስጥ ጦሩ ከመከላከያ ምሽጉ ውጪ በዝናብ እየተመታ የማይታመን ጀብዱ ፈፅሞ ሻዕቢያን ወደ መሀል እንዳያልፍ አግዶ አቆመው።

በሁለተኛው ቀን ሌሊት በበለዘና በመብራት ኃይል አካባቢ ያሉት ሁኔታዎች በጣም አስጉን። በመሆኑም እኔና ኮ/ል ቁምላቸው ደጀኔ ሌሊቱኑ ወደሰሜን ዕዝ ቢሮ ሄድን። የእዙን አዛዥ ብ/ጀ መርዕድ ንጉሴንና የኤርትራን ክ/ሀገር የኢ.ሠ.ፓ ተጠሪን ሻለቃ (ሜ/ጀ) ውብሸት ደሴን አገኘናቸው። የሄድንበትን ጉዳይ በማስረዳት በሻለቃ (ኮ/ል) ተስፋዬ

አበሻ የሚመራውን የመጨረሻውን ተጠባባቂ የሻለቃ ጦር በበለዛ በኩል እንዲገባና የአባት ጦርን እንዲያጠናክር እንዲሁም ተቃዋሚውን እንዲመታ ጠየቅን። የዕዙ ዋና አዛዥ ሆኑ የክፍለ ሀገሩ የኢ.ሠ.ፓ ተጠሪ ስለተስማሙልን ለሻለቃ ተስፋዬ ትዕዛዝ ሰጠነው። ሻለቃ ተስፋዬ አበሻም ትዕዛዙን ተቀብሎ ጥንቃቄ በተሞላበት አስደናቂ ፍጥነትና ስልት ተጠቅሞ በመግባት የአባት ጦሩን ይዞታ አጠናከረ። ሁኔታዎችን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ባይቻልም የሻለቃ ተስፋዬ በማይታመን ፍጥነት መግባት ተኩሱ እንዲቀዘቅዝና ረገብ እንዲል አስቻለ።

በሦስተኛው ቀንም ውጊያው ቀጥሎ ነበር። አስመራን የሸፈነው ጉም መካከል በትንሹ ሰማዩን የምታሳይ ሽንቁር ተከሰተች። ይሄንን ክፍት ቦታ እንዳስተዋልኩ የአየር እርዳታ ለማግኘት ይቻል እንደሆነ ለማረጋገጥ ወደ ሁለተኛ አየር ምድብ አዛዥ ከኮል (ሜ/ጀ) አምሃ ደስታ ጋር በሬድዮ ግንኙነት ፈጠርኩ። ኮ/ል አምሀ ደስታ የእኔን ጥቆማ እንደሰሙ "በቅድሚያ እኔ መጥቼ ልየው" አሉ።

በእይታ አለመጥራት ምክንያት ለመነሳትና ለመርዳት ተቸግሮ የነበረው የአየር ኃይላችን በዚች ክፍተት ተጠቅሞ ይረዳን ይሆን? አስጨናቂ ጥያቄ ነበር።

ኮ/ል አምሀ ደስታ ጀታቸውን አስነስተው በመምጣት አካባቢውን ካዩ በኋላ "ይቻላል" የሚል ምላሽ ሰጡኝ። ወዲያውኑም የጠላትን ይዞታ መደብደብ እንደጀመሩ ጉም መግለጥ ጀመረ። ሌሎች ጀት አብራሪዎችን አየር ላይ እንዳሉ በመጥራት ድብደባውን አጠናክረው ቀጠሉ። ጉሙም ስለገለጠ ሻዕቢያ የሚሸሸግበት አጣ። አየር ኃይላችን በግላጭ ያገኘውን የሻዕቢያ ጦር እያሳደደ በመምታት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አደረጉ። አስመራ ከተማንም ከውድቀት ያዳኑት እነዚህ አኩሪ የአየር ኃይል ጀግኖቻችን ናቸው። ኮ/ል አምሐ ደስታ በጥያቄው መሠረት ሌሎችን መላክ ሲችሉ የቅድሚያ አደጋውን እራሳቸው መጋፈጣቸው እንዳደንቃቸው አስገድዶኛል።

በዚህ ዘመቻ መተኪያ የሌላቸው ብዙ ከፍተኞና መስመራዊ መኮንኖችን አጥተናል። ለጦሩ እርሾ የነበሩ ባለሌላ ማዕረጎችም ተሰውተዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሌ/ኮ ሽባባው ዘለቀና የ105 አባት ጦር አዛዥ ሻለቃ ቦጋለ ወ/ዮሀንስን ማንሳት ይቻላል። በሻለቃ ቦጋለ ይመሩ የነበሩት አባት ጦሮች ምድባቸው የበለዛን የመብራት ጀኔሬተሮች መጠበቅ ነበር። እነዚህ አባት ጦሮች አስመራን ለማዳን በተደረገው በዚህ የሞት ሽረት ውጊያ ከጥበቃ ቦታቸው አንዲት ሜትር እንኳን ሳያፈገፍጉ

ተፋልመዋል። የቆሰሉትም ሆነ የመስዋዕትነት ዕጣ የገጠማቸው አባት ጦሮች የተመቱት ግንባርና ደረታቸውን ብቻ ነበር። እነዚህ አባት ጦሮች ውስጥ ሲሸሹ ጀርባቸውን ተመትተው የቆሰሉ ወይም የሞቱ አልተገኙም። እጅግ የሚያኮራና ታሪክ የማይረሳው የጀግንነት ሙያ ሰርተው አልፈዋል። ለመጪው ትውልድም አኩሪ ምሳሌ ሆነዋል።

የዚህ አባት ጦር ሻለቃ አዛዥ የነበሩት ሻለቃ ቦጋለ ወ/ዮሐንስ በዚህ ውጊያ ቆስለው ብዙ ደም እየፈሰሳቸው እንዲገለሉ ቢጠየቁ አሻፈረኝ ይላሉ። "ጦሬን ትቼ አልሄድም። አገሬ እየደማች የእኔ መታከም ምንድነው? አገሬ ስትድን እኔም እድናለሁ" በማለት የማዋጋት ተግባራቸውን ይቀጥላሉ። ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ በማዋጋት ላይ ሳሉ በድጋሚ ይቆስላሉ። ሊያዋጉ ባለመቻላቸው አሁንም ተገድደው ሲገለሉ በተማፅኖ እንዲህ ማለታቸው ትዝ ይለኛል፦

"በኢትዮጵያ አምላክ! ይቺን አገር አድኗት!" ይሄ ተማፅኗቸው ከሀሊናችን የማይጠፋ መልዕክት ተክሎብናል። ብዙ ደም ፈሷቸዋል። ሆስፒታል ደርሰው አንድ ቀን ካደሩ በኋላ የጥበቃ ይዞታቸው የአለመደ ፈሩን ደስታ ሰምተው ከጥቂት ቆይታ በኋላ በመስዋዕትነት አልፈዋል።

አባት ጦሮች ለዚች አገር የደሙላትና የደከሙላት በአጭሩ ተገልያ የሚያበቃ አይደለም። ከአስመራ ውጭ በምዕዋ ግንባርም ፊታቸውን ሳይመለሱ አኩሪ ሙያዎችን ሰርተው ሲያልፉ የአይን ምስክራቸው ለመሆን ችያለሁ። በጀግናው በሌ/ኮ (ኮ/ል) ኃይሉ ወ/ጊዮርጊስ የተመራው አባት ጦር አባሎች በአዛዣቸው ቆራጥ አመራር እየታገዙ ለምፅዋ መዳን ሲወድቁ ተመልክቻለሁ። በአጠቃላይ በከተማም ሆነ ከከተማ ውጪ የነበሩት የአባት ጦር መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች በየተሰማሩበት ቦታ ሁሉ ግንባርና ደረታቸውን በመስጠት አኩሪ ሥራዎችን ሰርተዋል። ጀርባቸውን ለጠላት ሳያሳዩ የማይረሳ እና የማይዘነጋ ታሪክን ለቀሪው ትውልድ ትተው አልፈዋል። ምሳሌነታቸው ግሩም፣ ውጤታቸውም እጅግ የሚያኮራና ድንቅ ነበር።

***

ከሰኔ 27 እስከ 29 - 1970 ዓ.ም ድረስ በተደረገው የአስመራ ዙሪያ ውጊያ ሻዕቢያዎች ስልት በሌለው አኳኋን እንዲሸሹ በወገን ጦር ተገድደዋል። አንዳንድ ቦታ ላይ የተዘጋጀላቸውን ምግብ አጠናቀው ከመብላታቸው በፊት በድንገት ይዞታቸውን ለቀው እንዲሸሹ ተገድደዋል። ምግባቸው የተዘጋጀበትን ድስት ትተው ስለሄዱ በየድስቱ ውስጥ የተረፈ ምግብ ይሸተናል። ምግቡ ያልተሰመደ ሽታ ያለው

በመሆኑ ተጠግተን ስንመለከተው በአረቄ የተፈተፈተ ምግብ ሆኖ አግኝተነዋል። ለምን እንደዚህ እንደሚያደርጉ ስንጠይቅ፣ በውጊያ ወቅት ድፍረት እንዲሰጣቸው ብለው እንደሚያደርጉት ተነገርን። ከከተማ ብዙ የአረቄ መጠጦች ሲወጡ ገጠር ላለው ህዝብ እየመሰለን ፍተሻ ቦታዎች ላይ እናሳልፍ ነበር። ከዚህ በኋላ ግን አረቄ በገፍ እንዳይዘዋወር መቆጣጠር ጀመርን።

ሻዕቢያ ለአንድ ቀንም ቢሆን አስመራን ለመያዝ ሠፌ ዕድል የነበረው በዚህ ውጊያ ብቻ ነበር። በአስመራ ከተማ ምዕራብ በኩል ሻዕቢያ የሞከረው ማጥቃት የከሸፈው ሁለት የተጠናከሩ ብርጌዶች በመኖራቸው ነበር። በሌ/ኮ (ብ/ጀ) ውበቱ ፀጋዬ የሚመራው 28ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድና በሌ/ኮ (ኮ/ል) በቀለ ኃይሌ የሚመራው 18ኛ ብርጌድ ቦታው ተይዞ ስለነበር ጀብሃ ብቻውን ሳይደፍር ቀረ። ጀብሃ ከሻዕቢያ ጋር በቅንጅት እንዳይዋጋ ሁለቱ ባለመስማማታቸው ምክንያት ቀረ። በመሆኑም ሻዕቢያ ብቻውን ድል ለመጐናፀፍ ሲል ለማጥቃት በመሞከሩ ሳይሳካለት ቀርቷል።

***

ሰሜን ዕዝ አቅሙ በፈቀደ ሁሉ ባሬንቱን፣ አስመራን፣ አዲቀይሕንና ምዕዋን ሳያደፍር ለሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት አስረክቧል። በሰሜን ግንባር ከተደረቡለት ጦሮች ጋር በመሆን ከጀብሃና ከሻዕቢያ ጋር ለረጅም አመታት ሲፋለም የኖረው የጀግናው 2ኛ ክ/ጦርና በኋላም የሰሜን ዕዝ ውጤት ነው።

ከዚህ በኋላ ሰሜን ዕዝ 506 ግብረ ኃይል የሚል መጠሪያ አዲስ ሥም ተሰጠው። በመሆኑም ከሌሎቹ የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አባሎች ጋር በብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ ዕዝ ሥር ሆኖ እንዲሰራ ተወሰነ። በአዲሱ መጠሪያው 506 ግብረ ኃይል በሚል መልሶ መቋቋም አደረገ።

አንዳንድ ላጋጠሙ ችግሮች
በሰሜን ዕዝ በኩል የተወሰዱ ርምጃዎች

የሰሜን ዕዝ ም/አዛዥ በነበርኩበት ጊዜ ጦሩ በመከላከያ ወረዳ በምሽጉ ውስጥ ብዙ በመቆየቱ ምክንያት ይመስላል ሁለት ያጋጠሙ ችግሮችን አጥንተን ከመፍትሄ ሃሳብ ጋር እንድናቀርብ በእኔ በፀሐፊው ሰብሳቢነት፦

1. ሌ/ኮ (ብ/ጀ) ታጠቅ ታደሰ

2. ሌ/ኮ (ብ/ጀ) ከበደ ወ/ጻዲቅ
3. ሌ/ኮ (ብ/ጀ) ዶ/ር ጋጋ አልጀን

ከዕዙ አዛዥ ከብ/ጀ (ሚ/ጀ) መርዕድ ንጉሤ ትዕዛዝ ይሰጠናል። ምክንያቶቹም

1. ራስን በራስ ማቁሰል
2. የአገር ማበጥ ችግር ናቸው

የአገር መከላከያ ሚኒስቴር አንድን ጦር ሥጋት ካለበት አካባቢ ሥጋት ወደ ሌለበት እንዲሁም በተቃራኒውም ቢሆን እያዘዋወረ ለማሠራት በወቅቱ ከየአቅጣጫው ሥጋት ነበረበት። ሥጋት ባይኖርበትም አቅሙ ስለማይፈቅድለት አንድ ጦር በተመደበበት ቦታ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት ይገደድ ነበር። ጦሩም ከዚህ ለመገለል ሲል እንዲሁ ራሱን በራሱ ማቁሰል ጀመረ። ከጠላት ጋር ግጭት ተደርጎ ላይቆሰል ቢቀር እንኳ ግጭቱን ምክንያት በማድረግ ራስን በራስ የማቁሰል ሁኔታ በብዛት ያጋጥም ነበር። ድርጊቱ ከተነቃባቸው ደግሞ ከጦር ሜዳ እንደሸሹ እየተቆጠረ እርምጃ ስለሚወሰድባቸው የጦሩ ሞራል ክፉኛ ተነክቶ ነበር። እናም ለችግሩ መፍትሄ መፈለግ አለበት በሚል ነው እንቅስቃሴ የጀመርነው። ሁልጊዜ ችግሩን ለምድር ጦርና ለአገር መከላከያ ብቻ ከመተው ይልቅ ዕዙ በቅድሚያ የራሱን ጥረት ለምን አያደርግም በሚል ነበር።

የተመረጥነው ስለሁኔታው በጥልቀት ከተነጋገርን በኋላ ከጦር ሜዳ ራሳቸውን ለማግለል የሚገፋፋቸውን ምክንያት በማጥናትና በተጨማሪም መኮንኖችንና ባለሌላ ማዕረጎችን በማነጋገር ችግሩ፦

ሀ.

1. ወደ ሌላ ቦታ ሳይቀየሩ በመከላከያ ወረዳቸውና ምሽጋቸው ውስጥ ብዙ ዓመት በመቆየታቸውና በመሰላቸታቸው
2. የቤተሰብ ናፍቆት (በደብዳቤም ሆነ በስልክ ስለማይገናኙ)
3. የመዝናኛ ጊዜ ባለማግኘታቸው
4. ገንዘባቸውን አደጋ በሚደርስባቸው ጊዜ በተቃዋሚዎች እጅ ስለሚገባ፤ ለዘመድም ሊልኩ ባለመቻላቸው መሆኑን ተረዳን።

በዚህ ጥናታችንም መሠረት በዕዙ አቅም ሊፈጸም ይችላል በሚል የሚከተለውን የመፍትሄ አቀረብን፦

1. ጦሩ በተለያዩ ምክንያቶች ገንዘቡ በታቃዋሚዎች እጅ እንዳይገባ ከአሥመራ የንግድ ባንክ ጋር በመነጋገርና ባንኩም መከላከያ ወረዳ ድረስ በመሄድ በፈቃደኝነት ለእያንዳንዱ ወታደር የባንክ ደብተር እንዲከፍትለት
2. በየጊዜው አንድ ብርጌድ በየተራ ለአሥር ቀን ወደ አሥመራ በመሄድ እንደየፍላጎቱ መዝናናት የሚፈልግ እንዲዝናና፤ ቤተሰቡን በስልክ ወይ በቴሌግራም እንዲያገኝ፤ እንዲገናኝ ገንዘብ መላክ ሲፈልግም እንዲልክ ሁኔታዎችን ማመቻቸት
3. ብርጌዶች በየተራ ለዕረፍት አሥመራ በሚሄዱበት ጊዜ የማረፊያ ቦታና የምግብ ችግር እንዳይገጥማቸውም ምግብ እንዲዘጋጅላቸው ሃሳብ አቀረብን።

የበላይ አካልም ተጠይቆ በቀረበው ሃሳብ በመስማማቱ

1. በየጊዜው ከመከላከያ መስመር ለ10 ቀን አንዳንድ ብርጌድ ወደ አሥመራ እንዲሄድ፤ ሲመለስም ሌላ ብርጌድ እንዲላክ ተደረገ።
2. ጦሩ የማረፊያ ቦታ እንዳይቸግረው በአሥመራ ኤክስፓ 69 ተብሎ በሚጠራው ግቢ ውስጥ ማረፊያ ተዘጋጀለት። ምግብም እዚያው ግቢ እንዲዘጋጅለት ተደረገ።

ከዚህ በኋላ ራስን የማቁሰል ጉዳይ ጎልቶ አልታይም።

ለ.

የእግር ዕብጠትን በተመለከተም በሰፊው ከተነጋገርን በኋላ ጉዳዩ ሙያን የሚጠይቅ በመሆኑ ሌ/ኮ (ብ/ጀ) ዶ/ር ጋጋ አልጆ ከሌሎች የሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር በመነጋገር መፍትሔ እንዲያፈላልጉለት ተደረገ። አንድ ወታደር ያለ እንቅስቃሴ ምሽግ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሲቆይ የእግር እብጠት እንደሚያጋጥመው፤ ስለዚህ በየጊዜው እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለበት፤ የእግር እብጠት ካጋጠመውም መድሃኒቱ የባቄላና የአተር በቆልት መሆኑን ተረዳን። ይህንንም የበላይ አካል ተጠይቆ በማስመጣት ያንን እያዘጋጁ በመብላታቸው የዕብጠቱ ችግር በዚህ ሊገታ ችሏል።

የኤርትራን ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች መልሶ ስመያዝና በኤርትራ ሠላምን ስመፍጠር የተደረገ ዘመቻ

ማዕከላዊው መንግሥት የኦጋዴንን አካባቢ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አስተማማኝና የማያሰጋ ሆኖ ስላገኘው ፊቱን ወደ ኤርትራ አዞረ። የኤርትራን ችግር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት እንዲሁም መከራና ችግር ያልተለየውን የኤርትራ ሕዝብን ለመታደግ ባልተከፋፈለ ልብ ክፍለ ሀገሩ ላይ አትኩሯል። በዚህም መሠረት ከአንደኛ አብዮታዊ ሠራዊትና ከሌሎችም የመከላከያ ኃይሎች በማሰባሰብ "ሁለተኛ የአብዮታዊ ሠራዊት" በሚል ስያሜ ግዙፍ ኃይል አቋቋመ። የኤርትራን ችግር ይፈታል ብሎ ያመነበት ይዜንን ሠራዊት በግንቦት በ1970 ዓ.ም መቀሌና ጎንደር እንዲከት አደረገ። ጦሩ መቀሌና ጎንደር ተጠቃሉ መግባቱ ሲረጋገጥ ዘመቻው በሰኔ 1970 ዓ.ም እንደሚጀመር በሊቀመንበር መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ትዕዛዝ ተሰጠ።

በትዕዛዙ መሠረት ዘመቻውን ለመጀመር ጦሩ ከመቀሌና ከጎንደር ተንቀሳቅሶ መነሻ ነጥቡ ላይ ደርሶ ሰፈረ። መነሻ ነጥቡም አዲግራት፤ ኢንጪጮ፤ አድዋ፤ መረብ፤ ሽሬና ሁመራ ናቸው። መጪው ክረምት ከመግባቱ በፊት፤ የአየር እርዳታ ለማግኘት ምቹ በሆነበት በሰኔ ወር አጋማሽ አካባቢ ዘመቻው ተጀመረ። ቀደም ሲል እንደተጠቀመው "ሁለተኛው የአብዮታዊ ሠራዊት" በስድስት ግብረ ኃይሎች ተከፋፍሎ በዕቅዱ መሠረት ወደዘመቻ ገባ።

501 ግብረ ኃይል ጀግናውን የ3ኛ ክፍለ ጦርን አካትቶ በክ/ል (ሜ/ጀ) ረጋሳ ጂማ አዝማችነት የተያዘለትን ግብ ለመምታት ተንቀሳቀሰ። ከተመደበለት በተጨማሪ ኃይል፤ የመንገድ መሣሪያ ዶዘሮችና ግሬደሮች በመያዝ፤ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሆኖ ዘመቻውን ጀመረ። እጅግ ተበላሽቶ የነበረውን የጉንደር ሁመራ ጋሉጅን መንገድ እየሰራ ተጓዘ። በአካባቢው የነበሩትን የተቃዋሚ ኃይሎች እየመታ ተከዜን አቋርጦ ጋሉጅን፤ ተሰነይንና ሃይታከታን በማፅዳት ባሬንቱ ገባ። ባሬንቱ ውስጥ ከ502 ግብረ ኃይል ጋር ተገናኘ።

502 ግብረ ኃይል በክ/ል (ሜ/ጀ) አስራት ብሩ እየተመራ ባሬንቱ የገባው እንደ 501 ግብረ ኃይል ሁሉ ዕቅዱን በማሣካት ነበር። ከመቀሌ

በመነሳት በተምቤን፣ በሽሬ፣ በአዲዳዕሮ፣ በሽራሮ፣ በይርጋ (በባድሜ) አድርጎ የመረብን ወንዝ በመሻገር ሽንበቆንና አካባቢውን ከተቃዋሚዎች እያፀዳ ባሬንቱ ገብቶ ከ501 ግብረ ሃይል ጋር ተገናኘ። 502 ግብረ ኃይል በክረምቱ ምክንያት ብዙ ችግሮች ገጥመውትም እንቅስቃሴውን ቢያዘገዩበትም በእርጋታና በዘዴ ተወጥቶ ነው ባሬንቱ የገባው። እኔ ራሴ በክረምቱ ምክንያት በመረብ ውስጥ አንድ ታንክ የሰጠመ መሆኑን ተመልክቻለሁ።

501 እና 502 ግብረ ኃይሎች ባሬንቱ ላይ ሲገናኙ የተቀበላቸው የተቃዋሚ ኃይል አልነበረም። ለረጅም ጊዜ የባሬንቱን ከተማ ይዘ የሻዕቢያን ከባድ መሣሪያ ድብደባ በመቋቋም የቆየው ጀግናው 16ኛ ብርጌድ የፈጥኖ ደራሽ ሻለቃና የኩናማ ህዝብ ሠራዊት ነበር። ቀደም ሲል ከ8ኛ ብርጌድ ጋር አስፍቶ የያዘውን የመከላከያ ቦታ ሳይለቅ በመጠኑ አጥብቦ ተከታታይ ማጥቃት ተቋቁሞ ባሬንቱን ሳትያዝ አቆይቷታል። በሌ/ኮ ሰለሞን ወልዴ የሚመራው ጀግናው 16ኛ ብርጌድ ሆነ 8ኛ ብርጌድ ታሪክ የማይረሳቸው ባለውለታዎች ናቸው።

501 እና 502 ግብረ ኃይሎች ባሬንቱ ላይ ተጠቃለው 508 ግብረ ኃይል በመባል መቋቋም አደረጉ። በ2ኛው ምዕራፍ 508 ግብረ ሃይል በክ/ል (ሜ/ጀ) አስራት ብሩ አዝማችነት እየተመራ አቆርዳትን፣ አንገርኔን፣ አደርዲንና ሀጋዘን በማፅዳት ከረንን በመያዝ ግዳጁን ፈፀመ። ክ/ል ረጋሳ ጅማ 501 ግብረ ኃይልን ለክ/ል አስራት ብሩ አስረክበው ወደሌላ የሥራ ምድብ ተዛወሩ።

በተመሣሣይ 503 ግብረ ኃይል በክ/ል ካሣ ገብረማሪያም አዝማችነት እንደአመዳደቡ ሁሉ በሦስት ንዑስ ግብረ ኃይሎች ተከፍሎ ዘመቻውን አካሂዷል። ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" በክ/ል ሠይፉ ወልዴ፣ ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" በክ/ል ታሪኩ ዐይኔና ንዑስ ግብረ ኃይል "መ" በጀግናው በክ/ል ኃይሉ ወ/ጊዮርጊስ እየተመሩ ሦስቱም የመጨረሻ ግባቸው አስመራ ገብተዋል።

ንዑስ ግብረ ሀይል "ሀ" ከአድዋ በመነሳት በራማ አድርጎ የመረብን ወንዝ በመሻገር እንዳጊዮርጊስን፣ አዲኳላን፣ መንደፈራንና ደባርዋን ከተቃዋሚ በማፅዳትና በመያዝ አስመራ ገብቷል።

ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ"ም አንጢጮን፣ በዘትን፣ ዖረናን፣ ሐዘሞን፣ ኮአቲትን፣ ማይአይኒን መርበትንና ደቀመሐሪን ከተቃዋሚው አፅድቶ አስመራ ገብቷል። በተመሣሣይ ንዑስ ግብረ ኃይል "መ"

ከአዲግራት በመነሳት በዛላአንበሳ፣ በፎርቶ ካዶርና፣ በሰንአፌ፣ በአዲቀይህ፣ በማይለራዋ፣ በሰገነይቲንና በደቀመሀሪ አድርጎ አስመራ ገብቷል።

ከሦስቱም ንዑስ ግብረ ሃይሎች የንዑስ ግብረ ሃይል "መ" አዝማች የነበሩት የምፅዋው ጀግና የአባት ጦሩ ክ/ል ኃይሉ ወልደጊዮርጊስ ሰገነይቲ ላይ መኪናቸው ላትታይ በታለፈች ፈንጂ ተመትታ ለሚወዷትና ለረጅም ዘመን ላገለገሏት አገራቸው መስዋዕትነት ከፍለው አልፈዋል። ጦሩ በም/አዛዣቸውና በግብረ ኃይሉ አዛዥ በክ/ል ካሣ ገብረማሪያም እየተመራ ንቅናቄው ሳይገታ አስመራ ከተማ በድል ገብቷል።

ተቃዋሚ ኃይሎች የሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት ምት ሊቋቋሙ ባለመቻላቸው አስመራ ዙሪያ ተሰባስበው የማደናቀፍ ሥራ መሥራት ጀመሩ። ከአስመራ ቀጥላ 2ኛ ከተማ ወደሆነችው ወደከረንና ምዕራባዊ ቆላ፣ እንዲሁም ወደ ሰሜን ናቅፋ፣ አልጌናና ቃሮራ ጦሩ እንዳይዘምት በመስጋት ነው የማደናቀፊያ ተግባር የሚያከናውኑት። የባቡር ኃዲዶችን በመነቃቀል፣ ድልድዮችን በማፈራረስና "ፍፁም ሊበገር የማይችል" የተባለለትን ምሽግ መስራትና ማጠናከር ጀመሩ።

504 ግብረ ኃይል በክ/ል ቁምላቸው ደጀኔ እየተመራ ትግራይን ከሰርጎ ገቦች በመጠበቅና በማፅዳት የተሰጠውን ግዳጅ በአግባቡ ተወጥቷል።

በክ/ል አበራ አበበ አዝማችነት የሚመራው 505 ግብረ ኃይል እንዲሁ ከምፅዋ በመነሳት አስመራ ገብቶ ግዳጁን ተወጥቷል። ዶጋ አሌን፣ ማይአጣልን፣ ገሃቴ ላይን፣ ደንጎሎን፣ ጊንዳዕን፣ አምባትካላን፣ ነፋሲትንና ማይሐባርን ከተቃዋሚው አፅድቷል። ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሎ ያልተሰካውን የአስመራ ምፅዋን መንገድ በሁለት ቀን ውስጥ ከፍቶ "የተዘጋ ምዕራፍ" የተባለለትን ጉዳይ ቀይሮ አሳይቷል።

"የሰሜን ዕዝ" ይባል የነበረው 506 ግብረ ኃይል በብ/ጄ መርዕድ ንጉሴ አዛዥነት በእኔ ም/አዛዥነት የሚመራው ነው። ይሄ ግብረ ኃይል 503 እና 505 ግብረ ኃይሎች ተጠቃለው አስመራ አስኪገቡ ድረስ ከተማዋን ከጠላት ማጥቃት ሲከላከል የነበረ ነው። የሻዕቢያና የጀብሃ ጦሮች ከየአቅጣጫው በመሸሽ አስመራ አካባቢ ተሰባስበው ስለነበር ከተማዋ እንዳትያዝ ብርቱ ተጋድሎ አድርጓል። በመጨረሻም ሁለቱ ግብረ ኃይሎች አስመራ አስኪገቡ ከተማዋን የማከላከል ግዳጁን በአመርቂ ሁኔታ ተወጥቷል።

2ኛው አብዮታዊ ሠራዊት መረብን ተሻግሮ ድል በድል እየተጎናፀፈ መገስገሱን ያየው የሻዕቢያና የጀብሃ ጦር ተስፋ በመቁረጥ የወገንን ጦር የሚያዘገይ አነስተኛ ኃይል በየቦታው እየተወ አስመራ ዙሪያ ተሰበሰበ። ከከተማው ምዕራብ፣ ሰሜንና ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫዎች ተጠቃለው ምሽጋቸውን አጠናከሩ። ሀሳባቸው የከረንና የምፅዋ መንገድ እንዳይከፈት ነበር። በዚህም ወደምዕራብ ማለትም ወደከረን፣ ወደሰሜን ናቅፋና ቃሮራ የሚደረገው የማጥቃት ዘመቻ እንዳይሳካ ለማድረግ ነበር። በዚህ መንፈስ የከረንና የምፅዋን የባቡር ሐዲድ መስመር በማፈራረስ ምሽጋቸውን አጠናከረው ገነቡ።

እንደዚያም ሆኖ ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊትን አልገቱትም። ምሽጋቸውን በመደረማመስ አስመራና ባሬንቱ ገባ። ጀብሃና ሻዕቢያም አብዛኛውን ይዞታቸውን ለቀው ለሁለተኛ አብዮታዊ ሠራዊት አስረከቡ። በእነዚህ የማጥቃት ዘመቻዎች ጦሩ በነፃ አልተነቃነቀም። የፈራረሱ መንገዶችንና የተሰበሩ ድልድዮችን እየሰራ፣ የተጠመዱ ፈንጂዎችን እያፀዳና በውጊያም ብዙ መስዋዕትነት እየከፈለ ነው በድል ላይ ድል የተረማመደው።

የውጪ መንግስታት ሬዲዮኖችና ቴሌቪዥኖች አዘውትረው የሚያቀነቅኑት ተመሳሳይ ጉዳይ ነበራቸው። "ሻዕቢያ ታሪክ ይሰራባቸዋል" እያሉ አንዳንድ ከተሞችንና መንገዶችን መጠቆማቸው ነው። ከረን፣ አፍአበትና ምፅዋ ከሚጠቀሱት ከተሞች ውስጥ ናቸው። የምፅዋ ሻዕቢያ እና የአልጌና ቃሮራ መንገዶችም ሻዕቢያ ታሪክ የሚሠራባቸው ተብለው ይጠቆማሉ። የውጭ መንግሥታት መገናኛ ብዙሃን በልበሙሉነት እንዲህ ለማለት የቻሉት ከአንድ ታሪክ በመነሣት ነው። እሱም የእንግሊዝ ጦር[16] ከምሥራቅ ሱዳን ተነስቶ የጣሊያንን ጦር ከኤርትራ ለማስወጣት ሲሞክር ከረን ላይ ሲደርስ ለረጅም ቀናት የመከላከያ መስመሮቹን ሰብሮ ማለፍ ተስኖት ስለነበር ነው። እንግሊዞች ባለማወቃቸው እንጂ ከረንን ለመያዝ ፊት ለፊት መጋፈጥ አልነበረባቸውም። ከረንን ለመያዝ በስተቀኝ ወይም በስተግራ አስፍተው ከኋላ በኩል በመሄድ መከላከያ መስመሩን በቀላሉ ማጥቃት ይችሉ ነበር። በወቅቱ ጥሩ ካርታ አልነበረም። ወይም እንግሊዞችን ህዝቡ አልተባበራቸውም።

[16] ህንድ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስለነበረች በዚህ ግንባር ተሰልፈው እንደቅጠል የረገፉት የእንግሊዝ ጦር ህንዶች ነበሩ። መሪውም ጄኔራልኻላት ነበር።

ሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት ተጠናቆ አስመራና ባሬንቱ መግባቱ ከተረጋገጠ በኋላ የብሔራዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ እዙን ከመቀሌ ወደ አስመራ አዛወረ። ዘመቻውን በበላይ ለመቆጣጠርና ለመምራት እንዲያመች በሌ/ጄኔራል ተስፋዬ ገብረኪዳን (የአገር መከላከያ ሚኒስቴር) የሚመራው ይሄ መምሪያ ጠቅልሎ አስመራ ገባ።

የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ ዕዝን ወደ አስመራ እንዳዘዋወረ ቅድሚያ ትዕዛዙን ያስተላለፈው ለ506 ግብረኃይል ሆነ። ግብረ ኃይሉ "የሰሜን ዕዝ" ተብሎ ከሚጠራበት ጊዜ አንስቶ አስመራን፣ ምፅዋን፣ ባሬንቱንና አዲቀይህን ሳያስደፍር የቆየ ነበር። ይሁንና በአግባቡ ባልተጠናና እጅግም ባልታሰበበት ዕቅድ ግብረ ኃይሉ የተሟላ ኃይሉን ሳይዝ ምዕራብ በኩል የሚገኘውን የሻዕቢያና የጀብሃ መከላከያ ኃይል ሰብሮ በመውጣት የአስመራ ከረንን መንገድ እንዲከፍት ታዘዘ። ግብረ ኃይሉ ዕቅዱን ለማስፈፀም ያደረገው ሙከራ ባለመሳካቱ ቀረ።

አሁንም በመቀጠል ቀዳሚ መምሪያው ሌላ እቅድ አወጣ። የ506 ገሚስ ግብረ ኃይልና የ503 ንዑስ ግብረ ኃይል (ለ) በአንድነት እንዲያጠቁና ያልተሳካውን የአስመራ ከረን መንገድ እንዲከፍቱ ትዕዛዝ ወጣ። ትዕዛዙን ለማስፈፀም በዝግጅት ላይ ያለው የ503 ንዑስ ግብረ ኃይል (ለ) አንድ ብርጌድ ቦታውን ባለማወቅ የተነሣ ለመሰናዶ ከተሰጠው ቦታ በማለፍ ሻዕቢያ ይዞታ ውስጥ ይገባል። ብርጌዱ በተኩስ በመያዙ ማጥቃቱ ሊደረግ ከታቀደበት ቀን በፊት እንዲጀመር ተገደደ። ያሰበቂ መሰናዶ ድንገት የተጀመረው ማጥቃት እንደተፈለገው አልተሳካም። በሻዕቢያ ይዞታ ውስጥ ገብቶ የነበረው ጦር ግን በ506 ግብረ ኃይል የተኩስ ሽፋንና እርዳታ ከመደምሰስ ተረፎ ከገባበት ሊላቀቅ ችሏል።

የእነዚህ ዕቅዶች አለመሣካት በብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ ውስጥ የነበረውን አንድ ጉልህ ስህተት የሚያሳይ ነው። የቀዳሚ መምሪያው አንዳንድ ባለሥልጣኖች እነሱ ብቻ እንደሚያውቁ ማሰባቸው የችግሩ ዋነኛ ምክንያት ነበር። እነዚህ ባለሥልጣኖች ዕቅድ በሚያወጡበት ጊዜ አካባቢውን የሚያውቁና ጦሩን ይዘው የሚዘምቱ መኮንኖችን ባለማካተታቸው ለተደጋጋሚ ውድቀትና ክሽፈት ጦሩን አጋልጠውታል። ከላይ ለተጠቀሱት ሁለት ማጥቃቶች ብቻ ሣይሆን ወደፊት ለምገልፃቸው ውጊያዎች ድክመት ሁሉ ምክንያት ናቸው ብዬ አምናለሁ።

በምስክርነት መጽሐፍ መስተካከል ያለባቸው ግድፈቶች

በሽም/ተስፋዬ ርስቴ ግንቦት 2001 ምስክርነት በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ከገጽ 301 ጀምሮ ስለሁለተኛው አብዮታዊ ሠራዊት በተለይ ስለ 503 ግ/ኃይል ንዑስ ግ/ኃይሎች ሁሉም የተጻፈው ደራሲው የደህንነት መኮንን በመሆናቸው ከቦታው ላይ ባልነበሩ ሰዎች እየተነገራቸው የጻፉት ስለመሰለኝ በድጋሚ የሚታተም ከሆነ ለማስተካከል እንዲረዳ እንደሚከተለው ቢታረም።

1. በገጽ 302 ላይ እንደተገለጸው 507 የሚባል የለም 501 እና 502 ግ/ኃይሎች ባሬንቱ ላይ ከ 16ኛ ብርጌድ ይዞታ ላይ ከተገናኙ በኋላ በ508 ግ/ኃይል መጠሪያ ስም በሚጀ አሥራት ብሩ (ያኔ ኮ/ል) በመመራት ከረንን እንዲይዙ ነው ግዳጃቸው። የ501 ግ/ኃይል አዛዥ የነበሩት ኮ/ል በኋላ (ሚ/ጀ) ረጋሣ ጂማ ወደ ሌላ ሥራ ተዛውረ።
2. 504 ግ/ኃይል በኮ/ል በኋላ (ሚ/ጀ) ቁምላቸው ደጀኔ እየተመራ የትግራይን ፀጥታ እንዲያስከብር እንጂ ወደ አሥመራ እንዲንቀሳቀስ አልታዘዘም።
3. የ502 ግ/ኃይል ግዳጅ ከሽሬ እስከ ባሬንቱ ያለውን የተቃዋሚውን ኃይል እየደመሰሰ ሄዶ ከጀግኖቹ የ16ኛ ብርጌድ ከኤርትራ ፈጥኖ ደራሽ ሻለቃና ከሁናማ ሕዝባዊ ሠራዊት ጋር እንዲገናኝ እና ከዚያም ከጎንደር ከተነሳው በኮ/ል (ሚ/ጀ) ረጋሣ ጂማ ከሚመራው ከ501ኛ ግ/ኃይል ጋር ባሬንቱ ላይ ተገናኝተው 508 በመባል ወደ ከረን እንዲንቀሳቀሱ እንጂ ባሬንቱ ቀደም ብላ ከላይ በተጠቀሰው 16ኛ ብርጌድ ቁጥጥር ሥር ነበረች።
4. በገጽ 306 ላይ እንደተገለጸው ኮ/ል ገብረ ክርስቶስ ቡሊና ኮ/ል (ሚ/ጀ) ታረኩ ዓይኔ ደቀመዛሪ ላይ ተጣልተው ኮ/ል (ብ/ጀ) ታረኩ ዓይኔ በኮ/ል አስጢፋኖስ ተተኩ። ኮ/ል አስጢፋኖስም በኮ/ል ሲይፉ ተተኩና ዘመቻው ወደ ምጽዋ ቀጠለ ይላል። እኔ ሁለቱ መኮንኖች መጣላታቸውን አላውቅም ትክክለኛው ግን እኔ ቀደም ሲል የሰሜን ዕዝ ም/አዛዥ በኋላም ሰሜን ዕዝ 506 ግ/ ኃይል ሲባልም የ 506 ግ/ኃይል ም/ አዛዥ እንጂ ደቀመዛሪ ላይ ኮ/ል (ብ/ጀ) ታረኩን አልተካሁም።

ኮ/ል ሠይፉ ወልዱም እኔን አልተኩኝም። ኮ/ል (ብ/ጀ) ታረኩ ዓይኔም ደቀመዛሪ ላይ ማንም ሳይተካቸው የራሳቸውን ንዑስ ግ/ኃይል (ለ)ን ይዘው አስመራ ከገቡ በኋላ የአሥመራ ከረንን መንገድ ለመክፈት ከ 506 ግ/ኃይል ጋር ትዕዛዝ ተሰጥቷቸው በዘመቻ መምሪያው ስሁተት አንዱ ብርጌዳቸው ሻዕቢያ ይዞታ ውስጥ መግባቱና በተኩስ በመያዙ በቅድሚያ የከረንን መንገድ ለመክፈት ታቅዶ የነበረው እንዲሠረዝ ተደርጓል። ኮ/ል ሠይፉ ወልዱም የራሳቸውን የ503 ንዑስ ግ/ኃይል (ሀ)ን ይዘው በአድዋ ራማ መረብ እንዳ ጊዮርጊስ አዲኳላን መደፈራና ድባርዋ አድርገው አሥመራ ከገቡ በኋላ ንዑስ ግ/ኃይላቸውን ይዘው ከነኮ/ል ካሣ ገ/ማሪያም ጋር ለሌላ ግዳጅ ተሰማርተው በመስዋዕትነት አለፉ እንጂ የ503 ግ/ኃይል ንዑስ ግ/ኃይል (ለ)ን አላዘዙም።

የአሥመራ ከረንን መንገድ መክፈት

የአስመራ ከረንን መንገድ ለመክፈት ሁለት ያልተሳኩ ሙከራዎች ተደርገዋል። ከዚህ በኋላ የከረንን ከተማ በሁለት አቅጣጫ አጥቅቶ ለመያዝ የሚያስችል ዕቅድ ወጣ። በውጭ አገር ሬዲዮና ቴሌቪዥን ሲለፈፍላት የቆየችው ከረን፣ የተባለው እውነት ይሁን ሐሰት የሚረጋገጥበት ቀን ደረሰ። የውጭዎቹ መገናኛ ብዙሃን ትንታኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሥጋት መፍጠሩ አልቀረም። የከረን ዕቅድ ካልተሣካ ለሻዕቢያዎቹ የልብ ልበ እንደሚሰጥ አይጠረጠርም።

እንደ ቀድሞዎቹ የአሥመራ ከረን መንገድ ማስከፈት ዕቅድ ግብረ ኃይሎቹ አልተገለሉም። 508 እና 506 ግብረ ኃይል አዛዦችና መምሪያ መኮንኖች ባሉበት ቀዳሚ መምሪያው የዕቅድ ስብሰባ አካሄደ።

ሻዕቢያ ከረንን ከአሥመራ ቀጥሎ እንደ ሁለተኛ ዋና ከተማ ይቆጥራታል። በመሆኑም ከረንን የሚከላከለው የተሰባሰበው ጦር ከአሥመራ እንዳይወጣ በማድረግ ነው። ስለዚህ ሻዕቢያ ከከረን ግንባር ይልቅ ኃይሉን በአሥመራ ዙሪያ አጠናክሮ ይዞ ነበር። ከረን ላይ ከአሥመራ ዙሪያ ያነሰ ኃይል ያስቀመጠው የከረን ግንባር ለሚያጠቃ ጦር ለመከላከል ስለሚያመችም ጭምር ነው። የከረን መሬት አቀማመጥ አለመመቸቱ እንዳለ ሆኖ በጣሊያን ጊዜ የተሰሩት ምሽጎች ሻዕቢያም ስላጠናከራቸው የሚበገሩ አይሆኑም። በተለይ ከባሬንቱና ከአቆርዳት አቅጣጫ ለሚመጣ ጦር ምሽጎቹ ጥሩ የመከላከያ ዋሻዎች እንደሆኑ ሻዕቢያ ተማምኖባቸዋል።

በቀዳሚ መምሪያው ሰብሳቢነት የተካሄደው የዕቅድ ማውጣት ውይይት በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ባንስማማም ዕቅዱ ወጣ። ዘመቻው ህዳር 12 ቀን 1971 ዓ.ም እንዲጀመር ተወሰነ። የማጥቃቱ ቀን እስኪደርስ ለዕቅዱ የመጨረሻ ውሳኔ ጥናቱ እንዲቀጥል ስምምነት ላይ ተደረሰ።

በጥናቱ ላይ የ506 ግብረ ኃይል አዲያቆብና ህዘጋ በተባሉት ቦታዎች በኩል ሰብሮ ከወጣ በኋላ አቅጣጫውን ወደ ግራና ቀኝ በማዙር በስፋት ሻዕቢያና ጀብሃ ላይ ጥቃት መሰንዘር።[9] በጥቃቱ ከአሥመራ

አካባቢ አስለቅቆ ማፅዳትና ወደ ከረን አቅጣጫ መነቃነቅ። ከሀዘጋና፣ ከአምባ ደርሆ በመነሳት በውና ላዕላይና ታህታይ፣ በአጠአራሽ፣ በሸማ ንጉስ ታህታይና ላዕላይ፣ በትንሽዋ ደቀመሐሪ አድርጎ የመንገዱን ግራና ቀኝ በስፋት በማሰስ አዲተከለዛን ከያዘ በኋላ መልሶ መቋቋም በማድረግ በማግስቱ ወደ ከረን ለመቀጠል ሀሳብ ቀረበ።

ይህ ዕቅድ ሻዕቢያ ከሚደርስበት ጥቃት ሳያንሰራራከረንን ለመያዝ ከማስቻሉም በላይ የአሥመራን አካባቢ ለቆ በሚሸሸው የሻዕቢያና የጀብሃ ጦር ላይ የማሳደድ ውጊያ ለማድረግ የተመቸ ነበር። በዚህ ላይ የጠላት ጦር መሬት እንዳይዝና የጦሩን እንቅስቃሴ እንዳይገታ የሚያደርግ ፍጥነት ይኖረው ነበር። የ506 ግብረ ኃይል ይሄንን መንገድ የመረጠው በነሲብ ሳይሆን አካባቢውን ጠንቅቆ ስለሚያውቀው ነበር። አማካሪዎቻችን ግን የአሥመራ አካባቢ ከፀዳ በኋላ በአዲበደል በኩል ተንቀሳቅሰን አዲተከለዛን ላይ መልሶ መቋቋም አድርገን ወደ ከረን እንድናመራ ሃሳብ አቀረቡ። አዲበደልና አዲተከለዛን በጣም የተለያዩ አቅጣጫዎች ከመሆናቸውም በላይ በመካከላቸው እጅግ ሠፊና ሰበርባራ መሬት አለ። አካባቢው መንገድ የሌለውና ለተሽከርካሪም ሆነ ለታንክ አመቺ ባለመሆኑ ይታወቃል። በዚህም አዲተከለዛን ለመድረስ እንኳን ዕለቱን አምስት ቀንም አይበቃም። ታንኮችና በዛ ያሉ ድርጅት የጫኑ ተሽከርካሪዎች ስለነበሩን መንገድ የግድ መኖር ነበረበት። መንገድ እየሰሩ ለመሻገር እንኳን ቢታሰብ መንገድ መሥሪያ መሣሪያዎች አልነበሩንም፣ ቢኖሩም ከቦታው ሰበርባራነት የተነሳ ለጠላት ማጥቃት የተመቹና ውጊያውም በሽንፈት እዚያ ላይ ያበቃ ነበር። ብቻ ዕቅዱ ተንኮል ነበረበት።

ይሄ ሐሳብ እንዲሰረዝ 506 ግብረ ኃይል አጥብቆ ተከራከረ። ነገር ግን ምንም እንኳን መከራከሪያው በቂ ምክንያት ቢኖረውም የአብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያውና የ506 ግብረ ሃይል አማካሪዎች ሳይቀበሉት ቀሩ። የሚገርመው ቀዳሚ መምሪያው ሆነ አማካሪዎቻችን እኛ የምንከራከርበትን አካባቢ ፈፅመው አያውቁትም። ነገር ግን አማካሪዎቻችን በካርታ ንድፍ ብቻ በመመራት የእግር መንገዱን ለታንክና ለተሽከርካሪ አመቺ ነው በማለት ቀዳሚ መምሪያውን ለማሳመን ቻሉ። በዚህም የሻዕቢያን መከላከያ ሰብሮ ማለፍም ሆነ ተከታተይ ማጥቃቱ ቀዳሚ መምሪያውና አማካሪዎቹ በመረጡት አቅጣጫ እንዲሆን ተወሰነ። በዚህም በአዲበደል በኩል በመቀርካና በአንሰባ መንደሮች አድርጎ አዲተከለዛንን መያዝ የሚለው አጓጉል ዘመቻ በግዳጅ ተጫነብን።

በውሳኔው መሠረት የ506 ግብረ ኃይል አዛዥ ብ/ጄ መርዕድ ንጉሴ የሚመለከተንን መኮንኖች ስብሰባው የሥራ ድርሻችንን ሰጡን። ለሁለቱ ግብረ ኃይል አዛዦች ማለትም የንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" አዛዥ ኮ/ል ሁሴን አህመድና የጀግናው የንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" አዛዥ ሌ/ኮ (ብ/ጄ) ተስፋዬ ሀ/ማሪያም፣ መምሪያ መኮንኖችና እኔም የ506 ግብረ ኃይል ም/አዛዥ የሥራ ድርሻችንን ተቀበልን። ትዕዛዙ በሚሰጥበት ወቅትም የቀዳሚ መምሪያው ምክትል ኃላፊ ሜ/ጀ ኃይለጊዮርጊስ ሀ/ማሪያምና ረዳት ስታፎቻቸው ተገኝተው ተጨማሪ ማብራሪያና ገለፃ አድርገውልናል። ከዚህ በኋላ አጥቂ መስመር ላይ የተመደቡት የማጥቂያ መስመራቸውን በማጥናት ተዘጋጁ።

ማጥቃቱ ከመደረጉ አስቀድሞ ለአራትና ለአምስት ቀን ያህል የማዘናጊያ መድፎችና የአየር ጥቃቶች ድብደባ ተካሄደ። በእርግጥም የማጥቂያውን ሰዓትና ቀን ለማሳሳት የረዳ ዘዴ ነበር። ከምዕዋ ልምድ የተወሰደው ይሄ ማደናገሪያ በመጀመሪያው ቀን ድብዳባ በሬዲዮ በየት በኩል ማጥቃት እንደተጀመረ ሲጠያየቁ የነበሩት ሻዕቢያና ጀብሃ ሲደጋገም ተዉት። በዚህም "ልምዳቸው ነው" በማለት እንደተዘናጉ ገባን።

የጎዳር 11 ቀን 1971 ዓ.ም የአሥመራ ከረንን መንገድ ለመክፈትና ሠብሮ የማጥቃት ውጊያ ከመጀመሩ አንድ ቀን በፊት የቅስቀሳ ሙዚቃ ዝግጅት ቀረበ። የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በሆኑት በሻለቃ (ብ/ጄ) ገብረመስቀል አዝብጤ መሪነት የማዕከላዊ ዕዝ የኪነት ቡድን ዝግጅቱን ለጦሩ አቅርቧል። በእነ ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ፣ ብዙነሽ በቀለ፣ እሳቱ ተሰማ፣ ተፈራ ካሣ፣ ተዘራ ኃ/ሚካኤል፣ መሐሙድ አሕመድና ሌሎች ለዛ ባላቸው ዜማዎቻቸው ቅስቀሳ ካደረጉና የጦሩን የውጊያ መንፈስ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ካደረሱ በኋላ ተሰነባብተው ለሌላ ቅስቀሳ ወደ መንደፈራ አመሩ። የኪነት ቡድኑ መንደፈራ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው መንገድ ላይ በተጠመደ ፈንጂ መኪናው ተመትቶ መጠነኛ ጉዳት ደረሰበት። የኪነት ቡድኑ መሪ ሻለቃ ገብረመስቀል አዝብጤ፣ ጥላሁን ገሠሠና ሌሎችም ድምፃውያንና ተወዛዋዦች ቀላል የመቁሰል አደጋ ሲደርስባቸው አንዲት ልጅ ግን እግሯ በጣም ተጎድቶ ስለነበር ተቆርጣል። ጦሩ ይሄንን አደጋ በሰማ ጊዜ ደስታው ወደ ሐዘን ተለውጧል። ሁኔታው ጠንክሮ ለመዋጋት እልህ ውስጥ ከትቶት ነበር።

በማግስቱ በጎዳር 12 ቀን በ0530 (በ11 ሰዓት ተኩል) ሰዓት የቢ.ኤም 21፣ 122፣ 130፣ 76 ሚ.ሜ መድፎችና የቀጥታ ተኩስ ከባድ

መሣሪያዎች ከዚህ ቀደም ካከናወኑት ሦስት እጥፍ ድብደባ በማድረግ ቆዩ። ቀደም ባሉት የማዘናጊያ ተኩሶች በመዘገቧቸው ቦታዎች ላይ ነው ድብደባውን ያካሄዱት። ከዚያ በመቀጠል ሁለተኛው የአየር ምድብ ደግሞ ከጠዋቱ 12 ሰዓት አንስቶ ያልተቋረጠ የ15 ደቂቃ ድብደባ አካሄደ 506 ንኡስ ግብረ ኃይል "ሀ" እና "ለ" በታንክና ሜካናይዝድ ብርጌዶች መሪነት የንቅናቄ ተኩስ አደረጉ። በሻዕቢያ ጠንካራ ምሽግ ላይ በተሰነዘረው በዚህ ተኩስ ገና ከመጀመሪያው ጠላት መፍረክረክ ያዘ። እግረኛውና ታንከኛው ከምሽግ ምሽግ በመሸጋገር የሚሸሸውን የሻዕቢያና የጀብሃ ጦር እየጣለ ምንጊዜም ከሀሲና የማይጠፋ የማጥቃት ውጊያ ተደረገ። ጊዜ የወሰደው የሻዕቢያንና የጀብሃን ምሽግ ሰባብሮ ማለፍ ሳይሆን ምርኮኞችን ማሰባሰቡ ነበር።

የሻዕቢያ ምርኮኞችን የማሰባሰቡ ውጊያም በአምስት ሰዓት ተጠናቆ፣ አሳድዶ መምታቱ ቀጠለ። በዕቅዱ መሠረት ሁለቱም ንዑስ ግብረ ኃይሎች ወደ አዲበደል ተንቀሳቀሱ። እግረኛው በጨበጣ ውጊያ ተቀላቅሎ ተፋልሞ ስለነበር በወገን በኩል የተከፈለው መስዋዕትነት ቀላል አልነበረም።

ኅዳር 11 ቀን ከአሥመራ ዙሪያ ጦርነት አንድ ቀን ቀደም ብሎ በሌ/ኮ (ሚ/ጀ) አበራ አበበ የተመራው 505 ግብረ ኃይል የምዕዋ አሥመራን መንገድ አጥቅቶ በመክፈት አሥመራ ገባ። ፍጥነቱና ውጤቱ ያልተጠበቀ፣ የሚያስደንቅና የሚያኮራ ነበር። 506 ግብረ ኃይልም "የማይደፈር" የተባለውን የሻዕቢያና የጀብሃ ምሽጎች በማጥቃት ሰብሮ ከወጣና አካባቢውን ካፀዳ በኋላ ምርኮኞችን ለአሥመራ ዙሪያ ጥበቃ አስረክቦ የማሳደድ ውጊያውን በተወሰነው በአዲበደል አቅጣጫ ቀጠለ።

የማሳደድ ውጊያው አዲበደል ላይ ሲደርስ የተፈራው ማነቆ መጣ። መንገዱ ጠባብና የእግር መንገድ ብቻ በመሆኑ በስፋት እያሰሱ ለመሄድ አዳገተ። ለታንክና ድርጅት ለጫኑ ተሽከርካሪዎች የማያመች ሆነ። ይታሰፍ ቢባል እንኳን መንገድ እየተሠራ በመሆኑ ረዘም ያለ ጊዜ የሚወስድ፣ በአጭር ጊዜ አዲተከለዛን ለመድረስ የማያመች መሆኑ ተረጋገጠ። ሁኔታዎችን ለማስተካከልና ለማመቻቸት እንዲቻል የእንቅስቃሴ ወረዳውን መቃኘት ግድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ። በዚህም መሠረት ከ2ኛው አየር ምድብ ለቅኝት ሔሊኮፕተር ተጠይቆ በኮ/ል ግርማ ደምሴ የምትበር አሉዌት ሄሊኮፕተር ተላከችልን።

በሄሊኮፕተሯ የ506 ግብረ ኃይል አዛዥ ብ/ጀ መርዕድ ንጉሴና የግብረ ኃይሉ አማካሪ ጀርጅያዊው ኮ/ል ኤድዋርድ ከአስተርጓሚያቸው

ጋር ተሳፍረው ቅኝቱን ጀመሩ። ይሁንና በሽሽት ላይ ከነበሩ የጠላት ጦር አባሎች በተተኮሰ ጥይት ሄሊኮፕተሯ ተመታች። ሄሊኮፕተሯ ባትጎዳም በውስጧ ያሉት ኮ/ል ኤድዋርድ በፅኑ ቆሰሉ። ሎሌቹ ተሳፋሪዎች ምንም ጉዳት አልደረሰባቸውም። የግብረ ኃይሉ አማካሪ ግን ለህክምና አሥመራ ቢደርሱም ሊድኑ ባለመቻላቸው መስዋዕት ሆነው ዓለማቀፋዊ ግዴታቸውን ተወጥተዋል።

በቅኝቱ አንድ ድምዳሜ ላይ ተደርሶ ነበር። አካባቢው ለተሸከርካሪ ሆነ ለታንኮች ምቹ ያለመሆኑ ከመረጋገጡም በላይ እንደተሰጋው የበለጠ ውጤት የሚገኝበት የማጥቃቱን ፍጥነት አዘግይቶታል። በመሆኑም የዕለቱ አዳር አዲበደል ላይ ሆኖ በማግስቱ የማጥቃት ፍጥነቱ ስለዘገየ ቀደም ሲል የ506 ግብረ ኃይል አቅዶት የነበረው እቅድ እንደገና መተግበር ግድ ሆነ። የተያዘው ዕቅድም ተለወጠ።

በተለወጠው ዕቅድ መሠረትም በጀግናው በሌ/ኮ (ብ/ጀ) ተስፋዬ ሀ/ማሪያም የሚመራው የ506 ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" አንድ ግዳጅ ተሰጠው። በእግረኛ ብቻ ወደ ሽማ ንጉስ ታህታይና ላዕላይ መንደሮች በመሄድ ወንዙን አቋርጦ እጅግ ከባዱንና አስቸጋሪውን ዳገት ወጥቶ እንዲይዝ ትዕዛዝ ተሰጠው። እዚያ አዳር ካደረገ በኋላ በቀጣዩ ቀን በእግረኛ ብቻ የአሥመራ አዲተከለዛንን መንገድ ግራና ቀኝ በስፋት እያሰሰ አዲተከለዛን እንዲገባ።

በተመሣሣይ በኮ/ል (ሚ/ጀ) ሁሴን አህመድ የሚመራው ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" ደግሞ የግብረ ኃይሉን ድርጅት የያዙ ተሽከርካሪዎችና ታንኮች ይዞ ወደ ሀዘጋና አሥመራ እንዲመለስ። የአሥመራ አዲተከለዛን መንገድ ከፈንጂ እያፀዳ በአስመራ እና በአዲተከለዛን መካከል ከምትገኘው ትንሿ ደቀመሃሪ ላይ አዳር እንዲያደርግ ተወሰነ። እንደታቀደው ተከናውኖ ዋለ።

ኅዳር 14 ሁለቱም ንዑስ ግብረ ኃይሎች አዳር ካደረጉበት በመነሳት የተሰጣቸውን ግብ ተከትለው ተጓዙ። ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" የመንገዱን ግራና ቀኝ በስፋት እያሰሰ፣ አካባቢውን ከወንበዴ እያፀዳ መጥቶ አዲተክለዛን ለመግባት 10 ኪሎ ሜትር ሲቀረው አዳር አደረገ። ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" በበኩሉ እንዳቀደው ብዙ የተቀበሩ ፈንጂዎችን አላገኘም። ምክንያቱም ሻዕቢያ መንገዱን ይጠቀምበት ስለነበር ነው። ከዚሁ ሌላ ድንገት ስለተመታና የሚሸሸውም በአየር ክትትል ግዳይ ስለደረሰበት በየመንገዱ ፈንጂ ለመቅበር ጊዜ አላገኘም። በመሆኑም ንዑስ

ግብረ ኃይል "ሀ" ካቀደው በመፍጠን በ1700 (11) ሰዓት ከግብረ ኃይል አዛዥ ጋር አብሮ አዲተከለዛን ይደርሳል። እንደደረሰም መልሶ መቋቋም ሳያደርግ የብሔራዊ አብዮታዊ ዘቻ ቀዳሚ መምሪያ ዘመቻ መኮንን ኮ/ል ገብረክርስቶስ ቡሊ እና የመምሪያው አማካሪ ጄኔራል ሾሮሆቭ ከቀኑ በ11 ሰዓት ላይ በሄሊኮፕተር ይመጣሉ። ብ/ጄ መርዕድ ንጉሴን አግኝተውም "የ508 ግብረ ሃይል አደርዴ ላይ ተይዟልና በፍጥነት ወደ ከረን ቀጥሉ" የሚል ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ።

"አሁን ሰዓቱ እየመሸ ነው። ጦሩም ገና ተሰባስቦ አልገባም። መልሶ መቋቋም አላደረግንም" በማለት ብ/ጄኔራል መርዕድ ንጉሴ ትዕዛዙ ትክክል አለመሆኑን ለማስረዳት ይጥራሉ። "ደግሞም'ኮ አደርዴ ሰ508 ግብረ ኃይል ማጥቃት ቀላል እንጂ አስቸጋሪ አይደለም። ሁለት ግብረ ኃይል ይዞ አስቸጋሪ ቢሆንበት እንኳ ከ11 ሰዓት በኋላ የመከላከያ ወረዳን አዘጋጅቶ አዳር ማድረግ እንጂ ከመሸ በማያውቁት ወረዳ መንቀሳቀስን የአገር መከላከያ ደንባችን ይከለክላል" ሲሉ አስተያየታቸውን ይገልፃሉ። እንኳን ከረን ኢላበረድም እንደማይቻል ይነግሯቸዋል።

የቀዳሚ መምሪያው ዘመቻ መኮንን ኮ/ል ገብረክርስቶስና አማካሪው ጄ ቮሮሆቭ የሰጡት ምላሽ የሚያናድድና ቅሬታ የሚፈጥር ነበር። "ፈርታችሁ እንደሆነ እኛ የመጀመሪያው ታንክ ላይ እንወጣለን" ነበር ያሉት። እርግጠኛ ነኝ ኑ ውጡና እንሂድ ቢሏቸው አያደርጉትም።

የግብረ ኃይሉ ዋና አዛዥ የሰዎቹ ንግግር ቢያናድዳቸውም በትዕግስት ለመመለስ ሞክሩ።

ግን "ወታደራዊ ትዕዛዝ ነው!" ተባሉ።

ትዕዛዙ የወጣው በቂም በቀልነት መሆኑን በኋላ ተረድተናል። የዘመቻው ጠቅላላ ዕቅድ ሲወጣ አማካሪዎቹና የቀዳሚ መምሪያው መኮንኖች ያቀረቡት ሐሳብ ትክክል አለመሆኑን አስረድተን በግፊት ቢፀድቅም በተግባር ተረጋግጦ በመለወጡ ቅሬታ አድሮባቸው ነው ለመጉዳት "ወታደራዊ ትዕዛዙን" የሰጡት።

በንግግሩ ላይ የነበሩት ኮ/ል ሁሴን አህመድ በጣም በመናደድ ከነሱ የተሻሉና ግዳጃቸውንም ለመወጣት የሚችሉ መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ "ወታደራዊ ትዕዛዙን" ለማስፈፀም መልሶ መቋቋም ያላደረገውን ጦራቸውን ለእንቅስቃሴ እንዲዘጋጅ አዘዙ። ሰብርጌድ አዛዦችም የንቅናቄ ትእዛዝን በመስጠት አመሻሽ ላይ ጉዞአቸውን ወደ ከረን ቀጠሉ።

በእቅዱ መሰረት ሁለቱም ንዑስ ግብረ ኃይሎች አዲተከለዛን ደርሰው መልሶ መቋቋም ቢደረግ ኖሮ ሁሉም የተስተካከለ በሆነ ነበር። ምክንያቱም በኤርትራ ክፍለ አገር ለረዥም ጊዜ የቆዩና ቦታዎችንም ደህና አድርገው የሚያውቁ መኮንኖችና አባሎች በንዑስ ግብረ ኃይል «ለ» ውስጥ ተካተው ስለነበር ነው። እንዲቀድም ተወስኖና ታቅዶ የነበረውም ንዑስ ግብረ ኃይል «ለ» ነበር። ሆኖም የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ በመደናገጥ፣ ሁኔታዎችን በትክክል ካለማወቅና ካለማጤን የተነሳ ሳያገናዝብና ሳያረጋግጥ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ንዑስ ግብረ ኃይል «ሀ» እንዲንቀሳቀስ ተደረገ።

ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" በምሽት ከመነሳቱም በላይ አዛዡ ቦታውን ጠንቅቆ አያውቀውም ነበር። በጨለማውም ምክንያትም አደገኛ የጠላት ወረዳና ቁልፍ የሆኑ መሬቶች አለመታየታቸው ሌላ ችግር ሆነ። ግንኙነት እንዳይቋረጥና የአርስ በርስ መረዳዳት እንዲኖር በማሰብ ንዑስ ግብረ ኃይሉ መንገዱን ተከትሎ እንዲሄድ ተወስኖ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ኤላበርድ ደረሰ። መድረሱንና እዚያው አዳር ማድረጉን ገልፆ ካመለከተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ግንኙነት ተቋረጠ። በመካከላችን ትልቅ ድንጋጤ ተፈጠረ። የግብረ ኃይሉ አዛዥም ሆነ እኔ ከመጠን በላይ ተረበሽን።

ምክትል አዛዥ እንደመሆኔ ያለአግባብ የተንቀሳቀሰውን ድርጅት እንዳይንቀሳቀስ ማስተባበር ነበረብኝ። የቀዳሚ መምሪያ እንዲህ ያለ ያልተገናዘበና ያልተጣራ ትዕዛዝ ይሰጣል ብዬ ስላልጠረጠርኩኝ ከንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" ጋር ብዙ ቆየሁ። የአስመራ አዲተከለዛንን መንገድ በደንብ ስለማውቀው ንዑስ ግብረ ኃይሉን ከኋላ፣ ከግራና ከቀኝ እየገባሁና እያየሁ ስከታተል እንደዚህ ያለ ስህተት ተፈፀመ። ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" አዲተከለዛን አጠገብ መድረሱን ካረጋገጥኩ በኋላ ነበር ቀጥታ ወደ አዲተክለዛን አምርቼ የተወሰነውን ብ/ጄ መርዕድ ንጉሴ የተነገረኝ። ማስተባበሩ የእኔ ድርሻ ቢሆንም በዚህ ምክንያት ማድረግ የሚገባኝን አላደረኩም።

ኮ/ል ሁሴን አህመድ ንዑስ ግብረ ኃይሉን ይዞ በተንቀሳቀሰበት ጊዜ በግብረ ኃይሉ የድርጅት መኮንን ተወካይ አንድ ትልቅ ስህተት ተፈፅሞ ነበር። በዚህም አደገኛ የምሽት እንቅስቃሴ የሁለቱም ንዑስ ግብረ ኃይሎች ከባድ መሣሪያዎችና የድርጅት ተሽከርካሪዎች አብረው እንዲሄዱ መፍቀድ አልነበረበትም። መድፎች፣ ታንኮች፣ ቢ.ኤም 21 መድፎች አብረው ተንቀሳቀሱ። ያለ ትዕዛዝ የተንቀሳቀሱት

ተሽከርካሪዎችና መድፎች ኤላበርድ ከደረሱ በኋላ ወደፊትም ወደኋላም ማለት የማይችሉት ሽጥ ውስጥ ተሰግስገው ቆሙ። ይህ አጋጣሚ ከጥቂቶቹ መድፎች ውጭ ሊረዱ በማይችሉበት ሁኔታ ነበር የቆሙት።

ከዚህ በተጨማሪ ንዑስ ግብረ ኃይሉ የሰው ኃይል ተቀንሶበት ነበር። በተዋጊነቱ የታወቀው የ84ኛ ሚሊሺያ ብርጌድ በሌላ ብርጌድ እስኪቀየር ድረስ አዲተከለዛን ላይ እንዲቆይ ተወስኖ ነበር። ሻዕቢያ ከኋላ እንዳያጠቃ ሌላ ኃይል ተቀንሶበት ስለነበር ንዑስ ግብረ ኃይሉ ባልተሟላ ኃይል ነበር የተንቀሳቀሰው።

ኤላብረድ በተራራ የተከበበች ትንሽ መንደር ናት። ደናዳይ በተባለ ኢጣሊያዊ ባለሐብት የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእርሻና የወተት ላሞች ርቢ ይከናወንበታል። ሻዕቢያ ኤላብረድ እንደገባ መጠነኛ እረፍት ለማድረግና ጦሩን ለመመገብ ይወስናል። የሻዕቢያ ግምት ኃይሉን ከአሥመራ ዙሪያ ስላነቃነቀ ጦሩ የአሥመራ መከላከያውን ሊቆ አይከተለንም የሚል የተሣሣተ ነበር። በዚህም ኤላበረድ ላይ ያገኙትን ፍራፍሬ እየመገቡ፣ ከብቱን እያረዱ መመገብ ይጀምራሉ። በዚህ መካከል ከአሥመራ አይወጣም ብሎ የገመተው ጦር ድንገት ስለደረሰበት በመደናገጥ ጨለማውን ተገን አድርጎ ቦታ ቦታውን ለመያዝ ይጣደፋል። ከጦሩ በላይ ኤላበርድን ጠንቅቆ የሚያውቀው ሻዕቢያ አካባቢውን ለቆ ጉዳት ለማድረስ የሚያስችሉትን ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በመያዝ አደረ።

በጎዳር 15 ሊነጋጋ ሲል ሻዕቢያ በጦሩ ላይ የከባድ መሣሪያ፣ የመትረየስና የቀላል መሣሪያዎች ተኩስ ይከፍታል ጦሩ በምሽት ውጊያ ስላልገጠመው አካባቢው ሠላም እንደሆነ ገምቶ ነበር። ከይዞታው ረባዳነት በተጨማሪ ጥቂት ታንኮች ቀደም ብለው ወደፊት ወጥተው ነበርና ለሻዕቢያ ማጥቃት የተጋለጡ ሆኑ። ሻዕቢያ በቅድሚያ ታንኮቹን በመደምሰስ በጦሩ ላይ ማጥቃት ሠነዘረ። ውጊያው ተፋፋመ። ምንም እንኳን ሻዕቢያ በአሥመራ ዙሪያ ውጊያ ብዙ ኃይል ያጣ ቢሆንም ከክረን አካባቢ ተጨማሪ ረዷ ኃይል አስመጥቶ በመጠናከር የወገንን ጦር ተፈታተነው። ንዑስ ግብረ ኃይሉ የአልሞት ባይ ተጋዳይ መከላከሉን ተያያዘው። በተለይም አንድ ጥሩ ተዋጊ 84ኛ ሚሊሽያ ብርጌድ ወደኋላ ያስቀረ በመሆኑ ጦርነቱ ተፈታትኖታል። ከዚህም በተጨማሪ ድርጅት የጫኑ ተሽከርካሪዎችንና ከባድ መሣሪያዎችን ለማስጠበቅ ሌላ ኃይል ወደኋላ አስቀርቷል። ይህም ሆኖ ንዑስ ግብረ ኃይሉ ተደራቢ ኃይል እስኪደርስለት ድረስ ከጀግናውና ስመጥሩው አየር ኃይላችን ጋር በመሆን ይዞታውን ሳያስደፍር ቆየ።

ከአንድ ቀን በፊት በህዳር 14 ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" የአሥመራ ከረንን መንገድ እያሰሰ አዲተከለዛን ሳይደርስ ከ8 - 10 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የመከላከያ ቦታውን ይዞ አዳር ያደርጋል። ብ/ጀ (ሜ/ጀ) መርዕድ ንጉሴ ንዑስ ግብረ ኃይሉ አዳር ካደረገበት ቦታ ጀግናው ሌ/ኮ (ብ/ጀ) ተስፋዬ ኃ/ማሪያምን አስጠርተው ያነጋግራሉ። ብ/ጀኔራሉ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ወደ ከረን የላኩት ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" ኤላበርድ መድረሱን ቢገልፅም ከዚያ በኋላ ግንኙነት የተቋረጠ መሆኑን በመደናገጥ ይነግሩታል። በቀጣይ ቀን ጠዋት ወደ ኤላበርድ እንደሚንቀሳቀሱና ዝግጅቱንም እንዲያጠናቅቅ ለሌ/ኮ ተስፋዬ እኔ ባለሁበት ነግረውት ወደ ጦሩ ተመለሰ።

በትዕዛዙ መሠት በማግስቱ ሌሊት 11 ከ 30 ሰዓት ንዑስ ግብረ ኃይሉ ካደረበት ወጥቶ ወደ ኤላበርድ ተንቀሳቀሰ። ብ/ጀኔራል መርዕድ ንጉሴ ከንዑስ ግብረ ኃይሉ ጋር ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ለእኔ እንድ ትዕዛዝ ሰጡኝ። በሌ/ኮ አዱኛቸው አራጋው የሚታዘዘው 84ኛ ሚሊሺያ ብርጌድ ሊቀይረው የሚመጣ አንድ ብርጌድ ስላለ በአስቸኳይ አስቀይረህ እንድትከተለኝ ሲሉ ነበር ትዕዛዝ የሰጡኝ።

ኤላበርድ ሲቃረቡ ከንዑስ ግብረኃይል "ሀ" ጋር የሬዲዮ ግንኙነት በማድረግ ኮ/ል ሁሴን አህመድን በየትኛው አቅጣጫ ጠላት እንዲመታለት እንደሚፈልግ መጠየቅ ነበረባቸው። ነገር ግን ይሄንን በማድረግ ፈንታ ቀጥታ ከንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" ጋር ተቀላቀሉ። ብዙ ኃይል በአንድ ቦታ ስለተከማቸ ለሻዕቢያ አመቸው። በእርግጥ ሻዕቢያ ከባድ ጉዳት የደረሰበት ቢሆንም በዚህ የመደባለቅ ስህተት በወገን ጦር ላይ ብዙ ጉዳት ሊደርስ ችሏል። በሌላ አቅጣጫ ታቅዶ ወደ ሻዕቢያ ይዞታ ማጥቃት ቢደረግ ኖሮ በወገን ላይ ይደርስ የነበረው ጉዳት ያን ያህል ባልሆነ ነበር።

እኔ የ84ኛ ሚሊሽያ ብርጌድን ይዤ ለመሄድ ቀያሪውን ጦር በመጠባበቅ ላይ ነበርኩ። ጦሩ በጣም በመዘግየቱ በተፈለገው ፍጥነት ኤላበርድ መድረስ አልቻልኩም። በመጨረሻ የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መመሪያ አዛዥና የመከላከያ ሚኒስትር ሜ/ጀ (ሌ/ጀ) ተስፋዬ ገብረኪዳን ኤላበርድ ድረስ በሄሊኮፕተር ሄደው ከአየር ላይ የውጊያውን ክብደት አይተው ይመለሳሉ። አዲተከለዛን እርፈውም እኔን ያስጠሩኛል። "ብ/ጀ መርእድ ንጉሴ በውጊያው ከባድነት የተነሳ የድካም መልክ ስለሚታይባቸው ወደ ኤላበርድ በአስቸኳይ ተንቀሳቅሰህ እርዳቸው" ሲሉ ትዕዛዝ ይሰጡኛል።

አሁንም ቀያሪው ጦር አልደረሰልኝም። ከምሽቱ 11 ሰዓት ሲሆን ቀያሪው ጦር እየተቃረበ መሆኑን የዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው አዛዥ በሄሊኮፕተር መጥተው ስለነገሩኝ ዝግጅት ማድረግ ጀመርኩ። ለ84ኛ ብርጌድ እንደተቀየርክ ተከተለኝ የሚል ትዕዛዝ በመስጠት ከምሽቱ 11:30 ላይ ተንቀሳቀስኩ። አንድ መትረየስ የጫነች ጂፕ መኪና ከባለሙያዎቿ ጋር፣ የዘመቻ ረዳት መኮንኑን ሻለቃ (ኮ/ል) ጌታሁን እርቁን፣ የመገናኛ ኃላፊውን ሌ/ኮ ተስፋዬ ይሳቡንና 10 ባለሌላ ማዕረጎችን በመያዝ ወደ ኤላበርድ አመራሁ። እንደ ሰራዊቱ ደንብ ቢሆን ከምሽቱ 11 ሰዓት በኋላ ሠራዊቱ እንቅስቃሴ አያደርግም ነበር። ነገር ግን ሜ/ጀ ተስፋዬ ገብረኪዳን አይተው እንደነገሩኝ የሁኔታውን አሳሳቢነት በመገንዘብ እንቅስቃሴዬን ጀመርኩ። የተንቀሳቀስነው ፀሐይ በመጥለቅ ላይ ባለችበት ወቅት ስለነበር የሻዕቢያን እንቅስቃሴ ለማየት እይታችን ደካማ ነበር።

የአብረንቃቃ ጠመዝማዛ መንገድ አልፈን ወደ ኤላበርድ እንደተጠጋን ከውጊያው ከባድነት የተነሳ ጨለማውን ተገን አድርገው ወደ ኋላ በመመለስ ላይ የነበሩትን እንደገና ወደ ክፍላቸው እንዲመለሱ አደረግን። ከዚያ እንቅስቃሴአችንን በመቀጠል ከኤላበርድ ሁለትና ሦስት ኪ.ሜ ርቃ በምትገኝ ድልድይ ላይ ስንቃረብ የሻዕቢያ አድፋጮች አንድ 76 ሚ.ሜ መድፍና ቁስለኞችን የጫነ የድርጅት መኪና ያለትእዛዝ ወደ ኋላ ሲመለሱና ድልድዩ ላይ ከነቁስለኞቹ ያቃጠሏቸው ሲሆን ሌላው 122 ሚ.ሜ. መድፍ የጫነውን ደግሞ ጎማውን መትተው ሲያስቆሙት ድንገት እንደርሳለን። እኛ አንያቸው እንጂ እነሱ ግን በተቃጠለው መኪና ውጋጋንና በእኛም መኪኖች መብራት ያዩናል። የመኪናው ቃጠሎ ብርሃንና የተሳፈርንባቸው ሁለት መኪኖች መብራት የእኛን ወደ ድልድዩ መቃረብና ማለፍ ያለመቻላችንን ያሳያቸዋል። በዚህም ለረዥም ጊዜ ተኩስ አወረዱብን። ከተሳፈርንባቸው መኪናዎች በፍጥነት በመውረድ ከመንገድ ግራ ቀኝ ለፍላሽ መውረጃ በተሰራው ቦይ ውስጥ እንገባለን። ወዲያውም የአፀፋ ተኩስ መስጠት እንጀምራለን።

በዚህ መካከል ቁስለኛ አዲተከለዛን አድርሰው የሚመለሱ አራት መኪኖች መብራታቸውን በረጅሙ ለቀው ከኋላችን ይመጣሉ። የመኪናዎቹ መብራት እኛን ለሽምቅ ተዋጊዎቹ እይታ ያጋለጠ ቢሆንም በሌላ በኩል መኪናዎቹ ብዙ ወታደር ጭነው እንደመጡ በማስመሰል ስለተጠቀምንባቸው ጠቅመውናል። የሻዕቢያ ተዋጊዎች መኪናዎቹ ባዶ ሳይሆኑ ወታደር የጫኑ መስለዋቸው ኖሮ ካሉበት ሳይንቀሳቀሱ መተኮሳቸውን ቀጠሉ። የተኩሱን ብልጭታ በመመልከት እኛም መልስ እንሰጥ ጀመር።

የኛ ለሽምቅ ተዋጊዎቹ አፀፋ መስጠታችን አንድ ጥርጣሬ አሳደረብኝ። እሱም በመልስ ተኩሳችን ማነስ ኃይላችን አነስተኛ መሆኑን ይገምታል፣ ጦሩ ቦታውን እንደለቀቀ በመገመትም ሊነጋጋ ሲል ተጠናክሮ ሊያጠቁን ይችሉ ይሆናል። ስለዚህ የ506 ግብረ ኃይል አዛዥን በሬዲዮ በማግኘት ከእነርሱ 2 እና 3 ኪሎ ሜትር ርቀት የምትገኝ ድልድይ ላይ መሆናችንን እነግራቸዋለሁ። የተፈጠረውንም ሁኔታ አብራርቼ ሻዕቢያ ደፈጣ ውስጥ የገባን መሆናችንን ገለፅኩላቸው።

ብ/ጄ መርዕድ ንጉሴ "አንድ ብርጌድ ጦር ይዞ እንዴት ደፈጣ ውስጥ ገባሁ ይላል?" በማለት አጠገባቸው ላሉት መኮንኖች ሲነግሩ ሰማሁ። 84ኛ ሚሊሺያ ብርጌድን ይዤ የመጣሁ መስሏቸው እንደሆነ ገብቶኛል። እውነቱን እንዳልነግራቸው ሬዲዮናችን በአድፋጮቹ ተጠልፎ ከሆነ ከፍተኛ ኃይል እንዳሌለን ለአድፋጮቹ መረጃ መስጠት ስለሆነብኝ ብዛታችንን ሳልገልፅላቸው ቀረሁ። ብቻ በድፍኑ የመድፍ እርዳታ ጠየቅሁ። የመድፍ እርዳታ የጠየኩት የአድፋጮቹን ይዞታ ለማስደብደብ ብቻ አይደለም። በሻዕቢያ ለመማረክ የተቃረብን ሆኖ እራሳችንን ለማጥፋት ብንጠራጠርና ብንማረክ ስለወገን ኃይል መረጃ እንዳንሰጥ በመድፍ ደርበው እንዲመቱን በማሰብ ነበር። በዚህ መሠረት የመድፍ እርዳታው ታፈቅዶ አስተባባሪው ሌ/ኮ (ብ/ጄ) ዘውዱ ታደሰ በእኔ የተኩስ መሪነት ሶስት ጥይት እንዲስተካከሉ ሌላ አራተኛ ሳይተኩስ አቆሙ። ምክንያታቸውም ሻዕቢያ ፊት ለፊት የሌሊት ማጥቃት ሲሰነዝርባቸው ተኩሳቸውን ወደዚያው በማዞራቸው ነበር።

ለአደጋ የተጋለጥን ሆኖ ተሰምቶኝ ነበር። ነገር ግን ሻዕቢያ ከኛ ኋላ ያሉትን አራት የጭነት መኪናዎች አይቶ ወታደር የመጣ ስለመሰለው (እኛም በድምጽ አድፍጮቹ እንዳያመልጧችሁ ብለን በመናገራችን) ይህም የማፈግፈጊያውን መንገድ ለመዝጋት ይመስላል። ሲነጋ ጥቃት እንዳይደርስበት ሰግቶ ሌሊቱን ቦታውን ለቅቆ ሸሽቷል። ሲነጋጋ ታንክ አስጠርቼ ድልድይ ላይ የነበሩትን መኪናዎች በማስገፋት ከመንገድ ውጭ አስደረኩ። ከዚህ በኋላ ከግብረ ኃይሉ አዛዥ፣ ከዘመቻ መኮንኑና ከመድፍ አስተባባሪው ጋር በመነጋገር 130 ሚ.ሜ መድፍ ጉዳት እንዳይደርስበትና እርዳታ ሊሰጥ ወደሚችልበት ወደ አዲተከለዛን እንዲመለስ ተወሰኖ ተመለሰ።

የ130 ሚ.ሜ ወደ አዲተከለዛን መመለስ ሻዕቢያን የተሳሳተ ግምት እንዲኖረው አደረገው። ጦሩ በሸሸት ላይ ወይም ያፈገፈገ ስለመሰለው የተከማቸውን ድርጅትና ከባድ መሣሪያ ማርኮ ለማስቀረት

በሁለት አቅጣጫ ማጥቃት ሰነዘረ። በፊት ለፊትና በኋላ በኩል ውጊያ ገጠመን። ይህም የማፈግፈጊያውን መንገድ ለመዝጋት ይመስላል።

የእኔ ቡድን ባለበት የኋላ ድልድይ በኩል ከአንድ ሻለቃ ያላነሰ ኃይልና ከ10 በላይ በ12.7 ሚ.ሜ ከባድ መትረሽ (ጆሹክ) አሳልፏል። ገና ውጊያ ውስጥ ያልገባውን 84ኛው ሚሊሺያ ብርጌድ እንድጠቀምበት ከ506 ግብረ ኃይል የዘመቻ መኮንን ጋር በመነጋገር አስፈቀድኩ። ዘመቻ መኮንኑ ኮ/ል (ብ/ጄ) ውበቱ ፀጋዬ በሃሳቡ ስለተስማሙ ለትግር ጊዜ ድራሹ 84ኛ ሚሊሺያ ብርጌድ አዛዥ ለሌ/ኮ አዱኛቸው አራጋው ትዕዛዝ ሰጠሁ። ብርጌዱም በተሰጠው ትዕዛዝና መመሪያ መሠረት ተረተሩን ተከትሎ በወንበዶው ደካማ ጎን በኩል በማጥቃት በሚያካሪ ሁኔታ የሰውና የመሣሪያ ምርኮ አስመዘገበ።

ሻዕቢያ በፊት ለፊት በንዑስ ግብረ ኃይሎቹ "ሀ" እና "ለ" ሲመታ ከኋላ በኩል በሌ/ኮ አዱኛቸው በሚመራው 84ኛ ሚሊሺያ ብርጌድ ተመሳሳይ ሽንፈት ደረሰበት። በዚህም የመጨረሻ ማጥቃታቸው እንደሆነ በመወሰን በጎዳር 18 አጥቢያ ሌሊቱን ይዞታውን እየለቀቀ አፈገፈገ።

በዚህ ቀን የብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ ወሳኝ አባሎች የኤላበርድን ሁኔታ ለማየትና በሃሳብም ለመርዳት ጦርነቱ በተፋፋመበት በጎዳር 17 መጥተው እንደነበር አስታውሳለሁ። የሻዕቢያ ጦር የ130 ሚ.ሜ. መድፉን ሊረዳ ወደሚችልበት ወደ አዲተስዛን በመለስንበት ወቅት በዛ ባሉ አየር መቃወሚያ መትረየሶች እየተረዳ እኔ ባለሁበት አቅጣጫ ሲያጠቃ የተመለከቱት እነዚያ ወሳኝ አባሎች ተስፋ በመቁረጥ ይመስላል "እግዚአብሔር ይርዳችሁ" በማለት በመጡበት የብረት ልብስ ተሽከርካሪዎች ውስጥ በመግባት ከአጃቢዎቻቸው ጋር ጥለውን መሄዳቸው ትዝ ይለኛል። በዚያ ቀን ሻዕቢያ ክፉኛ የተመታበትና እነሱም ትዝብት ላይ የወደቁበት ነበር። አሁን እነዚያ ወሳኝ አባሎች አብዛኞቹ የሉም።

ከጎዳር 15 - 18 የተደረገው ውጊያ ላይ የአየር ኃይል ሁለተኛው መደብ ተዋጊ አውሮፕላኖች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እየተመላለሱ ተቃዋሚውን ተሰብስቦም ሆነ በተናጠል ሊያገኙት እንደ ኢላማው አይነት ቦምብና መትረየስ እየተጠቀሙ መትተውታል። የሻዕቢያ ጦር ኤላበርድ ላይ የነበረው ድርጅትም ሆነ ድርጅት አቅራቢ ተሽከርካሪዎችን እንዳያመለጡ በማድረግ ከፍተኛ አኩሪ ውጤት አስመዝግበዋል።

በዚሁ ዕለት ሻዕቢያን ለአየር ኃይላችን ሆነ ለታንክና ለመድፎቻችን ጥቃት ያጋለጠው አንድ ጉዳይ ነበር። ሻዕቢያ መሳሪያዎቹ አንድ ቦታ ተከማችተው ሲመለከት የራሱ ለማድረግ ከመቋመጥና ጦሩም ከአሥመራ ያስለቀቀው በመሆኑ ለመበቀል ሲል ያደረገው ውጊያ እልህ አስጨራሽ ቢሆንብንም አራሱንም ለከባድ መሣሪያና ለአየር ጥቃት አጋልጦታል። የሻዕቢያ ጦር ከምሽግ ውጪ በመገኘቱ ከፍተኛ ዕልቂትና ጉዳት ደርሶበታል። ሻዕቢያ ብዙ ተዋጊዎቹንና መሪዎቹን በማጣቱ ምክንያት በዚሁ ሌሊት እስከ ንጋቱ ድረስ በመሸሽ ከረን ያለውንም አነስተኛ ጦር ይዞ ከከረን ሰሜን ምሥራቅ ወደምትገኘው የአትክልት ቦታ እንዲሄዱ ተገደዱ። በዚህም ሻዕቢያ ያለምንም ውጊያ ከረንን ለቆ ወጣ። በመሸሽ ላይ ሳለም ጀግናው ሁለተኛው የአየር መደብ እየተከታተለ መትቶታል። ተሽከርካሪዎቻቸውን ከጫኑት ሰውም ሆነ ድርጅት ጋር አብሮ ደምስሷል። ጦሩ በአካባቢው ያሉትን የሻዕቢያ ጦር እሬሣና መስዋዕትነት የከፈሉትን የወገን ጦር አስከሬን በተቻለ መጠን ከቀበረ በኋላ ቀሪውን ሥራ ለአካባቢው ህዝብ አስረክቦ የማሳደድ ማጥቃቱን ቀጠለ።

በቀጣዩ ቀን ማለትም በሀዳር 18 የማሳደዱን ውጊያፍጥነት ለመጠበቅና ሻዕቢያ ለመልሶ መቋቋም ጊዜ እንዳያገኝ በማድረግ ከከረን 10 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ደረስን። ይሄ ቦታ ሐቢብ መንተል ከምትባለው መንደርና ሩባ አንሰባ ከሚባለው ወንዝ ድልድይ አጠገብ ነበር። እዚያ እንደደረስን ከዘመቻው ቀዳሚ መምሪያ አንድ መመሪያ ደረስን። "ባላችሁበት ቁሙ" የሚል ትዕዛዝ። የግብረ ኃይሉ አዛዥ ብ/ጄ መርዕድ ንጉሴ በትዕዛዙ መሠረት ጦሩ እንዲቆምና ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ይዞ ትዕዛዝ እንዲጠባበቅ አዘዙ። ካዘዙም በኋላ ቀዳሚ መምሪያውን "አሁን ያለነው ከከረን ከ8 — 10 ኪ.ሜ. ላይ ነው። በሁለት ሰዓት ውስጥ ከረን በመግባት ሻዕቢያን መልሶ ሳይቋቋምና ሳይጠናከር እንዲሁም ሳይርቅ ማጥቃታችንን እንድንቀጥል ይፈቀድልን" ሲሉ ጠየቁ። አልተፈቀደም። ተንኮል ነበረውና። በአንድ ዘመቻ ሁለት ትልቅ የዘመቻ ስህተት መሆኑ ነው።

የ506 ግብረ ኃይል ሐቢብ መንተል ላይ እንዲቆም በተደረገ ማግስት ማለትም በጎዳር 19 ከረን በ508 ግብረ ኃይል ያለውጊያ መያዙን በሬዲዮ ሰማን። ቀዳሚ የዘመቻ መምሪያ ከውጊያው ውጤት ይልቅ በጦሩ መካከል የታሪክ ሽሚያና ቅሬታ የሚፈጥሩ ነገሮችን ያደርግ ጀመር። የኤላበርድ ውጊያ ለከረን መያዝ ወሳኝ ስለነበር ሻዕቢያ ከአሥመራ ዙሪያ ይልቅ ጠንክሮና ጥርሱን ነክሶ ተዋግቷል። በቂ

የተዘጋጀ ምሽግ ላይኖረው ለሦስት ቀን ያለማቋረጥ ተዋግቷል። ሻዕቢያ 506 ሻብረ ኃይልን ኤላበርድ ላይ ድል ቢመታ ኖሮ ከረን ላይ በነበረው ጠንካራ ምሽግ ምክንያት 508 ግብረ ኃይልን ለብዙ ጊዜ ሊቋቋመው እና ሊጎዳውም በቻለ ነበር።

የ506 ግብረ ኃይል ሻዕቢያ በመሸሽ ላይ በነበረበት በዚያ ዕለት ተከታታይ ማጥቃቱን እንዲገታ ባይታዘዝ ኖሮ ከረንን በጧት ከመያዙም በላይ የሻዕቢያን ሁኔታ ከ508 ግብረ ኃይል በላይ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ አጠናቆ መምታት በቻለ ነበር። የሻዕቢያም ዕድሜ እዚያች ዕለት ላይ ባበቃ ነበር። አሁን ያጋጠመው ሁኔታ ላይ ባልዳረሰም ነበር።

ቀዳሚ መምሪያው ለምን 506 ግብረ ኃይልን እንዳቆመው ተጠይቆ ነበር። "በመካከላችሁ ባለመተዋወቅ እርስ በእርሳችሁ ግጭት እንዳታደርጉ ነው" የሚል ምላሽ ሰጠ። ይህ እንዳይሆን በራዲዮ ግንኙነት መፍታታ ይቻል ነበር። በዚያ ላይ 508 ግብረ ኃይል ከረን የገባው 506 ሊገባ ከሚችልበት በአንድ ቀን ዘግይቶ በመሆን ግጭት እንዳይነሳ ከመስጋት እንዳልሆነ ግልፅ ነው። ያም ሆነ ይህ በህዳር 20 የ508 ግብረ ኃይል ተጠሪ ያረፍንበት ሀቢብ መንቱል ድረስ መጥቶ አርማዎቻችንን በመለዋወጥ በዚያ ዕለት ከረን ገብተን አደርን።

በስህተት ላይ ስህተት መደራረቡ አላበቃም። የ508 ግብረ ኃይል ከሽሬና ጎንደር እስከ ባሬንቱ ከአየር ጠባይና ከወንዞች ሙላት አስቸጋሪነት በቀር ያለከባድ ውጊያ ከገባ በኋላ ከባሬንቱ ወደ አቆርዳት ተንቀሳቅሶ ከገባ በኋላ ወደ ከረን በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ብቻ መጠነኛ ውጊያ ገጥሞታል። ይህም 506 ግብረ ኃይል ያለዕቅድ እንዲንቀሳቀስ የተደረገበት አንገርኔ ላይ ያጋጠመውን ውጊያ በቀላሉ ተወጥቶ ኃይሉ ሳይቀናነስበትና ሳይጎዳ ከረን ገባ። ከዚህ በኋላ ከረን ከተማ ውስጥ እንዲቀመጥ ከሚወሰን ይልቅ ወጣ ወጣ ብሎ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ቢይዝ ኖሮ አሥመራና ኢላበርድ ላይ የተጎዳው ሻዕቢያ እዚያ ላይ ያበቃለት ነበር። ግን ይሄ ሳይሆን ቀርቶ ከፍተኛ ውጊዎችን ፈፅሞ የተጎዳ መሆኑ እየታወቀ 506 ግብረ ኃይል አሁንም ማጥቃቱን ወደ አፍአበት እንዲቀጥል ትዕዛዝ ከዘመቻ ቀዳሚ መምሪያው መጣ።

ሻዕቢያም ከከረን 2 እና 3 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኘው የአትክልትና ፍራፍሬ ሥፍራ ነበር። እዚያ አርፎና ፍራፍሬ ሲመገብና ሲዝናና ቆይቶ 506 ግብረ ሃይል ከረን ሲገባ ከረን ላይ ሁለት ተዋጊ ግብረ ኃይሎች እንደመጡበት አውቆ ቦታውን ለቆ ተንቀሳቀሰ። ቀደም ሲል በክ/ል (ብ/ጀ) ለሜላ በዳሶ አዝማችነት በጥሰ ብርጌድ አፍአበትን እንዲይዝ መላኩ

ይታወሳል። ሻዕቢያ በጥሰ ብርጌድን መስሐሊት ላይ ጠብቆ አግዶትም ነበር። አሁንም ቀደም ሲል ወዳጠናከረው የመስሐሊት ምሽግ በመሄድ ገባ።

መስሐሊት ከጀርባዋ ሁለት ሰንሰለታማ ተራሮች ያሉባት ሜዳ ናት። በሁለቱ ተራሮች መካከል ወደ አፍአበት የሚወስድ ጠመዝማዛ መንገድ አለ። ከፊት ለፊታ የአንሰባ ወንዝ የሚያቋርጠው በጣም ሰፊ ገላጣ ሜዳ አለ። የሻዕቢያ መከላከያ ምሽግ በእነዚህ ተራሮች ጥግና ታች ሜዳው ላይ ነበር።

በትዕዛዙ መሠረት የ506 ግብረ ኃይል ከ10 እስከ 15 ኪ.ሜ የሚሆነውን ሜዳማ ቦታ አቋርጦ ለማለፍ መሞከር ጀመረ። ይሁንና የመከላከያ ሥፍራዎቹን ይይዛሉ ብሎ ካልጠበቀው ከሜዳማው ቦታ መሸጎ ኖሮ ተኩስ ተከፈተበት። ለማጥቃት ቢሞክርም ምሽግ ውስጥ ለተደበቀው ሻዕቢያ ተኩስ ምቹ በሆነ ሜዳ ላይ በመሆኑ ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት።

ጀርመናዊው እስትራቴጂስት ክሉዝዊትስ በTHE ART OF WAR መጽሐፉ "ማጥቃት ጀምረህ ድልን የተጎናፀፍክ ከሆነ ያለማቋረጥ ጠላትህን እየተከታተልክ አጥቃ፣ ማጥቃትህን ትተህ ከቆምክ ግን ጠላትህ ድክመት እንዳለብህ በመረዳት መልሶ በመቋቋም ችግር ይፈጥርብሃል" ይላል። በእኛም በኩል የተፈጠረው ስህተት የዚህ ዓይነቱ ነው። ያለማቋረጥ ተከታትለን ባለማጥቃታችን፣ ከተማን ከያዝን በኋላ ከከተማ ውጣ ወጣ ብለን ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ለመያዝ እንደማንሞክር የተረዳው ሻዕቢያ ይህ ድክመታችንን አውቆ መሰሐሊት ላይ መልሶ ማቋቋም በማድረግ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰብን። በዚህም ሻዕቢያ የአሥመራ ዙሪያውን የኢላበርድን ጥቃት በመጠኑም ቢሆን ተብቀለ ለማለት ይቻላል።

ለማንኛውም ይሄ አቅጣጫ የሚያዋጣ ባለመሆኑ በሌላ አቅጣጫ ለማጥቃት አስበን ዕቅድ አወጣን። ለዕቅዱ መሳካት የ508 ግብረ ኃይል አዛዥን ድጋፍ ጠየቅን። እኛ በጎን ሄደን በጠላት ደካማ ጎን በኩል ለማጥቃት ስላሰብን የፊት ለፊቱን ጠብቅልን አልነው። የ508 ግብረ ኃይል "ከበላይ አልታዘዝኩም" የሚል ምላሽ ሰጠን። እንዲጠብቅልን የጠየቅንበት ምክንያት የፊት ለፊቱ ሻዕቢያን ወደ ከረንና ጦሩ ወዳለበት የሚያስገባ ክፍት ቦታ ነበር።

በኤርትራ ውጊያ የታየው ትልቁ ድክመት የጦሩ ከፍተኛ የበላይ አዛዦች በጦሩ መሀል ያለትዕዛዝ የመረዳዳት መንፈስ እንዲኖር፣ እንዲጠናከርና እንዲዳብር አይገፋፋም ነበር። አንዱ ክፍል በውጊያ ሲያዝ "ሳልታዘዝ እርዳታ ብሰጥ ቅጣት ይደርስብኛል" በሚል ስጋት አጠገቡ ያለውን ጦር ለመርዳት ትዕዛዝ ይጠብቅ ነበር። በዚህ ምክንያት ጠላት በተኩስ ስለማይጠመድ ያለስጋት ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሰ በመረዳዳት፣ በመከላከልም ሆነ በማጥቃት ጊዜ በወገን ላይ ጉዳት ያደርስ ነበር። በኤርትራ ውስጥ ከተደረጉ ውጊያዎች አብዛኞቹ ውጤት አልባ የሆኑትም በዚህ የተነሳ ነው።

የ508 ግብረ ኃይል "ከበላይ አልታዘዝኩም" በማለት ባይረዳንም እኛ የፊት ለፊቱን ማጥቃት እንደገና ሞክረን ነበር። ሳይሳካልን ቀረ። በዚያ ውጊያ ብዙ ነባርና በሳል መኮንኖቻችንንና በተዋጊነታቸው የታወቁ ባለሌላ ማዕረጎቻችንን አጥተናል።

የ506 ግብረ ኃይል በሰሜን ጦር ግንባር ብዙ የደከመ፣ ከአሥመራ እስከ መስሐሊት ባደረጋቸው ውጊያዎች በዛ ያለ ኃይሉን በማጣቱና በመዳከሙ የግዳጅ ትዕዛዝ ለውጥ ማድረግ አስፈለገ።

በ506 ግብረ ኃይል መዳከም ሳቢያ በተደረገው የግዳጅ ትዕዛዝ ለውጥ የዕዝ ልውውጥ ሲካሄድ እኔ ከ506 ግብረ ኃይል ምክትል አዛዥነት ወደ 508 ግብረ ኃይል ምክትል አዛዥነት ተዘዋወርኩ። የ506 ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" አዛዥ ኮ/ል ሁሴን አህመድ ወደ አሥመራ ተዘዋውረው የ14ኛ ክፍለ ጦር አዛዥና የአሥመራ ዙርያ ጥበቃ ሃላፊ ሆኑ። በምትካቸው የ504 ግብረ ኃይል አዛዥ የነበሩት ኮ/ል (ሚ/ጄ) ቱምላቸው ደጀኔ ከመቀሌ መጥተው የ506 ግብረ ኃይል ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" ዕዝን ተኩዋቸው። የ506 ግብረ ኃይል ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" ደግሞ በጀግናው በሌኮ (ብ/ጄ) ተስፋዬ ሀ/ማሪያም እየተመራ የከረንን ከተማ ጥበቃና የበላይ አስተዳዳሪ ሆነው ተመደቡ።

በዚህ የግዳጅ ትዕዛዝ ለውጥ መሰረት ብዙ ጉዳት የደረሰበት የ506 ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" ለ508 ግብረ ኃይል ተደርቦለት አፍአበትን ከዚያም ናቅፉን እንዲይዝ ለ508 ግብረ ኃይል ትዕዛዝ ተሰጠ። በትዕዛዙም መሠረት ከጠንካራ ውጊያ በኋላ አፍአበትን ያዘ። የ508 ግብረ ኃይል በውስጡ ልምድ ያላቸው ጠንካራ መኮንኖችና ነባር ባለሌላ ማዕረጎችን የያዘ ስለነበር እስከ ናቅፉ ድረስ ውጤቱ በጣም የሚያስደስትና የሚያኮራ ነበር። ናቅፉ ከደረሰ በኋላ በመሬቱ አስቸጋሪነትና የቦታውንም ሁኔታ በደንብ ካለማወቅ የተነሳ ይመስላል፣

ሻዕቢያ ከተለያየ አቅጣጫ ተሰባስቦና ተረባርቦ ባጠቃው ጊዜ ይዞታውን ለቆ ወደኋላ እንዲመለስ ተገደደ። ይሽኔ ያ በችግሩ ወቅት ያልረዳው የ506 ግብረ ኃይል ንዑስ ግብረ ኃይል "ሀ" መረዳዳት ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ስለሚያውቅ በሌላ አቅጣጫ ጠላትን አጥቅቶ 508 ግብረ ኃይል የለቀቀውን ቦታ መልሶ እንዲይዝ አድርጎታል።

ከ506 ወደ 508 ግብረ ኃይል መዘዋወር ላይ ላዩን እንደሚታየው የግብረ ኃይል ለውጥ ብቻ አልነበረም። ውስጥ ውስጡን ያመረቀዘ የመናናቅና የእኔ እበልጥ የእኔ እበልጥ ፉክክር በጦር ክፍሎች መካከል ስለነበር ከ508 ግብረ ሃይል ጋር በቀላሉ መቀላቀል ተስኖኝ ነበር። አዲስ የተዛወርኩበት ግብረ ኃይል ሙሉ ለሙሉ ስላልተቀበለኝና ምግቤን እንኳን ለማግኘት ስለተቸገርኩ የምበላው ከቀድሞ ክፍሌ ከ506 ንዑስ ግብረ ኃይል "ለ" መኮንኖች ጋር ነበር።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ ቅሬታዎችም ያድሩብኝ ነበር። 508 ግብረ ኃይል አፍአበትና ናቅፉ ከመነቃነቁ በፊት አዛዡ ለለማካሪዎቻችን 506 ግብረ ኃይልን እንደተለመደው ቢሸሽ በሚልና በማናናቅ ሲናገሩ በተደጋጋሚ በመስማቴ እጅግ ቅሬታ ያድርብኝ ጀመር። ይህ ግብረ ኃይል ኤርትራን 2ኛው አብዮታዊ ሠራዊት እስኪመጣ ድረስ በተቃዋሚዎች ሙሉ በሙሉ እንዳትያዝ ጠብቆ ያስረከበ ክፍል ነው። ከዚህ ክፍል ጋር ለረዥም ጊዜ የሠራሁና ስለታሪኩም ስለማውቅ አዛዡ ይሄንን ማንቋሸሺያ ንግግር እንዲተዉ በተደጋጋሚ ብነግራቸውም ስላልተዉ ከአዲሱ ግብረ ኃይል ጋር ያለኝ የሥራ ፍላጎት እየጠፋ መሄድ ጀመረ። በዚህም ከግብረ ኃይሉ ጋር ከመነቃነቁ በፊት ከዚህ ቀደም የሀገር ጉዳይን በማስቀደም የተውኩትን የህክምና ፈቃድ ቀሰቀስኩ። በእግሬ ህመም ምክንያት ሜዲካል ቦርድ ገብቼ ወደ አዲስ አበባ እንድሄድ ተወሰኖ አዘግይቼው ነበር። አሁን ግን ሁኔታው ሁሉ ስላላማረኝ የሜዲካል ቦርድ ወረቀቴን ለዘመቻ ቀዳሚ መምሪያ አሳይቼ ለህክምና ወደ አዲስ አበባ ተንቀሳቀስኩ።

በ"ምስክርነት" መጽሐፍ መስተካከል ያለባቸው የተዛቡ ታሪኮች

በሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ተዕፎ "ምስክርነት" በሚል ርዕስ ታትሞ ግንቦት በ2001 ዓ.ም ለገበያ የቀረበው መጽሐፍ ከገጽ 312 - 313 ላይ እንደተጠቀሰው የአሥመራ ከረንን መንገድ ለመክፈት በብ/ጀ (ሚ/ጀ) መርዕድ ንጉሤ የተመራው 506 ግብረ ኃይል በዕርግጥም ጉዳት ደርሶበታል።

ጉዳት የደረሰው ግን መጽሐፉ እንደሚያትተው ከችኮላና ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሳ ወይም ለታሪክ ሹሚያ ሳይሆን አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያው (ኮ/ል) ንብረክርስቶስ ቡሊና አማካሪዎቻችን አንድ ጦር ሊንቀሳቀስ በማይገባው ሰዓት ሁለት ግብረ ኃይል አጣምሮ የያዘውን 508 ግ/ኃይልን በአቆርዳት አካባቢ በተኩስ ተይዟል በማለት በመደናገጥ ከመሸና በመኪና መብራት ካልሆነ በቀር መንገዱ በማይታይበት ሁኔታ ከጨለመ በኋላ እንዲንቀሳቀስ በመታዘዙና በመንቀሳቀሱ ነው።

ከዚህ ሌላ የ506 ግብረ ኃይል ኤላበርድ ላይ እጅግ ዘግድ ውጊያ አድርጎና ብዙ መስዋዕትነትን ከፍሎ ተቃዋሚዎችን ከደመሰሰ በኋላ ወደ ከረን ተንቀሳቅሶ ከረንን ለመያዝ በመዘገስ ላይ እያለና የአንድ ሰዓት ጊዜ ብቻ ሊወስድበት በሚችል ርቀት ላይ እያለ ካለበት ቦታ ለይ እንዲቆም ከዘመቻ መምሪያው የታሪክ ሹሚያን የፈጠረ ትዕዛዝ ደርሶት ባይቆም ናሮ ቀድሞ ከረንን ይይዝ ነበር። የ506 ንዑስ ግ/ኃይል (ሀ) አዛዥ ኮ/ል (ሚ/ጀ) ሁሴን አህመድም ለታሪክ ሹሚያ ሲሉ ወደ ኢላበርድ ያለ ዘመቻ መምሪያው ትዕዛዝ አልተንቀሳቀሱም። ንዑስ ግ/ኃይል «ሀ»ን ይዘው የተነቃነቁትም እሳቸው ናቸው። የቀዳሚው ብርጌድ አዛዥ የነበሩት ሌ/ኮ (ኮ/ል) በቀለ ኃይሌ ኤላበርድ እንደደረሱ በጨለማ ሊያስይዙ የማይችሉትን ቦታዎች ሁሉ አስይዘዋል። ጥፋታቸው አይታየኝም። ይህንንም ከዚህ ከእኔ ጽሁፍ መረዳት ይቻላል።

እግረ መንገዴን በዚሁ "ምስክርነት" መጽሐፍ ላይ በተለያዩ ገጾች ውስጥ ስለ ብ/ጀ ታረኩ አይኔ የባፋትን የተዛባ መረጃ ጥቂት ልበል። ፀሀፊው ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ፣ ብ/ጀ ታረኩ አይኔን እንደ ጀግና ቆጥረው ያመሰግኑና ያሞካሹ አስመስለው ከሥነ ሥርዓት ውጪ በሆነ መልኮንኖችንና አለቆቹን የሚሳደብ፣ የሚጋፋና የሚንቅ አድርገው ስለውታል። እንድ መኮንን ጠንካራ ሠራተኛ ቢሆን እንኳ በጠባዩ ያልታረመ፣ ሥነሥርዓት የሌለውና አለቆቹን የሚጋፋ ከሆነ እጅጉራልነት ማዕረግ ሊደርስ አይችልም።


እኔ የ2ኛ ክ/ጦር ዘመቻ መኮንን ሆኜ እሱም የ35ኛ ሻለቃ አዛዥ ሆኖ አብረን ስለሠራን እንዲህ ያለ ጠባይ አለየብትም። ያላመሰክት ትዕዛዝ ሲሰጠው ግን ሊከራከር ይችል ይሆናል።

ብ/ጀ ታረኩም የክብር ዘበኛ መኮንኖችንም እንደሚንቅና ይጠላ እንደነበር በዚሁ መጽሐፍ በገጽ 280 ላይ "የክብር ዘበኞች ለአጃቢነት እንጂ ለጦር አለቅነት ብቁ አይደሉም" የሚል ጽሑፍ ሠፍሯል። ፅሁፉ ስድብም

ስላለበት ሌላውን ትቸዋለሁ። ጀ/ታረኩ የክብር ዘበኛን ታሪክ በደንብ ስለሚያውቅ ይህን ይላል ብዬ አላምንም። በእርግጥ ካለም የመጽሐፉ ደራሲም ሆነ ብ/ጀ ታረኩ ተሳስተዋል።

የክብር ዘበኛ ሠራዊት በተባበሩት መንግሥታት ጥያቄ በኮሪያና በኮንጎ መዘመቱና አኩሪ ሥራ መሥራቱ ይታወቃል። በተለይ በሩቅ ምስራቅ በኮሪያ በዘመተበት ጊዜ በማያውቀው መሬትና በማያውቀው የአየር ጠባይ በፈጸማቸው አኩሪ ውጊያዎች እንኳን በሕይወት ያለውን፣ ቁስለኛና መስዋዕት የሆኑትን አባሎቹን ሳያስማርክ የመጣ ጀግና ሠራዊት ነበር። ይህም የሆነው በአለቆቹና ከክብር ዘበኛ ጦር አካዳሚ በተመረቁት ወጣት መኮንኖች ብልህነትና ጠንካራ አመራር ነው። ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ በተደረገው ዘመቻ ሁሉ በቦታው ላይ ተገኝቶ ባየው በግሪክዊው ደራሲ ኪሞን አስኮርዲለስ (KIMON SKORDILES 1954) እሷል የተፃፈውንና በኋላም በአቶ በጋሻው ድረሴ ወልደ ሰማያት ተተርጉሞ በኛው ዘመን አቆጣጠር በ2000ዓ.ም የታተመውን "ቃኘው" የተሰኘውን መፅሐፍ ማንበብ ስለክብር ዘበኛ መኮንኖችና ሠራዊት የበለጠ ግንዛቤ ይሰጣል ብዬ አምናለሁ።

የቃኘው ሻለቃና የመኮንኖች አኩሪ ታሪክ በተባበሩት መንግስታት ድርጅትም ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛል። ሰፊጸሙትም አኩሪ ተግባር ከተባበሩት መንግስታት፣ ከአሜሪካ መንግሥትና ከደቡብ ኮሪያ መንግስት እንዲሁም ከኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ የጀግና ሜዳልያዎችን ተሸልመዋል። ለዚህ የሚያኮራ ጀግንነታቸውም በደቡብ ኮሪያ ሕዝብና መንግሥት በዚያ ጦር ሜዳ ሰዋሉት ለሌሎች መንግሥታት ጦሮች ያልተደረገውን ለቃኘው ሻለቃ ብቻ መታሰቢያ እንዲሆን ለኮሪያ ዘማቾች ጽ/ቤት የሙዚየምና የስብሰባ አዳራሾችን ሠርተው አስረክበዋል። በኮሪያም ለሌሎች ያልተደረገ ለኢትዮጵያ ጀግኖች ከ16 (አሥራ ስድስት) ሜትር የሚበልጥ ትልቅ ሐውልት ሠርተውልናል። እንዲሁም የቀድሞው የአፍንሎ በር መናፈሻ በእሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኮርያ ዘማቾች ፓርክ ተብሏል። የኢትዮጵያ ኮርያ ዘማቾች ፓርክ በተባለው መናፈሻ ደግሞ ከጽሕፈት ቤቱና ሙዚየሙ ሌላ ኮርያ ላይ የተሰራውን ሐውልት ተመሳሳይ ከ16 ሜትር በላይ የሆነ የመታሰቢያ ሐውልትና በኮሪያ ጦር ሜዳ መስዋዕት ለሆኑት መኮንኖችና ባለሌላ ማዕረጎች ለአያንዳንዳቸው ስማቸው እየተቀረፀበት በኮርያ መንግስትና ሕዝብ መታሰቢያ ሐውልት ቆሞላቸዋል። ታሪክን ለማወቅና ክልዩ ልዩ ወታደራዊ መሪዎችና የሐገር መሪዎችም የተሰጠውን ምስክርነት ሙዚየሙን በመጎብኘት እውነቱን መረዳት ይቻላል።




የኢትዮጵያ ጀግኖች በኮሪያ ቹንቾን የቆመ መታሰቢያ ሐውልት
lonument dedicated to Ethiopian heroes in Korea (Chooncht

ከግርማዊ ቀኃሥላሴም የድል አርማቸው እንዲሆን ተሰጥቷቸው ይዘውት የሄዱት ሰንደቅ ዓላማም ለፊጸሙት አኩሪ ተግባር ሦስት ጊዜ ከተባበሩት መንግሥታት የጀግና ሜዳልያ ተሸልሟል። በዚህም ዘመቻ አገራቸውን አኩርተውና አስመግነው ተመልሰዋል።


ስለዚህ ከሌላው አገር ታሪክ ይልቅ በቅድሚያ የራስን አገር ታሪክ ማወቅ ተገቢ ይመስለኛል። ጥፋት ያለበት ደካማ መኮንን ካለ በተለይ ስሙ ተጠቅሶ መጻፍ አለበት እንጂ በአጠቃላይ የክቡር ዘበኛ መኮንኖችን መውቀስና መስደብ ያለባቸው አይመስለኝም። "ምስክርነት" መጽሐፍ በአብዛኛው ስድብ አዘል ጽሁፍ ነው። ዳግመኛ ላለመስደብ ሁሉንም አልጻፍኩትም። ታሪክን የሚያውቅ ሁሉ ሲያነበው እንደሚያዝን እርግጠኛ

ነኝ። አንድ አሉባልታ ያዘለ ጽሑፍ ከመጻፍ በፊት በተለይ የመጽሐፉ ደራሲ የደህንነት መኮንን ከሆነ የተነገረውን እንዳለ ከመጻፍ ይልቅ የተገኘውን መረጃ በብዙ አቅጣጫዎች በመጠየቅና በመመርመር አመዛዝኖ እውነተኛነቱንም አረጋግጦ መጻፍ ተገቢ ይመስለኛል። በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ተቻኩሎ ውሳኔ ላይ ከመድረስ የተነሳ በደርግ ዘመን በተሳሳተ መረጃ የብዙ ሰው ሕይወት እንደጠፋም እገምታለሁ። እንዲሁም ባለፈው መንግሥት በተለያዩ ስሞች በተቋቋሙ የጦር ትምህርት ቤቶች የሰለጠኑ ብዙ መኮንኖች አሁንም በሕይወት ስላሉ ያለበቂ ማስረጃ ስም እየተጠቀሰ በ"ምስክርነት" የተጻፈው አሉባልታ የሚያቀያይም፣ በወቃሹም ሆነ በተወቃሹ መሣል ቅሬታን የሚያስከትል ነው ብዬ እገምታለሁ። መልስ ሊሰጥ አይችልም በሚል በሕይወት በሌለ ሰው ላይ ማላከክም ተገቢ ስላልሆነ በድጋሚ የሚታተም ከሆነ ቢታረም እላለሁ።




የጀግኖች የኢትዮጵያ ኮርያ ዘማቾች መታሰቢያ ሀውልት በኮርያ ዘማቾች ፓርክ (የቀድሞው አፍንጮ በር መናፈሻ) ጡሩ ብሎ የሚታየው ስም እየተጻፈበት ለእያንዳንዳቸው በኮርያ ጦር ግንባር መሰዋዕት ለሆኑት መኮንኖችና ባለማዕረጎች የቆመ መታሰቢያ ነው

አሁንም እግረ መንገዴን በሻለቃ ጌታቸው የሮም ተሰማ በ1993 ዓ.ም የታተመው "ፍረጂ ኢትዮጵያ" የሚለው መጽሐፍም ላይ ስለ ምሥራቁም ሆነ ስለ ሰሜኑ ውጊያ ያተዘገበው ብዙ ከእውነት የራቀ ስለሆነ



የኢትዮጵያ ጀግኖች በኮሪያ ቹንቾን የቆመ መታሰቢያ ሐውልት

Ionument dedicated to Ethiopian heroes in Korea (Choonchu



የጀግኖች የኢትዮጵያ ኮርያ ዘማቾች መታሰቢያ ሀውልት በኮርያ ዘማቾች ፓርክ (የቀድሞው አፍንጮ በር መናፈሻ) ጠቅር ብሉ የሚታየው ስም እየተግፈበት ለእያንዳንዳቸው በኮርያ ጦር ግንባር መስዋዕት ለሆኑት መኮንኖችና ባለማዕረጎች የቆመ መታሰቢያ ነው

አንባቢያን ሌሎች መጽሐፍትን በማንበብ አመሳክረው ወደ እውነቱ እንዲጠጉ አደራ እላለሁ። 506 ግብረ-ኃይል ከአዲተከለዛን ወደከረን የተንቀሳቀሰው ያለአግባብ ላይሆን በትዕዛዝ የተፈፀመ እንቅስቃሴ እንጂ ለታሪክ ሽሚያ አይደለም። ሻለቃ ጌታቸው የሮም ከእኔ ጋር አብሮ ዘምቶ የሚያዘውን የነበልባል ሻለቃ ጦር አክሱም ላይ ለምን በትኖ እንደከዳ እንኳ ሳይገለጽ ምንም ስለማያውቀው የ506 ግብረ ኃይል ግዳጅ የታሪክ ሽሚያ ነው ብሎ ጽፏል። አሉባልታ። ቅጥፈት።

የህይወት ምስረታ
ጋብቻ

"ሰው አባቱን እና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ጋር አንድ ይሆናል።"
ዘፍ. 2፡23-24

"ሰው አባቱን እና እናቱን ይተዋል፣ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"
ማር. 7፡7

የውትድርና ህይወት በአጠራጣሪ ነገሮች የተሞላ ኑሮ ነው። አብሮህ እየተሳሳቀ የወጣ የበረሃ ጓድህ በአፍታ ውስጥ ከየት እንደተተኮሰች እንኳ በማይታወቅ ተባራሪ ጥይት ከህይወት ወደ ሞት ሲሸጋገር ትመለከታለህ። ያንተም ዕጣ-ፋንታ ያቺን የመሰለች አንዲት ቀን እንደምትጠብቅ ይሰማህና አስረዝሞ ማቀዱን በይደር መተለሙን ትተወዋለህ። በመሰናክሎች የተሞላው የውትድርና ህይወት የየዕለቱ መሰናክል ላይ እንጂ በመጪው የግል ጉዳይህ ላይ እንድታስብ ዕድል አይሰጥህም።

እኔም የገጠመኝ ይሄው ነው። እዚህ እደርሳለሁ ብዬ ላልም በማልችልበት አኳኋን ከብዙ ጦርነቶችና ከአልፍ ሞቶች አምልጬ አዲስ አበባን በድጋሚ አየኋት። ተአምር ነው የሆነብኝ። ከጥይት ድምፅ፣ ከማጥቃት፣ ከማፈግፈግ፣ ከመማረክና ግዳይ ከመጣል--- አዙሪት ውስጥ የወጣ ሀሳብ ማሰብ የጀመርኩት የሰሜንን አካባቢ እንደለቀቅኩ ነበር።

ጉርምስና ነጉዷል፣ ወጣትነት ሄዷል፣ ጎልማሳነት እየተገባደደ ነው፣ ነገር ግን እራሴን ስፈትሽ የእኔ የምለው ቤትና ትዳር የሌለው ኦና ሆኖለሁ። ይሄ ሐሳብ እርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ስሰራ ነበር። እንደውም ያኔ መንገድ ጠረጋ ላይም ነበርኩ። ወ/ሪት ሰናይት ሽፈራውን ተዋውቄ ትዳር የመያዝ ዳር ዳርታ ላይ እያለሁ በሥራ መብዛትና ከቦታ ቦታ በመዘዋወር አጥብቄ ላልይዘው ቀረሁ። ወደ ሰሜን ዕዝ ስዘዋወር እዚያው የህይወት አጠራጣሪት ውስጥ ተዘፍቄ ለራሴ ማሰብ ተስኖኝ ቆየሁ።

አሁን እንደ ሁኔታውና እንደ አካባቢው ማሰብ ጀመርኩ። ለህክምና አዲስ አበባ ውስጥ ስድስት ወራት መቆየት እንዳለብኝ የጦር ኃይሎች ሜዲካል ቦርድ ወስኗል። ስድስት ወር በጣም ረጅም ነው። በውትድርና ህይወት ውስጥ ያን ያህል ሠፊ ጊዜ ግልጥጥ ብሎ ሊታይህ አይችልም። ዛሬ ስታጠቃ፣ ነገ ስትካላከል ወይም ከነገ ወዲያ--- የተቆጠበች ህይወትህን ለመውሰድ እንዲት ኢምንት አረር የተሳፈረ መልአኩ-ሞት ወደአንተ ሊመጣ ይችላል።

በህክምና ላይ እያለሁ ነው አንድ የማይታሰብ ገጠመኝ ወደ ህይወቴ የመጣው። ከዚህ በፊት ዕርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን እያለሁ የማውቃትን ወ/ሪት ሰናይትን በአጋጣሚ አገኘኋት። ያኔ የያዝኩት እጇ በአጋጣሚ ከእጄ ወጥቶ ሲቆጨኝ የቆየ ነገር ኖሯል። አጋጣሚው እንዲያመልጠኝ አልፈለኩምና ቀጥታ የትዳር ጉዳይ አነሳሁባት።

"እንዴት ነው ኑሮ? ህይወት?"

"ጥሩ ነው" አለችኝ

"አገባሽ? ወለድሽ?"

"አረ አላገባሁም፣ አንተስ? አገባህ?"

"እንዳውም"

በረጅሙ ተነፈስኩ። ልቤ በጥርጣሬ ተወጥራ ነበር። ብታገባስ? ትዳር ይዛ ቢሆንስ? ግማሽ ጭንቀቴ ተራገፈ። ካላገባች፣ ትዳር ካልያዘች እሷን የእኔ ለማድረግ ሃምሳ ከመቶ ዕድል አለኝ ማለት ነው።

"እና አሁን ምን ታስቢያለሽ"

"ማለት?"

ትዳር ስለመያዝ?--- እ---" አትፈልገኝ ይሆን? የሚል ጥርጣሬ መጥቶ እላዬ ላይ ሰፈረ። ምን አደርጋለሁ?